# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢኮኖሚ ልማትንና የማህበራዊ ኑሮ እድገትን ለማምጣት በሚደረገው ሀገራዊ ጥረት የመንገድ ዘርፍ ትኩረት ወሳኝ ድርሻ አለው፡፡ በሀገራችን ካሉት የመጓጓዣ ዘዴዎች የየብስ ትራንስፖርት ጠቀሜታ ድርሻ ከ95 በመቶ በላይ መሆኑ የመንገድ አውታሩን የማስፋፋትና የማሻሻል ሥራን አስፈላጊነት እጅግ የጎላ አድርጎታል፡፡
2. በሀገራችን የመንገድ ግንባታ ወጥነት ባለውና ተቋማዊ ይዘትን ተላብሶ የተጀመረው በ 1940ዎቹ መጀመሪያ ሲሆን የዛሬው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሰነገስት ዘመን የአውራ ጎዳና ባለስልጣን በሚል ስያሜ ስለአውራጎዳናዎች ድንጋጌ ማውጣት ስልጣን ተሰጥቶት ራሱን የቻለ መ/ቤት ሆኖ በአዋጅ ቁጥር 115/1943 የተቋቋመው በ 1943 ዓ.ም ነው፡፡የባለስልጣኑ መ/ቤት በተጓዘባቸው አመታት በየወቅቱ ከነበሩት ስርዓቶች የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች እና ትልሞች ጋር በተቆራኘ መልኩ እና እንደ የስርዓቶቹ የአደረጃጀት ፍላጎት የለውጥ ሂደቶችን በማለፍ ደረጃ በደረጃ እድገት እያሳየ መጥቷል፡፡
3. መ/ቤቱ ከተቋቋመበት ከ 1943 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ያሳያቸው የመንገድ አውታር እድገት ሲታይ በ1943 ዓ.ም የአስፋልት መንገድ 3,400 ኪ.ሜ እና የጠጠር መንገድ 3,000 ኪ.ሜ በድምሩ 6,400 ኪ.ሜ የነበረ ሲሆን በ 1965 ዓ.ም እድገቱ ተሻሽሎ የአስፋልት መንገድ 3,360 ኪ.ሜ እና የጠጠር መንገድ 5,800 ኪ.ሜ ሆኖ በድምሩ የመንገድ አውታሩ 9,160 ኪ.ሜ ደርሷል፡፡
4. ከ 1977 ዓ.ም እስከ 1983 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የነበረው የመንገድ አውታር እድገት ሲታይ ያሳየው ለውጥ በ 1977 ዓ.ም 4,042 ኪ.ሜ አስፋልት፣ 8,788 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ እና 3,808 ኪ.ሜ የገጠር መንገድ በድምሩ 16,638 ኪ.ሜ የመንገድ አውታር የነበረ ሲሆን በ 1983 ዓ.ም እድገት በማሳየት 4,109 ኪ.ሜ አስፋልት፣ 9,298 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ እና 5,610 ኪ.ሜ የገጠር መንገድ በድምሩ 19,017 ኪ.ሜ የመንገድ አውታር እድገት ታይቷል፡፡

5. በተለይም ሀገራችን በአዲስ የእድገት አቅጣጫ መመራት ከጀመረችበት ከ 1983 ዓ.ም ወዲህ ለመንገድ ግንባታ እና ለመገናኛ አውታሮች መስፋፋትና መጠናከር የተለየ ትኩረት በመሰጠቱ የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም በመቅረጽ ከ 1989 ዓ.ም ጀምሮ የተግባር እርምጃዎች እንዲወሰዱ ተደርጓል፡፡ በልማት ፕሮግራሙ ትግበራ ሂደት /1989- 2002 ዓ.ም/ የመንገድ አውታሩን የስርጭት አድማስ በማስፋፋት 23,000 ኪ.ሜ የመንገድ ግንባታ በፌዴራል እና በክልል የገጠር መንገዶች አማከኝነት ተሰርቷል፡፡

6. በተጨማሪም የገጠሩን ህዝብ በማሳተፍ ከ 80,000 ኪ.ሜ በለይ አነስተኛ ደረጃ ያላቸው የገጠር መንገዶች ተገንብተዋል፡፡ በ1989 ዓ.ም የመንገድ ዘርፉ ልማት ፕሮግራም ሲጀመር የአስፋልት መንገድ 10,680፣የጠጠር መንገድ 12,162 እና የገጠር መንገድ 10,680 ኪ.ሜ ተሰርተው በድምሩ የመንገድ አውታሩ 26,550 ኪ.ሜ መድረሱ እና በ 2002 ዓ.ም የአስፋልት 7,290፣ጠጠር መንገድ 14,957 እና የገጠር መንገድ 26,755 ኪ.ሜ በድምሩ 49,000 ኪሜ መድረስ የሀገሪቱ የመንገድ አውታር ከ 70 በመቶ በላይ ማደጉን አሳይቷል፡፡

7. የ2003-2007ዓ.ም የመንገድ ዘርፍ ልማት እቅድ መንግሥት ለቀረፀው የአምስት ዓመት እድገት እና ትራስፎርሜሽን እቅድ ስኬታማነት የመንገድ ዘርፉ ከፍተኛ አስተዋፆ እንደሚያበረክት ታምኖበት እየተተገበረ ይገኛል፡፡ የመንገድ ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ዓለማዎቹም፡-
   - አዳዲስ የልማት ቦታዎችን መክፈት፣
   - ከጎረቤት አገሮች ጋር የሚያገናኝ መንገድ ማሻሻል/መገንባት፣
   - አገናኝ መንገዶች መገንባት.
   - ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት ያላቸውን መንገዶች ማሻሻል እና
   - የኮንስትራክሽን ኢንደስትሪውን ጠንካራ እና ተወዳዳሪ ማድረግ ናቸው፡፡

8. በመሆኑም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከመንግስት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት ለመንገድ ግንባታ ሥራው እንቅፋት የሚሆኑ የግለሰብ እና የድርጅት ንብረቶች በፌዴራል መንግሥት አዋጅ ቁጥር 455/1997 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/1999 መሰረት ካሳ ተከፍሎ እንዲነሱ እያደረገ ይገኛል፡፡

9. በአጠቃላይ ከ 2003- 2007 ዓ.ም መርሃ ግብር በፌዴራል 99,431 ኪሜ፣ የወረዳ የመንገዶች ተደራሽነት ፕሮግራም 71,523 ኪ.ሜ፣ እንዲሁም የክልል ገጠር መንገዶች 11,212 ኪ.ሜ ክረምት ከበጋ የሚያስኬዱ መንገዶች ግንባታ የሚከናወን ሲሆን፣ ለዚህም ተግባር 121.7 ቢሊየን ብር ወጪ እንደሚደረግ ሲጠበቅ፣ የገንዘብ ምንጩ 60 ከመቶ ከመንግስት፣ 13

በመቶ ከመንገድ ፈንድ፣ 18 በመቶ ከአበዳሪዎች፣ 3 በመቶ ከእርዳታ ሰጪዎች ሲሆን፣ 6 በመቶ የሚሆነው የገንዘብ ምንጭ ተፈልጎ ከሚገኝ ነው፡፡

**የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዓለማዎች**

10. -መንገዶችን ማልማትና ማስተዳደር

- የመንገድ አውታር በተቀናጀ መልኩ የሚያድግበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር እና
- በመንገድ ሥራ የደረጀ ወጥነትን ማረጋገጥ ናቸው

**ራዕይ**

11. የኢትዮጵያ የመንገድ አውታር በ 2015 ዓ.ም መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ደረጃ በማድረስ ተገልጋዩን የላቀ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

**ተልዕኮ**

12. ደህንነቱ የተጠበቀ የመንገድ አውታርን በጥራት፣ በወቅቱ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ቀጣይነት ባለው መልኩ በማስፋፋት፣ በማሻሻል እና በመንከባከብ በሁሉም አካባቢ የሚኖረውን የኢትዮጵያ ህዝብ የመንገድ ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግና ለሀገሪቱ ሁለንተናዊ እድገት ትርጉም ያለው ድጋፍ መስጠት

**የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት**

13. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተግባርና ኃላፊነት እንደሚከተለው ቀርቧል

1. መንገዶችን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን እና ህጎችን ማመንጨት፣
2. የመንገዶችንአመዳደብ መመሪያ ማውጣት፣ብሄራዊ የመንገድአውታርንናየመንገዶች ደረጃን መመደብ ፣መሰየም እና የመንገዶችን የዲዛይን ደረጃ ማውጣት፣
3. የአገሪቱን የመንገድ አውታር አስመልክቶ ዕቅድ ማውጣት እና ለሚመለከታቸው አካላት ማሰራጨት፣
4. ለመንገድ ሥራ የሚያስፈልጉትን ዲዛይኖችና የፊዚብሊቲ፣የአካባቢና ተያያዥነት ያላቸውን ጥናቶች ማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጁ ማድረግ፣
5. የሥራ እና የአማካሪነት አገልግሎት ውሎችን ማዘጋጀት ወይም እንዲዘጋጁ ማድረግ፣ ውሎችን መዋዋል፣ሥራዎች በየውላቸው መሰረት የሚከናወኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ በበላይነት መቆጣጠር ወይም በሌላ አካል ቁጥጥር እንዲካሄድ ማስደርግ፣

6. የመንገድ ሥራዎች በአገር ውስጥ ወይም በአለም አቀፍ ጨረታ የሚከናወኑበትን አማራጭ መወሰን፡፡

7. መንገዶችን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ማካሄድ ወይም እንዲካሄድ ማስደረግ፣የተገኙ ጠቃሚ ውጤቶችንም በሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣

8. ለመንገድ ሥራዎች እንዲሁም ለመኖሪያ፣ለቢሮ፣ለመሳሪያ ማሳረፊያና ለሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚያስፈልግ መሬትና ድንጋይ ነክ ሀብቶች ያለክፍያ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣

9. በህግ መሰረት ለባለይዞታዎችና ለባለንብረቶች ካሳ በመክፈል ለመንገድ ሥራዎች የሚያስፈልግ መሬት ማስለቀቅ፣

10. በመንገዶች ክልል ውስጥ የተገኙ ህገወጥ ንብረቶችን ማንሳት ወይም ማስነሳት፣

11. የመንገድ ሥራዎች በሚካሄዱበት ወቅት ለአካባቢ ጥበቃ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ማድረግ፣

12. የንብረት ባለቤት መሆን፣ውል መዋዋል፣በስሙ መክሰስ እና መከሰስ ናቸው፡፡

**በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የሪጅናል ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዋና ዋና ተግባራት**

14. የሪጅናል ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዋና ዋና ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

1. ለዲዛይን ሥራና ለሱፐርቪዥን የተመረጡ ድርጅቶች እንዲሁም የመንገድ ግምባታ ፕሮጀክቶችን አሸናፊ የሆኑ ድርጅቶች ዶኩመንቶችና ከባለስልጣን መ/ቤቱ ጋር የውል ስምምነት የተፈራረሙበትን ሰነድ መነሻ በማድረግ የመንገድ ሥራው በተያዘለት ጊዜ እንዲጀመር አስፈላጊውን ሁኔታ ማመቻቸት፣

2. በውሉ መሰረት በተወሰነ መልኩ ለሥራው አስፈላጊ የሆነ የቅድሚያ ክፍያ እንዲፈቀድላቸው አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፣

3. የሱፐርቪዥን ሥራውን ከሚሰራው አማካሪ መሀንድስ በሚቀርበው የክፍያ ምስክር ወረቀት መሰረት ለተሰራው ሥራ የክፍያ ጥያቄው በፋይናንሻል ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት እንዲስተናገድ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፣

4. ቅድሚያ ክፍያዎች በአማካሪ መሀንዲሱ በኩል ከዋናው ክፍያ እየተቀነሱ ስለመጠናቀቃቸው መከታተል፣

5. ተጨማሪ ሥራና ተጨማሪ ጊዜ ለተቋራጩ መስጠት አስፈላጊ ሆኖ በሚጠየቅበት ጊዜ የቀረበው ጥያቄ በሥራ ውሉ መስፈርት መሰረት መቅረቡን በማረጋገጥ ገምግሞ ለበላይ ማኔጅመንት ማቅረብ፣

6. ለማንኛውም የግምባታው ዘርፍ ሥራ በክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት ከሚፈፀመው ከእያንዳንዱ ክፍያ ላይ ለግምባታ ሥራው ጥራት ዋስትና እንዲሆን 5% በመያዣ መልክ ተቀንሶ በአማካሪ መሀንዲሱ ስለመያዙ ማረጋገጥ፣

7. አጠቃላይ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ከአማካሪ መሀንዲሱ በሚቀርብ የክፍያ የምስክር ወረቀት መሰረት በየደረጃው ጊዜያዊናየመጨረሻ ርክክብ የሚፈፀሚበትንና የግዥ መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት የመጨረሻ ክፍያ እንዲፈፀም ለማድረግ አስፈላጊውን ሁሉ ማመቻቸት፡፡

**ከአማካሪ መሀንዲስ የሚጠበቁ ተግባራት**

15. ከአማካሪ መሀንዲስ የሚጠበቁ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል

1. የሚገነቡ መንገዶች ቴክኒካዊ ዝርዝሮችን /Technical Specifications/ እና መሃንዲሳዊ ንድፎችን መሰረት ያደረጉ እንዲሁም ማንኛውንም ጥራትን የሚያስጠብቁ ማሻሻዎችን ጠብቀው መሰራታቸውን ማረጋገጥ፣

2. የግንባታ ቁሶች ደንበኛውን ከመጥቀም አንፃር ወጪ ቆጣቢ መሆናቸውን፣ጥራት ያለው ሥራ መሰራቱን እና ከባቢያዊ የተፈጥሮ ሚዛንን የጠበቀና ማህበራዊ ጠቀሜታው ዘላቂነት ያለው ግንባታ መሰራቱን ማረጋገጥ፣

3. የመንገድ ግንባታው በኮንትራት ስምምነቱ መሰረት በተጠቀሰው በጀት እና ግዜ እንዲሁም በሌሎች ማሻሻያ ስምምነት መሰረቶች መጠናቀቃቸውን ማረጋገጥ ናቸው፡፡

**የተቋራጭ ኃላፊነት**

16. ከተቋራጭ የሚጠበቁ ኃላፊነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. በገባው ውል መሰረት ግዴታዎቹን በአግባቡ መወጣት እና ጥራቱን የተጠበቀ የመንገድ ፕሮጀክት ሥራ ማከናወን እና አጠናቅቆ ማስረከብ

2. በውል መሰረት በገባለት የማጠናቀቅያ ጊዜ ና የኮንትራት ዋጋ ማጠናቀቅ

**የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የፋይናንስ ምንጭ**

17. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የፋይናንስ ምንጭ ለሥራ ማስኬጃ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከመንግስት የሚመደብ በጀት፣ከወርልድባንክ፣ከአፍሪካደቨሎፐመንትባንክ፣ከሰውዲ ፈንድ፣ከኩዌት ፈንድ፣ከቻይና ፈንድ፣ከኦፒክ ፈንድ፣ከጃፓን ግራንት እና ከሌሎችም እርዳታና ብድር ሰጪ ከሆኑ ከውጪ ድርጅቶች ሲሆን በ2004፣በ2005 እና በ2006 በጀት ዓመታት የተገኘው በጀት እና ሥራ ላይ የዋለው በቅደም ተከተሉ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| ዓ.ም | መደበኛ በጀት | | ሥራ ላይ የዋለ | የካፒታል በጀት | | ሥራ ላይ የዋለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የታወጀ | ሥራ ላይ የዋለ | በመቶኛ | የታወጀ | ሥራ ላይ የዋለ | በመቶኛ |
| 2004 | 100,295,127 | 100,295,127 | 100 | 16,723,313,000 | 16,626,616,198 | 99.42 |
| 2005 | 114,435,500 | 114,435,500 | 100 | 17,139,199,000 | 17,109,445,717 | 99.83 |
| 2006 | 153,903,067 | 153,903,067 | 100 | 23,170,000,000 | 23,170,000,000 | 100 |

**የአሰራር ስርዓት መግለጫ/System Description/**

18. የአሰራር ስርዓቱ በሁለት ሁኔታዎች የሚገለፅ ሲሆን እነርሱም በኮንትራት አስተዳደር የመንገድ ግንባታ ሂደት እና የካሳ ክፍያ አፈፃፀም ናቸው፡፡

**ሀ. በኮንትራት አስተዳደር የመንገዶች ግንባታን በተመለከተ**

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከአማካሪ መሀንዲሱ እና ከኮንትራክተሩ ጋር ያለው ግንኙነት በተናጠል በውል መሰረት ቢሆንም፤ በሥራ ሂደት ውስጥ የሥራ ትዕዛዝም ሆነ የተቋራጩ ጥያቄ በአማካሪ መሀንዲሱ በኩል ለሥራ ተቋራጩ የሚደርስ ይሆናል፡፡የባለስልጣን መ/ቤቱን ጥቅም የሚያስጠብቅና ለሥራ አስፈላጊ የሆነ ጉዳይ ሲኖር አማካሪው ፕሮፖዛል/የውሳኔ ሀሳብ/ አቅርቦ በባለስልጣን መ/ቤቱ ከታመነበት ፀድቆ በአማካሪው በኩል ለሥራ ተቋራጩ የሥራ ትዛዝ ይሰጣል፡፡

**ለ. በመንገዶች ግንባታ ሂደት ውስጥ ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ የሚያሳይ የካሳ ክፍያ አፈፃፀም የአሰራር ሥርዓት መግለጫ**

**የመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ኃላፊነትና ተግባራት**

- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች፡- የተነሺ ንብረቶችን ዝርዝር ከማዕከል ወይም በፕሮጀክቱ ከሚገኘው አማካሪ መሀንዲስ ቢሮ በመረከብ ከመንገድ ወሰን ውስጥ የሚነሱ ንብረቶችን በቀረበው ዝርዝር መሰረት በትክክል ለንብረት ገማች ኮሚቴዎች ማሳየት፡፡
- ከማዕከል ወይም በፕሮጀክት ከሚገኘው የአማካሪ መሀንዲስ ቢሮ በሰነድ በሚሰጠው መረጃ መሰረት የመንገዱ ወሰን ከመንገዱ አማካኝ ወደ ግራና ወደቀኝ ምን ያህል ሜትር እንደሚርቅ በትክክልና በጥንቃቄ ለንብረት ገማች ኮሚቴ ማሳየት፤
- ቴክኒካል የሆኑ ችግሮች በሚያጋጥሙ ጊዜ ለፕሮጀክቱ አማካሪ መሀንዲስ ቢሮ በማቅረብ መፍትሄ እንዲሰጥ ማድረግ፤
- የንብረት ገማች ኮሚቴዎች በተገቢው ጊዜ የግምት ሥራውን እንዲያጠናቅቁ ማስተባበርና ሥራው በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን ከሚመለከታቸው የአስተዳደር አመራርና አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የኮሚቴ አባላት ለሥራው ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንዲያከናውኑ ማድረግ፤

- የንብረት ማስነሳት ሥራው በወቅቱ እንዲከናወን ለሚመለከታቸው የወረዳ/የከተማ አስተዳደር የበላይ አመራሮች መ/ቤቱን በመወከል ማሳሰብና ማስተባበር፤
- የካሳ ግምት በሚሰራበት ወቅት የንብረቱ ዓይነት በትክክል መለየቱን፣ልኬት በትክክል መወሰዱን፣ የቤቶች ደረጃ አመዳደብ ፍትሃዊ መሆኑንና ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተል ለባለስልጣን መ/ቤቱ ተገቢውን ሪፖርት ማቅረብ፤

**የካሳ ገማች ኮሚቴ ተግባራት፡-**

- የካሳ ግምት በሚሰራበት ወቅት የንብረት ዓይነት በትክክል መለየት፣
- ልኬት ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የቤቶች አመዳደብን ደረጃ ፍትህዊነት በጥንቃቄ መለየት፣

**የወረዳ/የከተማ አስተዳደር ተግባራት፡-**

- የገማች ኮሚቴ አባለት በግምት ሰነዱ ላይ መፈረማቸውን በማረጋገጥ የወረዳ/የከተማ ዋና አስተዳዳሪ ወይም ተወካይን በፊርማ ማፀደቅ፡፡
- በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ ማህተምና ሰነዱን ያፀደቀው ባለስልጣን ቲተር ማስመታት እና በሸኚ ደብዳቤ ለመንገድ ጥበቃ ወኪል ተሰጥቶ ወደ አስፈፃሚው ባለስልጣን መ/ቤት ማድረስ፡፡

**የባለስልጣኑ መ/ቤት ተግበር**

- የካሳክፍያው በወረዳው/በከተማው አስተዳደር በተጠየቀው መሰረት በኮሜርሻል ኖሚኒስ/በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ በኩል እንዲከፈል ማድረግ ናቸው፡፡

**የኦዲቱ ዓላማ፡-**

19. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በፌዴራል ደረጃ ለሚያሰራቸው መንገዶች ግንባታ የኮንትራት አስተዳደር እና የካሳ ክፍያ አፈፃፀም ተግባሮች ቀልጣፋ፣ግልፅነት እና ተጠያቂነት የተላበሱ ለመሆናቸው እንዲሁም በመንገድ ግንባታው ውል የገቡ አማካሪ መሀንዲሶች እና ተቋራጭ በገቡት ውል መሰረት እየፈፀሙ መሆኑን እና በመንገድ ግንባታ ምክንያት የሚነሱ ንብረቶች የካሳ ክፍያ አፈፃፀም በወጡ አዋጅ፣ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት የተፈፀሙ መሆኑን ማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ

የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የተቋቋመበትን አላማ እንዲያሳካ የሚያግዝ ድጋፍ ለማድረግና በባለስልጣኑ አሰራርም ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

**የኦዲትአካባቢ**

20. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኢዲትአካባቢ(potential audit area) የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንየመንገድግንባታፕሮጀክቶችኮንትራትአስተዳደር ሂደትን ከአማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭጋርበጋባውውልመሰረትተግባራዊማድረጉንእና በመንገድ ግንባታው ምክንያት ለተነሱ ንበረቶችና ለተለቀቁ ቦታዎች በአዋጅና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሰረት የካሳ ክፍያ አፈፃጸምን መገምገም እና ለዚሁ ተግባር የዋለው ግብዓት ያስገኘው ተመጣጣኝ ውጤት(Value for money) ለማረጋገጥ ነው፡፡

**የኦዲቱ ዋና የትኩተር አቅጣጫዋች እና መመዘኛ መስፈርቶች፡-**

21. በተመረጠው የኦዲት አካባቢ (potential audit area) ስር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫና ና ሁለት ንዑስ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡እነርሱም፡-

1. አማካሪም ሆነ ተቋራጭ መሀንዲሶች በገቡት ኮንትራት ውል በተቀመጠው ጊዜ፣የኮንትራት ዋጋ እና ጥራት ደረጃ መሰረት ኢኮኖሚያዊ፣ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ የመንገድ ፕሮጀክት ሥራዎች መስራታቸውን ማረጋገጥ፣

1.1 የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን አማካሪ መሀንዲስም ሆነ ተቋራጭ በገቡት የኮንትራት ውል መሰረት በተቀመጠለት ጊዜ፣ ዋጋ እና ጥራት መሰረት የፕሮጀክት ሥራዎች መከናወናቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረጉን እንዲሁም ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የተደራጀ የመረጃ አያያዝ ስርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣

2. በመንገድ ክልል/በመንገድ ግንባታክልል/ ውስጥ ለገቡት ንብረቶች እንዲሁም እንዲለቀቅ በሚደረግ መሬት እና በመሬቱ ላይ ለሚገኘው ቋሚ ንብረት እና በመሬቱ ላይ ለተደረገው ቋሚ መሻሻል ስለሚከፈል ካሳ የአከፋፈል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣

2.1 በመንገድ ግንባታ ክልል ውስጥ ለገቡ ንብረቶች፣ እንዲለቀቁ ለሚደረጉ መሬቶችና በመሬቶቹ ላይ ለሚገኙ ቋሚ ንብረት የካሳ አከፋፈል ከሚመለከታቸው አካላት ጋር

በመሆን ኢኮኖሚያዊና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ ለመፈፀም የሚያስችል የአሰራር ስርዓት የተዘረጋና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም የሚሉ ናቸው፡፡

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት/የተዘጋጀባቸው ማስረጃዎች/፡-**

22. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎችን እና ሁለትንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን ለመመዘን የሚረዱ 47 የመመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፤የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የ ሆኑት ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንን እንደገና ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 80/1989
- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣንን እንደገና ማቋቋሚያ የሚ/ሮች ሚክር ቤ/ት ደንብ ቁጥር 247/2003
- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የኮንትራት ውል ሰነድ
- የግዥ እና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የግዥ መመሪያ ሰኔ 2002
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ለአማካሪ መሀንዲስ የተዘጋጀ ቢጋር
- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅር
- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ማኔጅመንት ሳሚንታዊ ስብሰባ ቃለጉባኤ መጋቢት 30/2005
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የቦርድ ቃለ ጉባኤ
- ለህዝብ ጥቅም ሲባል የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበትን እና ለንብረት ካሳ የሚከፈልበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 455/1997
- የንብረት ካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የወጣ ደንብ 135/99
- በፌዴራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለሙስና ና ብልሹ አሰራር ክፍተት የሚፈጥሩ ስጋቶችን ለመከላከል የተካሄደ የአሰራር ሥርዓት ማሻሻያ ጥናት ሪፖርት ሚያዝያ 2004
- በመንገድ ክልልውስጥ የገቡ ንብረቶች ከመለየት እስከ ማንሳት /የውስጥ ኦዲት ክዋኔ ኦዲት/

- የ2004፣የ2005 እና የ2006 እስከ የካቲት ወር የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት
- የአምስት የኮንትራት አስተዳደር ሪጅኖች ከአማካሪ መሀንዲሶች እና ከተቋራጭ መሀንዲሶች ጋር ከ2004-2006 ዓ.ም የተፃፃፉቸው የተለያዩ ደብዳቤዎች
- በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ለኢንጂነሪንግ ኦፐሬሽን ደፐዩቲ ዳይሬክተር ጀነራል፣ለ አምስቱ ሪጅናል ኮንትራት ማኔጅመንት ዳሬክሬቶች፣ለመንገድ ጥራት እና ደህንነት ዳይሬክቶሬት ፣ለፕላኒንግ ዳይሬክቶሬት እና ለኢንቫይሮመንት ቡድን መሪዎች በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮች ለቀረበቃለ መጠይቅ ከተሰጠ መልስ
- መልካም ተሞክሮዎችን በማካተት የተዘጋጀ ነው፡በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰዋቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹም ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

**የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ፡-**

**የኦዲቱ ወሰን**

23. የክዋኔ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ 2004 እስከ 2006 በጀት ዓመት ባለው ግዜ ውስጥ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን የመንገዶች ኮንትራት አስተዳደርና የካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ ነው፡፡ የክዋኔ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ሲሆን በ 5 ሪጅን ኮንትራት አስተዳደር ስር በሚካሄዱ በናሙና በተመረጡ 12/አስራ ሁለት/ የመንገድ ፕሮጀክቶች መቀሌ-ስረት መንደር፣ወልቅጤ -አረቅጥ፣ አረቅጥ- ሆሳዕና፣ አለታ ወንዶ-ዳዬ፣ አርባምንጭ-በልታ፣ ሳንጃ- ቀራቀር፣ ጂማ -ቦንጋ፣ ጊዳሜ-ሙጊ፣ ሀረር- ጅጅጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣ ወሪኢ.ርጅ-አደዋ እና ሁምቦ-አርባምንጭ ናቸው፡፡በዝርዝር ኦዲት ወቅት ሳንጃ ቀራቀር እና ሁምቦ አርባምንጭ ፕሮጀክቶች ከመጀመሪያ ተቋራጭ ጋራ ውል በማቋረጥ ከሌላ ተቋራጭ ጋር አዲስ ውል የተዋዋለ በመሆኑ እያንዳንዳቸው በሁለት ተከፍለው የቀድሞውና አዲሱ በመባል ተለይተዋል››

**የኦዲቱ ዘዴ**

24. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን በናሙና በተመረጡ የመንገዶች ፕሮጀክቶችና ከካሳ ክፍያ አፈፃፀም ጋር ተያያዥ የሆኑ እና አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች መከለስ፣በአካል በመገኘት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ጋር ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና መረጃዎችን መተንተንና በማነፃፀር(Analysis) በማካሄድ ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

### የኦዲቱ ግኝቶች

### የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መሰራቱን በተመለከተ

25. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ዲዛይን ሥራ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ ለሥራው የሚያስፈልገው ጊዜና ትኩረት ተሰጥቶት ሊሰራ እንዲሁም የሥራ መጠን ስሌቶችና የቅየሳ ሥራዎች በሚፈለገው እስታንዳርድ መሰረት መሰራታቸው በሚመለከታቸው አካል ግምገማ ተደርጎ ሊፀድቅ ይገባል፡፡

26. በባለሥልጣን መ/ቤቱ በአማካሪ መሀንዲሶች የሚዘጋጁ የመንገድ ግንባታ ዲዛይን ሥራዎች፣ የሥራ መጠን ስሌቶች እና የቅየሳ ሥራዎች ግዜ ተሰጥቶአቸው በሚፈለገው እስታንዳርድ መሰራታቸውን እና በሚመለከተው አካል ተገምግሞ መፅደቁን የሚያሳይ ማስረጃ መኖሩን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 12 ፕሮጀክቶች የመቀሌ ስረት መንደር የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በኮዊ እና ሳባ ኢንጅነሪንግ/COWI and SABA Engineering/ አማካሪ ድርጅት በቅድመ ትግበራ የአዋጭነት፣የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ ግምገማ እና የምህንድስና ዲዛይን ጥናት በእቅድ 16 ወራት በትግበራ ወቅት 20.5 ወራት የወሰደ እና እ.ኤ.አ ጥቅምት 15/2010 መጠናቀቁን የሚያሳይ የአፈፃፀም ሪፖርት ፣ የአርባ ምንጭ በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በአርባ ምንጭ ከምባ- ሳውላ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ውስጥ በመካተት በ ኤም ኤች ኢንጅነሪንግ ፒኤልሲ/MH Engineering Plc/ እ.ኤ.አ ጥቅምት 22/2007 ተጀምሮ ለማጠናቀቅ 14 ወራት የሚያስፈልግ መሆኑን የሚያሳይ እቅድ የቀረበ ሲሆን የቀሪዎቹን ማግኘት እንዳልቻሉ የፕሮኪዩርመንት ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ሲገልፁ፣ እንዲሁም የአዋጭነት ጥናት ማስረጃዎችን ለሁለተኛ ግዜ እንዲያቀርቡ የተጠየቁ የሚመለከታቸው ዳይሬክቶሬቶችም ያላቀረቡ ሲሆን፣ በተጨማሪም የእያንዳንዱን ፕሮጀክት የአዋጭነት የጥናት ግዜ በቢፒአር ጥናት እስታንዳርድ በተቀመጠ የግዜ ልኬት መጠን ለማነፃፀር እንዲቻል ተጠይቆ የቢፒአር ጥናቱን የአዋጭነት የግዜ ልኬት በሚሰራው የመንገድ ርዝመት መጠን/በ 100ኪ.ሜ፣ 200 ኪ.ሜ፣300ኪ.ሜ፣ 400 ኪ.ሜ ወዘተ/ በመከፋፈል

መ/ቤቱ ማቅረብ ያልቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡ በናሙና ተመርጠው በታዩት ፕሮጀክቶች ተገቢው ግምገማ ባለመደረጉ ምክንት የዲዛይን ክለሳዎች ሲደረጉ በእያንዳንዱ ፕሮጀክት ተጨማሪ ሥራዎች እንዲሰራ መደረጉ፡- በወልቂጤ- አረቅጥ 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳበመደረጉ 6 ተጨማሪ ሥራዎች የታዘዙ በመሆኑ ብር 45,056,963.92 ተጨማሪ የተከፈለ መሆኑ በአማካሪ መሀንዲሱ በቀረበ የተጨማሪ ሥራዎች ማስረጃ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣ በአረቅጥ-ሆሳዕና በመንገድ ግንባታ ሂደት ውስጥ 1 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ የተገለፀው 8 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች የታዘዙ በመሆኑ ብር 41906619.86ሚሊዮን ተጨማሪ የተመደበ መሆኑበአማካሪ መሀንዲሱ በቀረበ የተጨማሪ ሥራዎች ማስረጃ ላይ የተገለፀ መሆኑ ፣ በጅማ- ቦንጋ በዲዛይን ወቅት ከመሬቱ አቀማመጥ ጋር ያልተጣጣመ ዲዛይን በመሰራቱ ምክንያት ለተደጋጋሚ ግዜ የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ 12 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዙ ብር 10,707,118.84 የተመደበ መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ በቀረበ ማስረጃ ላይ የተገለፀ መሆኑ፣ በቦንጋ-ሚዛን 1 ግዜ ታህሳስ 2009 እ.ኤ.አ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ 9 ግዜ የዲዛይን ለውጥ መደረጉ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት 9 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዛቸው ብር 4,331,654.76 ወጪ መደረጉ፣ በጊዳሚ-ሙጊ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ ለተጨማሪ ሥራ ወጪ ብር 4,334,654.76 የተመደበ መሆኑ፣ በምዕራብ ሪጅን ዳይሬክቶሬት የተገለፀ መሆኑ፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በተቋራጭ ሲገለፅ በአማካሪ መሀንዲስ ከኪ.ሜ 158+460 -ኪ.ሜ 159+ 600 የዲዛይን ክለሳ እየተደረገ መሆኑንና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ያላፀደቀው በመሆኑ ዲዛይኑ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ተቋራጭ አልፎት እንዲሄድ በመደረጉ ችግር የገጠመው መሆኑ፡እንዲሁም 10 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመታዘዙ ብር 101,116,054.21 ወጪ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡በተመሳሳይ መልኩ በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክቱ በሥራ ሂደት ላይ እያለ3 ግዜ የዲዛይን ክለሳ የተደረገ መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ በሥራ ሂደት ወቅት 6 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት 8ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች በመሰጠቱ ብር 145,395,499.62 ተጨማሪ ወጪ የተደረገ መሆኑ ለመረጋገጥ ተችሏል፡፡እንዲሁም በቀድሞው ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክቱ በዲዛይን ወቅት በነበረበት ወቅት 3 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ በተቋራጭ በዲዛይን ላይ በነበረበት

ወቅት 9 ግዜ መከለሱ የተገለፀ ሲሆን በዚህም ምክንያት ተጨማሪ ሥራዎች 8 ግዜ በመታዘዙ ወጪ የተደረገ ብር 122,361,123.85 የኮንትራት መነሻ ዋጋውን 32.18%፣ አዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክት በግንባታ ላይ እያለ 1 ግዜ ሙሉ በሙሉ የክለሳ ሥራ የተሰራ መሆኑና በቀጣይ ግዜያት 4 ግዜ መጠነኛ ክለሳ መደረጉ የተገለፀ መሆኑ፣ እና ለተጨማሪ ሥራ ብር 4,999,999.25 የተመደበለት መሆኑ ታውቋል፡፡የአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የዲዛይን ክለሳ ተዘጋጅቶ በታህሳስ 02/2010 ወደ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተላከ ሲሆን፣ በግንባታ ላይ እያለ 15 ግዜ ክለሳ የተደረገለት መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ ሲገለፅ፣በተቋራጭ ፕሮጀክቱ በግንባታ ላይ እያለ 30 ግዜ የዲዛይን ክለሳ መደረጉ ተገልጿል፡፡በዚህም ምክንያት 15 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች ቢታዘዙም በመነሻ ኮንትራት ከተገባው የሥራ መጠን መቀነስ ያሳየ በመሆኑ በብር 40,993,684.07 የዋጋ ቅናሽ ያሳየ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡የአለታ ወንዶ-ዳዬ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዋናነት 2 ግዜ የዲዛይን ክለሳ ሲደረግለት 14 ተጨማሪ አነስተኛ የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ ምክንያት ብር 146,537,656.01 የተመደበለት መሆኑ የተገለፀ ሲሆን የሀረር ጅግጅጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 8 ግዜ ተጨማሪ ሥራዎች ታዞለት ብር 109,329,353.80 ወጪ የተደረገለት መሆኑ ከቀረቡ ማስረጃዎች ማወቅ ተችሏል፡፡

27. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት 5ት የየሪጅኑ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ከማዕከላዊ ሪጅን ለወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆስዕና የዲዛይን ክለሳ የተደረገው ሥራው ለተቋራጮቹ ከተሰጠ በኋላ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በግንባታ ወቅት ለሚለዩ ሁኔታዎች እና ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ሲባል መሆኑን እና በዲዛይን ሥራዎች ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የዲዛይን ግዜ ማነስ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ የዲዛይን ሥራ ክለሳው አንድ ግዜ የሚከናወን ሆኖ በግንባታ ወቅት አንዳንድ የዲዛይን ማሻሻያ የሚደረግ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪም ለዲዛይን ማሻሻያ ምክንያቶች የህዝብ ጥያቄ፣ በተፈጥሮ የሚከሰቱ ችግሮች የመሬት መንሸራተት እና በዲዛይን ወቅት ያልታዩ አንዳንድ ክስተቶች ለማስተካከል ሲያጋጥሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም የዲዛይን ሥራዎች፣የሥራ መጠን ስሌቶች እና የቅየሳ ስራዎችን ጥልቅ ጥናት ማካሄድን በተመለከተ ዲዛይኑን የሚያጠናው ድርጅት ጥልቅ የሙከራ ምርምሮችን አካሂዶ ጥናቱን ለማጠናቀቅ የሚሰሩት ሥራዎች ጊዜና ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትሉ

በመሆናቸው እና በዲዛይን ወቅት ከተለያዩ መ/ቤቶች ለዲዛይን ጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ተሟልተው አለመገኘት ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉት ችግሮች በመኖራቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደርና ሳንጃ ቀራቀርን በተመለከተ በኮንትራት ውል መሰረት አማካሪ መሀንዲስ በዝግጅት ወቅት የተሰራውን የዲዛይን ሥራ ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር ሊጣጣም መቻሉን በመገምገም አንድ ግዜ ዲዛይን ክለሳ የሚያከናውን መሆኑን እና ፕሮጀክቱ ወደ ትግበራ ከተገባ በኋላ በተለያዩ ግዜያት እንዳስፈላጊነቱ የኮንትራት ውል በሚፈቅደው መሰረት የዲዛይን ማሻሻያ አነስተኛ ወይም መጠነኛ ለውጦች በፕሮጀክቱ ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የዲዛይን ሥራዎች፣ የሥራ መጠን ስሌቶችና የቅየሳ ሥራዎች በጥልቀት ግዜ ተሰጥቷቸው መሰራት ያለባቸው በመሆኑ የመንገዶች የዲዛይን ሥራ ሲሰራ ያለውን ነባራዊ የመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ ፕሮጀክቱ የሚያልፍባቸው ከተሞች በወቅቱ የሚኖራቸው የእድገት ደረጃ ሁኔታንና ሌሎችን አስፈላጊ ግብዓቶች ግምት ውስጥ በማስገባት እና ፕሮጀክቱ በሚያልፍበት አካባቢ ከሚገኙ ማህበረሰቦችና የመስተዳድር አካላት ጋር አስፈላጊው ውይይትና ምክክር በማካሄድ የዲዛይን ሥራዎቹ እንዲሰሩ የተደረጉ መሆኑ አስረድተዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ ከክልል፣ከዞን እና ከወረዳ መስተዳድር አካላት የዲዛይን ማሻሻያ እንዲደረግ ጥያቄ በማቅረባቸው የታየው ለውጥም የመስተዳድሩን ፍላጎት ከማሟላት አንፃር የመጣ መሆኑን፤ ሆኖም በወሪኢ ሪጅ-አድዋ 10 ግዜ የዲዛይን ክለሳ እንዲሁም በመቀሌ ስረት መንደር 8 ግዜ የተባለው በእያንዳንዱ 3 ግዜ የዲዛይን ለውጥ መደረጉን፣ ከደቡብ ሪጅን በቀድሞውና በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ በአርባ ምንጭ-በልታና አለታ ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክቶች፤ በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ ከአማካሪ መሀንዲሱ ሶስት ግዜ ዲዛይን ክለሳ ተደርጓል ተብሎ የተጠቀሰው ሰፋ ያለ ግዜ ወስደው በዋናነት የተሰሩ የዲዛይን ለውጦች የተስተናገዱበትን ሊሆን እንደሚችል ግምት ያላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡የዲዛይን ክለሳው ካስፈለገባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንደኛው በአርባ ምንጭ ከተማ በህብረተሰብና በአስተዳደሩ ጥያቄ መሰረት የአርባ ምንጭ ከተማ የመንገድ ግንባታው አካል ተደርጎ በ 6 ሌን/ተሽከርካሪዎች ጎን ለጎን መስመር ጠብቀው እንዲያልፉበት የተሰራ የምልክት መስመር ያለው መንገድ/ የተሰራበት ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የአርባ ምንጭ ከተማ የመንገድ ክልል በቀድሞው መስመር መሄዱ የቀድሞው የኩልፎ ድልድይ አስጊ ሁኔታ ውስጥ ከመሆኑ አንፃርና ብዙ ህዝብ ባልሰፈረበት/ከዩኒቨርሲቲ ጀምሮ እስከ ኩልፎ ወንዝ/ ስለሚያልፍ ተለውጦ ህዝብ በሰፈረበት መስመር እንዲሄድ በተወሰነው መሰረት

የተደረገ የዲዛይን ለውጥ እና ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ መንገዱ ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ ይህንን ለመከላከል የተሰሩ ተጨማሪ የፍሳሽ ማስወገጃ እና የመንገድ ዲዛይን ለውጥ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ተቋራጩ እያንዳንዱን የዲዛይን ለውጥ በመቁጠር 9 ግዜ ዲዛይን ክለሳ ተደርጓል ቢልም የተሰጠው ተጨማሪ ሥራ ቁጥር 8 ብቻ መሆኑን፣ በአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ መካከል በዲዛይን ክለሳው ላይ የታየው የአመለካከት ልዩነት የሥራ ተቋራጩ እያንዳንዱን ጥቃቅን ለውጥ የዲዛይን ለውጥ አስመስሎ የማቅረብ ሁኔታ የተስተዋለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡በሌላ መልኩ ከምሥራቅ ሪጅን የሀረር- ጅግጅጋ ፕሮጀክት ዲዛይን በሚሰራበት ወቅት በፕሮጀክቱ አጥቢያ የነበረው የደህንነት ሁኔታ አስተማማኝ ባለመሆኑ የመስክ ጥናቶቹ በሚፈለገው ደረጃ በአካል በመገኘት በጥልቀት እንዳይደረጉ እንቅፋት የነበር በመሆኑ መንገዱ የታቀደለትን አገልግሎት እንዲሰጥ በግንባታ ወቅት በአካል የታዩ በርካታ ችግሮችን ማስተካከል በማስፈለጉ እንዲስተካከል መደረጉን አስረድተዋል፡፡ እንዲሁም ከጅግጅጋ መንገድ ስፋት ጋር በተያያዘ በመጀመሪያው ዲዛይን ወቅት በነበረው ከተማ እስታንዳርድ መሰረት ዲዛይኑ የተሰራ ቢሆንም በክልሉ አስተዳደርና በአካባቢው ኗሪዎች የይስፋልኝ ጥያቄ መሰረት እንዲሰፋ ተደርጎ በመገንባቱ ምክንያት የዲዛይን ማስተካከያ መደረጉ ሲሆን በአማካሪ መሀንዲስ የሚዘጋጁ የመንገድ ግንባታ ዲዛይን ሥራዎች፣የሥራ ስሌቶች እና የቅየሳ ሥራዎች በሚፈለገው እስታንዳርድ ግዜ ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ሥራ እንዳያስከትሉ ያልሆነበት ምክንያት የመንገድ ዲዛይኖች በሚሰሩበት ግዜ በርካታ ሙያዊ ውሳኔዎች የሚያስፈልጋቸው ስለነበር መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከእነዚህም መካከል በተለይም የተፋሰስና የሀይድሮሊክስ ጥናት እና የቅየሳ ሥራዎች ዋናዎቹ ሲሆኑ እንደኛ ባሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሳተላይት ተጠቃሚ ባልሆኑ ታዳጊ አገሮች መረጃዎችን የመተንተንና ለተፈለገው ዓላማ የሚያውል ባለሙያ እጥረት ባለበት ሁኔታ ከተፋሰስ ጥናትና ቅየሳ ሥራ ጋር በተያያዘ ያለው ችግር ቀደም ባሉት ግዜያት በጣም አስቸጋሪ የነበረ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

28. የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች ከላይ የተመለከቱትን መልሶች ቢሰጡም በዋናነት ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት በአዋጭነት/Feasibility/፣በአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ እና በምህንድስና ዲዛይን በቅድመ ጥናት ወቅት ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የሚያስፈልገውን በቂ የጥናት ግዜ በማስቀመጥና ጥናቱ ተፈላጊውን እስታንዳርድ ማሟላቱንና የህብረተሰቡን ፍላጎት ማካተቱን አገናዝቦ ወደ ትግበራ ባለመግባቱ የተፈጠሩ

ችግሮች በመሆናቸው በኦዲቱ የተገነዘብን በመሆኑ በኃላፊዎቹ የተሰጡት መልሶች ለተከሰቱ ችግሮች መሰረታዊ ምክንያቶችን በጥልቀት እና በበቂ ሁኔታ ያካተቱ ሆነው አላገኘነውም፡፡

29. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ የዲዛይን ሥራዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተው እንዲሰሩ  በቅድመ ዲዛይን ጥናት ወቅት የመንገድ ግንባታው የሚሰራበት ቦታ ጂኦሎጅያዊ ጥናት በጥልቀት እንዲካሄድ ባለማድረጉና የማህበረሰቡንና የመስተዳድር አካላትን ሀሳቦች ከግምት ውስጥ በቅድሚያ ባለማስገባቱ፤እንዲሁም በየግዜው ከከተሞች አንጻራዊ እድገት ጋር በመስተዳደር አካላት በሚቀርቡ ጥያቀዎችና በመሬት  አቀማመጥ በሚከሰቱ ችግሮች የዲዛይን ለውጥ መደረጉ  ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ግዜ ተጠናቀው የሚጠበቅባቸውን ውጤት እንዳያስገኙና ለፕሮጀክቶቹ የሚውለው ሀብት ተፈላጊውን ጠቀሜታ/value for money/ እንዳያስገኝ አድርጓል፡፡

## <u>የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የአካባቢ ጥበቃ ፓሊሲን መሰረት አድርገው መከናወናቸውን በተመለከተ</u>

30. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ሥራ ከመጀመሩ በፊት በተቋራጮች የሚቀርብ እቅድ የአካባቢ ጥበቃ እና በባለስልጣን መ/ቤት መመሪያ መሰረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (environmental impact assessment) ተዘጋጅቶ በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተገምግሞ ሊፀድቅይገባል፡፡ ለመንገድ ግንባታ ግብዓትነት የሚውሉ የተፈጥሮ ሀብትን፣ አካባቢንና የማህበረሰቡን ደህንነት በማይጎዳና ወጭ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግበት ይገባል፡፡

31. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖን በተመለከተ ተቋራጮች ያቀረቡአቸውን የአካባቢ ጥበቃ እቅዶች በሥራ ከመተግበራቸው በፊት በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ያስገመገማቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት ዘጠኝ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 9ኙም፡-በወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ- ሆሳዕና፣በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣መቀሌ ስረት መንደር፣ አዲሱ ሳንጃ ቀራቀር፣የቀድሞውና አዲሱ ሁምቦ- አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች እቅዶችን ያላስገመገመ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት አማከሪ መሀንዲስ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

32. በተጨማሪም የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በመንገድ ግንባታ ሂደት ላይ እያሉ የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖን ለመከላከል የባለሥልጣን መ/ቤቱን የአካባቢ ጥበቃ መመሪያ እና የኢትዮጵያ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/95ን ተግባራዊ ከማድረግ አንፃር መመሪያውና አዋጁን በሥራ ሂደት እያመሳከሩ የሚጠቀሙ መሆኑ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ በ 8ቱ :- በወልቂጤ-አረቅጥ፣አረቅጥ-ሆሳዕና፣ በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣ በወሪኢ ሪጅ አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣ በቀድሞውና በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ በልታ መመሪያውንና አዋጁን በሥራ ሂደት እያመሳከሩ የማይጠቀሙ መሆኑ እና መመሪያውም በአማካሪ መሀንዲሱም ሆነ በተቋራጩ እጅ ያልተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

33.እንዲሁም ለመንገድ ግንባታ የሚውል ግብዓት/ማቴሪያል/ የተፈጥሮ ሀብትን፣ የአካባቢ ጥበቃንና የማህበረሰቡን ደህንነት በማይጎዳ መልኩ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- በወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕና በባለሥልጣን መ/ቤቱ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ የወርሃዊ መስክ ክትትል ስለመደረጉ ለሪጅኑ ዳይሬክተር በ 27/02/2007 በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑ ቢገለፅም ክትትል ማድረጋቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ ታውቋል፡፡ በጅማ-ቦንጋ፣ቦንጋ-ሚዛንና ጊዳሚ-ሙጊ ፕሮጀክቶች በወርሃዊ፣ሩብ ዓመትና ዓመታዊ ሪፖርት እንዲሁም በመስክ ምልከታ ክትትል አማካሪ መሀንዲሱ በቀጠረው የውጪ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ ባለሙያ/ኢንቫሮሜንታሊስት/ ከሐምሌ 3-13/2013 ዓ.ም በተደረገ ግምገማ የማሻሻያ ሀሳብ መሰጠቱ ከሐምሌ 2013 እ.ኤ.አ ለምዕራብ ሪጅን ከቀረበ ሪፖርት መረዳት ቢቻልም በመስክ ኦዲት በተካሄደ ግምገማ በጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን ተቋራጮች ግብዓት ያወጡባቸው ቦታዎች ያልተደፈኑ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኢንቫሮመንትና ሶሻል ደህንነት ቲም የመስክ ክትትል ስለማድረጉ በኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ተጠይቆ ማስረጃው ሊቀርብ አልቻለም፡፡ በአርባ ምንጭ በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ግብዓት የተጠቀመባቸውን ጉድጓዶች እንዲያስተካክል በአማካሪ መሀንዲስ ማሳሰቢያ ተሰጥቶት ለመፈፀም ተነሳሽነቱ ዝቅተኛ

መሆኑ መገለፁና በኢንቫሮመንትና ሶሻል ደህንነት ቲም የመስክ ክትትል ስለመደረጉ በኦዲት ቡድኑ ማስረጃ ተጠይቆ ማስረጃ አለመገኘቱ ታውቋል፡፡

34. እንዲሁም ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታው የሚያስፈልጉ ግብዓቶች/ማቴሪያሎች/ ተቆፍረው የወጡበት ጉድጓዶች የውሃ ማቆሪያና የወባ ትንኝ መራቢያ እንዳይሆኑ በገባው ውል መሰረት መድፈን /መሙላት/ ያለበት መሆኑን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በወልቂጤ-አረቅጥ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ለግብዓት መጠቀሚያነት የተገለገለባቸውን ቦታዎች ባለመድፈኑ በእምድብር ከተማ ገዳም ሰፈር ቀበሌ 01 እና በሌሎችም የወባ ትንኝ መራቢያ በመሆናቸው ህብረተሰቡ በወባ በሽታ እየተጠቃ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በጅማ-ቦንጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክትለግንባታ ግብዓት ከወጡባቸው ቦታዎች ቦሮው የቦታ መለያ ቁጥር 4,600 ከህዝብ መኖሪያ ቤቶች አካባቢ መራቅ ሲገባቸው ከመኖሪያ ቤቶች ጀርባ የተቆፈረ በመሆኑ፣እንዲሁም የቦታ መለያ ቁጥራቸው 5400 እና 4100 ባለመሞላታቸው ውሃ አቁረው የያዙ መሆናቸው፤ በተጨማሪም ድንጋይ የወጣባቸው የቦታ መለያ ቁጥራቸው 6,900 እና 58,800 ኳሪዎች ውሃ ያቆሩ መሆኑ፣ በቦንጋ ሚዛን የቦታ መለያ ቁጥራቸው 161+200 ኳሪ እና ቦሮው 156+200 ውሃ አቁረው የያዙ ሲሆን በጨና ከተማ በቤተክርስቲያን አካባቢ ግብዓት የወጣበት ጉድጓድ ባለመደፈኑ የህብረተሰቡ ከብቶች እየወደቁ መሞታቸውና በታቆረ ውሃ ምክንያት ህብረተሰቡ በወባ በሽታ እየተጠቃ መሆኑ ታውቋል፡፡

35. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የየሪጅኑ ዳይሬክቶሬትና የኢንቫሮመንትና ሶሻል ደህንነት ቡድን ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕንን በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግስት አካባቢ ጥበቃ አዋጅን ከፕሮጀክቱ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ማግኘት የሚቻል መሆኑንና ፕሮጀክቱጋ ማግኘት ያልተቻለበት ምክንያት ይህ ባለሙያ መደበኛ ሰራተኛ ባለመሆኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም የአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክቶቹን የመገምገም ስልጣን ለትራንስፖርት ሚኒስቴር በውክልና በመስጠቱ በዚህም መሰረት የባለሥልጣኑ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች እና ለእነዚህ ፕሮጀክቶች የተቀጠሩ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች በየግዜው የመስክ ጉብኝት በማድረግ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር በተያያዘ ሙያዊ ምልከታቸውንና አስተያየት እየሰጡ አተገባበሩን በቅርበት እየተከታተሉ መሆኑን፤

36. ለመንገድ ግንባታው የሚውሉ ግብዓቶች/ማቴሪያል/ የተፈጥሮ ሀብትን፣የአካባቢ ጥበቃንና የማህበረሰቡን ደህንነት በማይጎዳ መልኩ ሥራ ላይ መዋላቸውን በተመለከተ የመስክ ክትትል በባለሥልጣኑ መ/ቤትና ለፕሮጀክቶቹ በተቀጠሩ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያዎች መከናወኑን ገልፀዋል፡ እንዲሁም በእምድብር ከተማና በሌሎችም ተቋራጭ ለግብዓት የቆፈራቸው ጉድጓዶች ባለመደፈናቸው በህብረተሰቡ ላይ የወባ በሽታ ማስከተሉን በተመለከተ የደረሰ ሪፖርት ባይኖርም ሁኔታው ሊከሰት የሚችለው በተቋራጩ ድክመት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከምዕራብ ሪጅን በጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክቶች ተቋራጭ የባለሥልጣን መ/ቤቱ መመሪያ የአካባቢ ጥበቃ አዋጅን ተመርኩዞ የተዘጋጀ በመሆኑ፤ የአካባቢ ተፅዕኖን ለመከላከል የተዘጋጀውን መመሪያ ተመርኩዞ የራሱን እቅድ አቅርቦ በአማካሪ መሀንዲስ በማፀደቅ እየተገበረ መገኘቱን፤ እንዲሁም ለግንባታ የዋሉ ግብዓቶች የወጡባቸው ጉድጓዶች የማህበረሰቡን ደህንነት እንዳይጎዱ ከመድፈን አኳያ በጅማ-ቦንጋ ተቋራጩ ጉድጓዶችን በመድፈን ላይ የሚገኝ መሆኑን እና በመጨረሻ የርክክብ ወቅት ግዴታውን መወጣቱ የሚረጋገጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

37. በተጨማሪም ቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ ተቋራጩ በግንባታ ላይ ያለ በመሆኑ አብዛኛዎቹን እየተጠቀመ የሚገኝ መሆኑን፣ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣መቀሌ ስረት መንደር እና /የቀድሞውና አዲሱ/ ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክቶች የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖን ከመከላከል አንፃር በሥራ ተቋራጩ የቀረበውን እቅድ በአዋጅ ቁጥር 295/95 አንቀጽ 6 ተ.ቁ 5 በገባው ውል ውስጥ በተገለፀው መሰረት አማካሪ መሀንዲሱ በቀን ተቀን የሥራ ሂደት ውስጥ እንደ ግብዓት ለክትትል እየተጠቀመበት መገኘቱን እና የባለሥልጣኑ መ/ቤት ፕሮጀክት መሀንዲስ በመስክ በመገኘት ክትትል ማድረጉን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም ፕሮጀክቶቹ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን መገምገማቸውን በተመለከተ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የአካባቢ ጥበቃ ተፅኖን በተመለከተ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር ውክልና በመስጠቱ ከትራንስፖርት ሚኒስቴር በቁጥር 604/39 ሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም የአካባቢ ጥበቃ ሰነዶችን መርምሮ የማረጋገጥና የማፅደቅ ኃላፊነት መሰጠቱን ቢያሳውቅም በዚህ መሰረትፕሮጀክቶቹ እንዳልተገመገሙ ገልፀዋል፡፡ሆኖም ግን በዲዛይን ወቅት ዲዛይኑን በሚሰራው ድርጅት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቱ በአካባቢው ሊያመጣ የሚችለው ተፅዕኖ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ባለሙያዎች አስፈላጊው ግምገማ ተካሂዶ እየተተገበረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ከደቡብ ሪጅን በመስክ በታዩት በቀድሞውና በአዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ-ብልታ ፕሮጀክቶች የባለሥልጣኑ መ/ቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ መመሪያና የኢትዮጵያ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ የሥራ ተቋራጩ

የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ እቅድ ሲያዘጋጅ በእቅድ ውስጥ የተካተቱ በመሆኑና አማካሪው ድርጅት የተቋራጩን እቅድ ሲገመግም የተጠቀመባቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም ፕሮጀክቶቹ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ያልተገመገሙበት ምክንያት ኃላፊነትን በውክልና የትራንስፖርት ሚኒስቴር በመውሰዱና በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል በተመደቡ ባለሙያዎች በመገምገሙ ሲሆን በአርባ ምንጭ-ብልታ ፕሮጀክት ተቋራጩ ግብዓት የተጠቀመባቸውን ቦታዎች ለመድፈን ተነሳሽነት ያላሳየው በአካባቢው ካለው ውስን የመሬት ሀብት አንፃር የቁፋሮ ማቴሪያሎችን በተፈለገው ሁኔታ መድፋት የሚቻልበት ቦታ በበቂ ሁኔታ ባለመገኘቱመሆኑን ገልፀዋል፡፡በተጨማሪም በፕሮጀክቱ የተከሰተው ሰፊ የመሬት መንሸራተት ከፍተኛ የሚነሳ አፈር ማንሳት በማስፈለጉ መሆኑን ሲገልፁ፤የባለሥልጣኑ መ/ቤት የኢንቫሮመንትና የሶሻል ደህንነት ቡድን በወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፤በጅማ-ቦንጋና በቦንጋ-ሚዛን አራት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን የመስክ ክትትልና ግምገማ ማከናወኑን ገልፀዋል፡፡ቀደም ባለው ግዜ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የሚገመገሙበት አሰራር መኖሩን ሆኖም በሚያዚያ 10 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ከመንገድ ግንባታ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች እንዳስፈላጊነቱ የአካባቢ ጥበቃ ባለሙያ ድጋፍ በመጠየቅ እንዲገመግም እና የይሁንታ ፍቃድ እንዲሰጥ መወከሉን ነገርግን የትራንስፖርት ሚኒስቴር በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ባለሙያ ያልተደራጀ በመሆኑ ሪፖርቶችን መገምገም ያልጀመረ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

38. **የባለሥልጣኑ መ/ቤት** የየሪጅኑ ዳይሬክቶሬትኃላፊዎች ከላይ የተዘረዘሩትን መልሶች ያቀረቡ ቢሆንም በመስክ ኦዲት በተደረገ ምልከታና ለአማካሪ መሀንዲስና ለተቋራጭ በቀረቡ ጥያቄዎች በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ መመሪያ እና የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/1995 በእጃቸው የሌለ መሆኑን በሰጡት መልስ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ፕሮጀክቶችን በአካባቢ ጥበቃ አስገምግሞ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ መተግበርንም በተመለከተ ይሄን የሚያሳይ ማስረጃ ያልተገኘ ሲሆን ይህም ከላይ በባለስልጣኑ መ/ቤት የኢንቫሮመንትና የሶሻል ደህንነት ቡድን የትራንስፖርት ሚኒስቴር በአካባቢ ጥበቃ ዘርፍ ባለሙያ ያልተደራጀ በመሆኑ ሪፖርቶችን መገምገም ያልጀመረ መሆኑን መግለፁ የሚያጠናክር መልስ የተሰጠ መሆኑ፤

እንዲሁም ተቋራጮች ለግንባታ የተጠቀሙባቸው ግብዓቶች ተቆፍረው የወጡባቸው ቦታዎች በኦዲቱ በመስክ ግምገማ በተካሄደበት ወቅት ትኩረት የተሰጣቸው ቦታዎች ፕሮጀክቶቹ መጠቀም ያቆሙባቸው ቦታዎችን እንጂ በሥራ ላይ ያሉትን ባለመሆኑ በስራ ኃላፊዎች

የተሰጡት መልሶች በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፉ መሆናቸው በኦዲት ቡድኑ አግባብነት የሌላቸው መሆኑ ታምኖበታል፡

39. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ወደ ትግበራ ከመግባታቸው በፊት በተቋራጭ የተዘጋጁ የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ እቅዶችን በሚመለከተው አካል አለማስገምገሙ ደንብን አለመከተልን የሚያሳይ ሲሆን ባለመገምገሙ መሻሻል የሚገባቸው ሀሳቦች እንዳይካተቱ የሚያደርግ ሲሆን፣ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጁ የአካባቢ ተፅኖ ጥበቃ መመሪያ እና የኢትዮጵያ መንግስት የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ እጅ አኑሮ እያመሳከሩ እንዲሰሩ አለመደረጉ አዋጅና መመሪያን በመከተል ውጤታማ ሥራ እንዳይሰራ ያደርጋል፤እንዲሁም ተቋራጮች ለግብዓት የቆፈሩዋቸውን ቦታዎች ትኩረት ሰጥተው እንዲደፍኑ አለመደረጉ ጉድጓዶቹ የትንኝ መራቢያ በመሆን ህብረተሰቡ በወባ በሽታ እንዲጠቃ እና ለሰው እና ለእንስሳት አደጋ እንዲፈጥሩ ምክንያት ሆኗል፡፡





በጅማ-ቦንጋ ግብዓት የወጣበት ጉድጓድ የቦታ ጉድጓድ የቦታ መለያ.ቁ 4600 (ቦሮው)

በቦንጋ-ሚዛን ግብዓት የወጣበት ጉድጓድ መለያ.ቁ 161+200 (ኳሪና ቦሮው)

**ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ የሚያስፈልጉትን ግብዓቶች እናመሳሪያዎች ማቅረቡና በብልሽት ወቅትም በአፋጣኝ አስጠግኖ ሥራ ላይ ማዋሉን በተመለከተ**

40. ለመንገድ ግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣ የላቦራቶሪ እቃዎች እና የሰው ሃይል በሥራ አቅድ ፕሮግራም መሰረት መቅረባቸውና የግንባታ መሳሪያዎች እና ማሽኔሪዎች በሚበላሹበት ወቅትም በአፋጣኝ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

41. ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎችና የላቦራቶሪ እቃዎች እንዲሁም የሰው ሃይል በሥራ አቅድ ፕሮግራም መሰረት መቅረባቸውን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 3ቱ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

- በወልቂጤ-አረቅጥ የግንባታ ግብዓቶች በአቅራቢያ ባለመገኘታቸው በሥራው ላይ ግዜ የተጓተተ መሆኑ ለአማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፣
- በአረቅጥ-ሆሳዕና የግንባታ ግብዓቶች በአቅራቢያ ያልተገኘ መሆኑ እና ለሥራው ወሳኝ የሆኑ ሰዎች በየግዜው የሚለዋወጡ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ለአማካሪ መሀንዲስ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፤ እንዲሁም በላቦራቶሪ ለኮንክሪት የሚያገለግል 70mm distance piece for concrete compression machine እና Water Testing Equipment በተቋራጩ ተጠይቀው ባለመቅረባቸው በሥራ ላይ ተፅዕኖ ያሳደሩ መሆኑ፣በጅማ-ቦንጋ ለአፈፃፀም የማይመች/የሰው ሃይል፣ የግንባታ መሳሪያዎች አቅርቦት/ እቅድ በተቋራጭ መቅረብ፣የነዳጅ አቅርቦት ችግር፣ የክሬሸር ፕላንት በየግዜው ሥራ ማቋረጥ፣የቁጥጥር ሥራ የሚሰሩ ሰራተኞች አሲስታንት ማቴሪያል ኢንጅነርና ስትራክቸራል ኢንጅነር እጥረት መኖሩ ለአማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ- መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፣
- በቦንጋ-ሚዛን መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የግንባታ ሂደቱን ለመምራት የማኔጅመንት ችግርና የበጀት ችግር ያጋጠመ መሆኑ፣በወሪኢ ሪጅ-አድዋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በበጀት እጥረት ምክንያት የግንባታ ማሽነሪዎች አለመሟላቱ፤ እንዲሁም የሰራተኛ ደሞዝ በወቅቱ የማይከፈል በመሆኑ የሰው ሃይል ከእቅድ በታች የቀረበ መሆኑ ለአማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፣

- በመቀሌ ስረት መንደር የላቦራቶሪ እቃዎችን በተመለከተ አማካሪ መሀንዲስ ለተቋራጭ በ 03 ኦገስት 2011 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቆ በ 02/11/2013 ከሁለት ዓመት መዘግየት በኋላ የተረከበ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር ለግንባታው የሚያስፈልጉ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣የላቦራቶሪ እቃዎችና የሰው ሃይል በእቅድ መሰረት ያልቀረቡ መሆኑ ለአማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፣ እንዲሁም በቀድሞ ሳንጃ ቀረቀቀር ፕሮጀክት ከወርሃዊ ሪፖርት ቁጥር 29 ኖቬምበር በተገኘው መሰረት ተቋራጩ 25 የግንባታ ማሽነሪዎችን ሥራ ላይ አለማዋሉ፣
- በቀድሞው ሁምቦ አርባምንጭ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች እጥረት፣ የግንባታ መሳሪያዎች በቂ ሆኖ አለመቅረብ፣ የግንባታ ማሽኖች በሚበላሹበት ወቅት በአፋጣኝ ጥገና አለማድረግ እና ፕሮጀክቱ በተጀመረበት ወቅት የላቦራቶሪ በአፋጣኝ አለመደራጀት ዋና ችግሮች መሆናቸው ለአማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት የሰው ሃይል እጥረት፣በፕሮጀክቱ መጀመሪያ አካባቢ ለስድስት ወራት የላቦራቶሪ ዕቃዎች አለመሟላት እና አማካሪ መሀንዲስ በ 02/09/ 2013 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቆ በ 07/08/ 2014 የተረከበ መሆኑ፣ በአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት የአስፋልት ጠጠር ማምረቻ በቅርብ ባለመገኘቱ በፕሮጀክቱ ላይ የግዜ ጫና የፈጠረ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ ለአማካሪ መሀንዲስ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ታውቋል፡፡

42. በተጨማሪም ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ሥራ በግዥ፣በኪራይ ወይም በራሱ ያቀረባቸው መሳሪያዎች በግንባታ ሥራው ወቅት በተሟላ ሁኔታ ላይ የነበሩ ስለመሆናቸውና በተበላሹበት ወቅት በአፋጣኝ ተጠግነው ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ በኦዲቱ ወቅት የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- በአረቅጥ ሆሳዕና ከሰኔ 2014 የግንባታ መሳሪያዎች በተገኘ ሪፖርት አንድ CP-94 HAMM Compactor Roll H1690817 ለ 15 ቀናት ሥራ ያልሰራ ሲሆን ሌሎች ዶዘር፣ ሎደር፣ ካተር ፒላር ሞተር ግሬደር፣ ሚክሰር እና ዳምፕ ትራክ ብዛታቸው 9 የሚሆኑ ለ 30 ቀናት ሥራ ያልሰሩ መሆኑ/ ለማሳያ Komatsu Wheel Dozer Serial No. KMTWDOO2T1050029፣LD-45 KAWASAKI Wheel Loader Cater Pilar Motor

Grader Serial No. 14UASE00379፣ Concrete Mixer T CM-043 IVECO እና DT ASTRA DUMP TRUCK ET- 0301- 59953/፣

- በጅማ-ቦንጋ የክሬሸር ፕላንትና የመንገድ አስተካካይ ማሽኖች በየግዜው ሥራ ማቋረጥ፣ በቦንጋ- ሚዛን ፕሮጀክት ለመንገድ ግንባታ ከሚውሉ ከባድ ተሽከርካሪዎች 34ቱ ለጥገና በመቆማቸው አንድ ዓመትና ከአንድ ዓመት በላይ ሥራ ላይ ያልዋሉ ሲሆን በተጨማሪ 16 ከጥቅም ውጭ ሆነው መገኘታቸው፡፡
- በመቀሌ ስረት መንደር DHL DRESTA የሰሌዳ ቁጥር /DZ 0107/ በመለዋወጫ ምክንያት ለሁለት ወር የቆሙ መሆኑ፣ ግሬደር CAT ሰሌዳ ቁጥር 135H ሥራ ካቋረጠ አንድ ዓመት እንዲሁም LOADER LIUNG GONG ሥራ ካቆመ 2 ዓመት መሆኑ ታውቋል፡፡

43. ስለሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ የየ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን የግንባታ ግብዓት አለመኖር ተፈጥሮአዊ ስለሆነ ምንም ማለት የማይችሉ መሆኑን፣ የባለሙያዎች በየግዜው መለዋወጥ የባለሥልጣኑን መ/ቤት እየተፈታተኑ ከሚገኙ ሀገራዊ ችግሮች መካከል የሚገኝ ሲሆን ለመቀነስ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የተለያየ ቁጥጥር ስርዓት እየተገበረ መገኘቱን፣ የቤተ ሙከራ እቃዎችን በተመለከተ Machine Water Testing Equipment የፕሮጀክቱ እስፔስፊኬሽን በሚያዘው መሰረት የቀረበ ቢሆንም የጎደለው መጠቀሚያ ማንዋል ስለሆነ በዚህ የተፈጠረ ችፍር አለመኖሩ፤ ነገርግን 70mm distance piece for Concrete Compression በሚል የተጠቀሰው መሳሪያ በፕሮጀክቱ እስታንዳርድ ቴክኒካል እስፔስፊኬሽን ላይ አለመቀመጡን፤ እንዲሀም የግንባታ መሳሪያዎች እና ማሽነሪዎች በሚበላሹበት ወቅት አፋጣኝ ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ መግባት ያለባቸው ስለመሆኑ ባለሥልጣኑ የሥራ ተቋራጩን የግንባታ መሳሪያዎች ያሉበትን ሁኔታ በየወሩ በአማካሪ መሀንዲሱ በሚቀርበው ሪፖርትና በባለሥልጣኑ መ/ቤት ፕሮጀክት መሀንዲስ በኩል በሚደረገው ወርሃዊ የመስክ ጉብኝት አማካኝነት ቁጥጥርና ክትትል በመደረጉ እስካሁን ባለው ሁኔታ ፕሮጀክቱ ሥራ ያስተጓጎለበት ሁኔታ አለመኖሩ፣

- በምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋና በቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ በጅማ-ቦንጋ የግንባታ እቅድ ማቅረብ ኃላፊነት የተቋራጩ ሲሆን በአማካሪ መሀንዲስ ፀድቆ ሥራ ላይ ሲውል መቆየቱ፤ ሆኖም በአቀረበው እቅድ ውስጥ የተቋራጩ የውስጥ ችግር በመንፀባረቁ በአማካሪ መሀንዲስና በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ችግሩ ተቀርፎ ባቀረበው የሥራ

እቅድ ማከናወን እንዳለበት ማስጠንቀቂያ በውሉ መሰረት እንዲደርሰው የተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡በቂነዳጅና ለግንባታ የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች በታቀደው መሰረት ለማቅረብና ተገቢ የሆነ ወቅታዊ ጥገና የማድረግ ችግሮች ያሉበት መሆኑን እንዲቀርፍ በተለያዩ ውይይቶችና ደብዳቤዎች የተገለፀ ቢሆንም ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በተለያዩ ፕሮጀክቱ ቦታዎች በመከሰቱ የመሬት መሰንጠቅና መደርመስ እና በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች አለመነሳት ችግሮች እንደ ነበሩ ገልፀዋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የሥራ ተቋራጩ የውስጥ ችግርና ከሚያገኘው ገቢ ፕሮጀክቱን በአግባቡ ማስተዳደር ያለመቻል ችግር ስለነበረበት ይህን ለማስተካከል በተቆጣጣሪ መሀንዲሱና በባለሥልጣን መ/ቤቱ በኩል በተደጋጋሚ ማሳሰቢያ የተሰጠው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- በመቀሌ ስረት መንደር የለቦራቶሪ እቃዎች ሊዘገይ የቻለበት ምክንያት በመጀመሪያ ተቋራጩ /መከላከያ/ የመንግስት የልማት ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የመንግስት ግዥ ተከትሎ የሚሰራ መሆኑን በምክንያትነት የገለፀበት ሁኔታ እንደ ነበረ ገልፀዋል፡፡በሁለተኛነት ጨረታውን ያሸነፈው ድርጅት አስገባለሁ ባለው የግዜ ገደብ ውስጥ በተለያየ ምክንያት ማቅረብ ባለመቻሉ እንዲሁም በመጨረሻ እቃው ከገባ በኋላም በደረጃዎች መዳቢ በኩልም ካሊብሬት አድርጎ በወቅቱ ማስረከብ ባለመቻሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡፣ማሽኖችን በተመለከተ ተቋራጩ የተሟላ ጋራዥ ባለማደራጀቱና አስፈላጊውን መለዋወጫ ማቅረብ ባለመቻሉ በተደጋጋሚ በሰጠው ምክንያቶች መለዋወጫዎቹን አለማግኘቱን በመግለፁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- አዲሱና የቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክትን በተመለከተ በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር የመስክ ኦዲቱ በተካሄደበት ወቅት የዝግጅት ሥራዎች የሚሰሩበት ግዜ በመሆኑ ሲሆን በአሁኑ ግዜ ግን አብዛኛዎቹ የፕሮጀክቱ የግንባታ መሳሪያዎች የቀረቡ መሆኑንና በቀሪዎቹ ላይ መመሪያ ተላልፎ የቅርብ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም በቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክት በተደጋጋሚ በኦዲቱ የተገለፁትን መሳሪያዎች እንዲያሟላ ቢጠየቅም፣ አፈፃፀሙ ላይ የቅርብ ክትትል በማድረግ ችግሩን እንዲፈታ ለማድረግ ቢሞከርም መሻሻል ባለመቻሉ እና በውሉ መሰረት መሄድ ባለመቻሉ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ውሉን መሰረት በማድረግ ተገቢውን እርምጃ መውሰዱን ገልፀዋል፡፡
- በደቡብ ሪጅን የቀድሞውና አዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ- በልታ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ መንገድ ግንባታ የሰው ሃይል እጥረት ከዚህ ቀደም ያጋጠመ ቢሆንም በአሁኑ ሁኔታ ችግሩ የተቀረፈ መሆኑን

ገልፀዋል፡፡የግንባታ መሳሪያዎች በአፋጣኝ ጥገና ለማድረግ አስፈላጊ መለዋወጫዎችን አለማቅረብ እና ጥገና አለማድረግ መንስኤዎች የገንዘብ አቅም ቢሆንም ፕሮጀክቱ ባልታሰበ የጎርፍ አደጋ በመጎዳቱ ተቋራጩ ከፕሮጀክቱ በቂ ገንዘብ ማመንጨት ባለመቻሉ በመሆኑ ይህም በጥገናው ላይ የጎላ ተፅዕኖ ማሳረፉን ገልፀዋል፡፡በአዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ የላቦራቶሪ እቃዎች ከውጭ ለማስገባት ግዜ የወሰደ በመሆኑ ፤ እንዲሁም በአርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክት ለአስፋልት ጠጠር ማምረቻ ኳሪ በቅርብ ርቀት ማግኘት ያልተቻለው በአካባቢው የሚፈለገውን መስፈርት የሚያሟላ ኳሪ ሊገኝ ባለመቻሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

44. ሆኖም ከማዕከላዊ ሪጅን በተሰጠ መልስ ግብዓት በአቅራቢያ አለመኖርን በተመለከተ ምንም ማለት የማይችሉ መሆኑ ቢገለፅም ፣ እንዲሁም የላቦራቶሪ እቃዎችን በተመለከተ Machine for Water Testing የጎደለው መጠቀሚያ ማንዋል በመሆኑ ለሥራው ችግር አለመፍጠሩን ፣ 70mm distance piece for Concrete Compression እስታንዳደርድ እስፔስፊኬሽን ውስጥ የሌለ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም በመስክ ኦዲቱ በኦዲት ቡድኑ በተደረሰበት ግንዛቤ ተቋራጩ ከሩቅ ቦታ ግብዓት በማምጣቱ በሥራው ግዜና በገንዘብ በኩል ለነዳጅ ከአቅም በላይ ወጪ እያደረገ የሚገኝ መሆኑን፤እንዲሁም የላቦራቶሪ እቃዎችን በተመለከተ ችግሩ መኖሩ በአማካሪ መሀንዲሱ የላቦራቶሪ ባለሙያዎች የተገለፀ በመሆኑ በስራ ኃላፊዎች የተሰጡት መልሶች በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፉና ተገቢ ሆነው አልተገኙም፡፡

45. ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣የላቦራቶሪ እቃዎችና የሰው ሃይል በፕሮጀክቶች የሥራ ፕሮግራም በታቀደው እቅድ መሰረት አለመቅረብና በግንባታ ሂደት የሚበላሹ የግንባታ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች በአፋጣኝ ተጠግነው ወደ ሥራ አለመግባት በፕሮጀክቶቹ ላይ የግዜና የወጪ ጫና በመፍጠር የማጠናቀቂያ ግዜ እንዲራዘም አድርጓል፡፡

## <u>ለመንገድ ግንባታ የሚውሉ ግብዓቶች የሚደረግ የላቦራቶሪ ናሙና ፍተሻን በተመለከተ</u>

46. ለመንገድ ግንባታ የሚውሉ አፈርና ጥሬ እቃ ከቴክኒካልና እስፔስፊኬሽን ጋር አብረው የሚሄዱ ስለመሆናቸው የናሙና ፍተሻ በምንጫቸውና በላቦራቶሪ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

47. በኮንትራት ውል የመመዘኛ መስፈርት ክፍል 1000 ላይ በተገለፀው መሰረትበመንገድ ግንባታ ወቅት አማካሪ መሀንዲሱና ተቋራጩ የየራሳቸው የግብዓት ናሙና መፈተሻ ማሟላታቸው ኦዲት ሲደረግ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 7ቱ ፡- ወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ- ሆሳዕና፣ጅማ-ቦንጋ፣ ወሪኢ. ሪጅ-አድዋ፣መቀሌ ስረት መንደር፣በቀድሞውና በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ እና አርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክቶች ለግብዓት ናሙና ፍተሻ አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በአንድ ላቦራቶሪ በጋራ የሚጠቀሙ መሆኑ በመስክ ጉብኝት ታውቋል፡፡በቦንጋ-ሚዛን አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ የየግላቸው ላቦራቶሪ ያላቸው መሆኑ የተገለፀ ሲሆን፤በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቅድመ ክፍያ ባለመልቀቁ ምክንያት ተቋራጩ አማካሪውን አለማደራጀቱ በኦዲት ቡድኑ ለቀረቡ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስና በፕሮጀክቶቹ በተካሄደ ጉብኝት ለማወቅ ተችሏል፡፡

48.ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን በወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕና አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ የተለያየ ቤተ-ሙከራ ያላቸው ሲሆን ነገርግን እንደ አስፈላጊነቱ እንደሥራው ባህሪ በጋራ የሚያከናውኗቸው የግብዓት ናሙና ምርመራ መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

- ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋን በተመለከተ የኦዲት የመስክ ጉብኝት በተደረገበት ወቅት ፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ላይ የደረሰ በመሆኑ አማካሪ መሀንዲሱና ተቋራጭ አንዳንድ የማስተካከያ ሥራዎች ለመሥራት የጋራ ፍተሻ ሲያደርጉ ለማየት ተችሏል፡፡ በሰሜን ሪጅን ወሪኢ. ሪጅ-አድዋ፣መቀሌ ስረት መንደር እና አዲሱ ሳንጃ ቀራቀርን በተመለከተ፤ መቀሌ ስረት መንደርና ወሪኢ. ሪጅ-አድዋ አብዛኛውን ግዜ የሚከናወኑ ጥናቶች በሥራ ተቋራጩ በኩል የቅድመ ፍተሻ ከተደረገላቸውና ለፕሮጀክቱ ሥራ እንዲውሉ በአማካሪ መሀንዲሱ በኩል ለማፀደቅ የግብዓቶቹን ናሙና በአማካሪ መሀንዲሱ ላቦራቶሪ ውስጥ የሥራ ተቋራጩ ተወካይ ባለበት በጣምራ ናሙና ተወስዶ አስፈላገው ፍተሻ የሚከናወን መሆኑን ገልፀዋል፡፡በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር የመስክ ኦዲቱ ሲካሄድ ፕሮጀክቱ በዝግጅት ወቅት ላይ በመሆኑ ላቦራቶሪዎች አለመሟላቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በደቡብ ሪጅን በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ አማካሪ መሀንዲሱና ተቋራጭ በካምፕ በተገነቡ የተለያዩ ላቦራቶሪ ይጠቀሙ የነበረ ቢሆንም ከቅርብ ግዜ ወዲህ ሥራው ሙሉ ለሙሉ በሚባል ሁኔታ አርባምንጭና አካባቢዋ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እና ካምፑ ከከተማው ካለው ርቀት አንፃር የጋራ ላቦራቶሪ ጥቅም ላይ መዋሉን፤ እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭና አርባ ምንጭ በልታ ሥራውን ከማፋጠን አንፃር በጋራ አንድ ላቦራቶሪ የሚጠቀሙ መሆኑን ገለፀዋል፡፡

49. በኮንትራት ውሉ የጥራት መመዘኛ መስፈርት ክፍል 1000 በሰፈረው መሰረት አማካሪ መሀንዲስ በበላይነት የጥራት ፍተሻን የሚቆጣጠርበት የራሱ የሆነ ላቦራቶሪ በተቋራጭ ሊገነባለት እንዲሁም ተቋራጪ የራሱን ሥራ ቅድመ ፍተሻ የሚያደርግበት የራሱ ላቦራቶሪ ኖሮት ሥራን ማከናወን ያለበት መሆኑን የሚገልፅ በመሆኑ፤ በየዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በምክንያትነት የተጠቀሱ መልሶች የኮንትራት ውሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያላቸው በመሆኑ የኦደት ቡድኑ ተቀባይነት እንደሌላቸው ተገንዝቧል፡፡

50. አንድ ላቦራቶሪን በጋራ መጠቀም በኮንትራት ውል ላይ የተገለፀውን ስምምነት እንዲጣስ ከማድረጉም በላይ የመግባባትን ስሜት በመፍጠር የጥራት መስፈርቶች በተገቢው ሁኔታ እንዳይታዩ በማድረግ የሥራውን ጥራት ያጓድላል፡፡



በጨና ከተማ ጥራቱን ጠብቆ ያልተሰራ አስፋልት



በጨና ከተማ በቤተክርስቲያን አካባቢ በድንጋይ ካብ ለማሰር ተጀምሮ ያልተጠናቀቀን የሚያሳይ ፎቶ

**ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቱ የመድህንና የሥራ ዋስትና ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ**

51. ተቋራጭ የመድህን ዋስትና ማቅረቡን እንዲሁም የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ጨረታ አሸናፊነት በተቀበለ በ 28 ቀናት ውስጥ የሥራ ዋስትና በባንክ በኩል ማቅረቡ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

52. ተቋራጭ የመድህን ዋስትና ተግባራዊ ማድረጉና የጨረታ አሸናፊነት በተቀበለ በ28 ቀናት ውስጥ የሥራ ዋስትና በባንክ በኩል ስለማቅረቡ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የሚከተሉት ግኝቶች በ 4ቱ ፕሮጀክቶች ተገኝተዋል፡፡

- በጊዳሜ-ሙጊ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጩ የመድህን ዋስትና ያላቀረበ መሆኑ፣
- እንዲሁም በአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ የ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጭ የመድህን ዋስትና እንዲያቀርብ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ያላቀረበ መሆኑ፣
- በወሪኢ ሪጅ-አድዋ ፕሮጀክት ተቋራጭ የመድህንና የሥራ ዋስትና ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ተቋራጩ የመድህን ዋስትና ያላቀረበ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

53. ስለሁኔታው የየዳሬክቶሬቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከምዕራብ ሪጅን በጊዳሜ-ሙጊ ተቋራጩ በተደጋጋሚ ተጠይቆ የመድህን ዋስትና ሊያቀርብ ያልቻለ መሆኑን ገልፀው በደቡብ ሪጅን በአርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክት የመድህን ዋስትና ሥራው በሚሰራበት ወቅት ለሚያጋጥም አደጋ ስጋት የሚቀርብ ሲሆን በፕሮጀክቱ ስም ያልቀረበ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በሰሜን ሪጅን በወሪኢ ሪጅ-አድዋ የመድህን ዋስትና በተመለከተ ተቋራጩ በውል አንቀጽ 23.1 መሰረት በተደጋጋሚ ተጠይቀው ያላቀረቡ መሆኑን እንዲሁም በአዲሱ ሳንጃ ቀራቀር የመስክ ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅት በዝግጅት ላይ ያለ በመሆኑ ሲሆን የመድህን ዋስትናውን አቅርቦ ማስተካከያ እንዲያቀርብ የታዘዘበት ግዜ በመሆኑ ዋስትና ያልቀረበ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

54.የመድህን ዋስትናን ተግባራዊ አለማድረግ በፕሮጀክቱ ግንባታ ሂደት ወቅት በሰራተኞች እና በንብረት ላይ ለሚደርስ ድንገተኛ ጉዳት የሚሸፍን ካሳ የሚያሳጣ ሲሆን የሥራ ዋስትና እንዲያዝ አለማድረግ ተቋራጩን በኃላፊነት ግዴታ ውስጥ እንዳይሰራ ያደርጋል፡፡

**የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በውል በተያዘላቸው ዋጋና በታቀደላቸው ግዜ መጠናቀቃቸውን በተመለከተ**

55. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በውል ስምምነት በተያዘላቸው ዋጋና በታቀደላቸው ግዜ መጠናቀቅ እንዲሁም በየበጀት ዓመቱ በተያዘላቸው እቅድ መሰረት መከናወናቸው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

56. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በውል ስምምነታቸው መሰረት በተያዘላቸው ዋጋና በታቀደላቸው ግዜ የሚጠናቀቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት በሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ተገኝተዋል፡፡

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | የፕሮጀክቱ ርዝመት በ ኪ.ሜ | ፕሮጀክቱ የተጀመረበት ዓ.ም | ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ዓ.ም | የፕሮጀክቱ የተራዘመ ማጠናቀቂያ ግዜ | ፕሮጀክቱ የተራዘመበት ግዜ ብዛት | የኮንትራት መነሻ ዋጋ ብር | ክለሳ ዋጋ ብር | የዋጋ ልዩነት ብር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ወልቂጤ-አረቅጥ | 63.31 | ጥቅመት7/2011 | ከሚያዚያ07/2014 | ህዳር17/2014 | 8ወር | 717,440,576.42 | - | - |
| 2. | አረቅጥ-ሆሳዕና | 65.5 | ጥቅመት7/2011 | ከሚያዚያ05/2014 | ህዳር17/2014 እንደገና ግንቦት 2015 | 8ወር ወደ 1 ዓመት ከ 2 ወር | 618,997,534 | - | - |
| 3. | ጅማ-ቦንጋ | 110 | 21/04/2008 | 20/02/2011 | 28/02/2014 | 3 ዓመት | 686,102,036.19 | 679,620,450.08 | (6,481,586.11) |
| 4. | ቦንጋ-ሚዛን | 119.17 | 23/04/2008 | 22 የካቲት 2011 | ሰኔ 30/2014 | 3 ዓመት | 742,938,243.75 | 747,269,898.54 | 4,331,654.75 |
| 5. | ጊዳሜ-ሙጊ | 90.658 | ሰኔ 4/2008 | ሰኔ 3/2011 | እስከ 2014 አልተጠናቀቀም /በተጨማሪ ሥራዎች ምክንያት | 3 ዓመት | 372,420,036.56 | 376,751,691.32 | 4,334,654.76 |
| 6. | ወሪኢ-ሪጅ አድዋ | 62.7 ወደ 67.5 ከፍ ያለ | መስከረም6/2011 | ከነሀሴ 30/2006 | ጥር7/2007 | 5 ወር | 479,111,365.41 | 523,279,419.22 | 44,168,053.81 |
| 7. | መቀሌ ስረት መንደር | 64.64 | ሚያዚያ 18/2011 | አፕሪል 18/2014 | ፌቨሩዋሪ11/2015 | 10 ወር | 482,679,383.62 | 628,074,883.24 | 145,395,499.62 |
| 8. | የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር | 47.95 | የካቲት 24/2009 | ፌቭሩዋሪ 24/2012 | ኦገስት 24/2012 | 7 ወር | 5460964937.82 | - | - |
| 9. | የቀድሞ ሁምቦ | 73.5 | ጥር 1/2008 | ሀምሌ 2/2010 | መስከረም 9/2014 | 3 ዓመት ከ 2ወር | 380,204,197.21 | 502,565,321.05 | 122,361,123.84 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | አርባ ምንጭ | | | | | | | | |
| 10. | አዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ | 31.5 | ግንቦት 10/2013 | | - | - | 707,567,447.75 | 712,567,447 | 4,999,999.25 |
| 11. | አርባ ምንጭ-በልታ | 60 | ሚያዚያ 12/2010 | ሚያዚያ 30/2014 | የግዜ መራዘም የተጠየቀለት | - | 562,946,553.21 | (521,952,869.25)<br>/ዝቅ የተደረገ/ | (40,993,683.96) |
| 12. | አለታ ወንዶ-ዳዬ | 51 | መስከረም 5/2008 | መጋቢት 4/2011 | ጥቅምት 15/2014 | 2 ዓመት ከ 7ወር | 274,878,093.55 | 421,415,749.56 | 146,537,656.01 |
| 13. | ሀረር-ጅግጅጋ | 103.6 | ታህሳስ 2005 | 10 ጥር 2009 | 20 ሚያዚያ 2012 | 2 ዓመት ከ 7ወር | 346,262,115.22 | 455,591,469.02 | 109,329,353.80 |
| | ድምር | | | | | | | | 581,457,995.84 |

በሰንጠረዥ ውስጥ እንደተመለከተው ፕሮጀክቶቹ ከ 5 ወር እስከ 3 ዓመት የግዜ መራዘም ሲፈቀድላቸው የኮንትራት ዋጋ ክለሳ ተጨማሪ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶች አጠቃላይ ድምር ሲታይ ብር 581,457,995.84 መሆኑ፤/ ይህ የብር መጠን ባለስልጣን መ/ቤቱ ከ 2004- 2006 ዓ.ም በትግበራ ላይ ያሉ ፕሮጀክቶች ብዛት 107 በመሆኑ በናሙና ከታየው አንፃር ሲታይ እጅግ የበዛ ብር ጭማሪ የሚታይ መሆኑ/

- እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጅክቶች በየበጀት ዓመቱ በተያዘላቸው እቅድ መከናወናቸውን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 8ቱ በወልቂጤ-አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፣ ጅማ-ቦንጋ፣ቦንጋ-ሚዛን፣ ወሪኢሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር፣ የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭና አርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክቶች በየበጀት ዓመቱ የተያዘላቸውን እቅድ የማይፈፅሙ መሆኑ ከ 2004፣ 2005 እና 2006 ዓ.ም በጀት አፈፃፀም ሪፖርቶች መረዳት ተችሏል፡፡

57. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕናን አስመልክቶ ወልቂጤ-አረቅጥ የዋቤ ወንዝ ድልድይ መሰረት ጥናት ሰብ ኮንትራክተር/Foundation Investigation Sub-Contractor/ መረጣ ላይ ባጋጠመ መዘግየት፣የዋቤ ወንዝ ድልድይ ዲዛይን በወቅቱ ለሥራ ተቋራጩ ባለመሰጠቱ እና ለዋቤ ወንዝ መዳረሻ ግንባታ /Approach Works/ ተጨማሪ ሥራ በመሰራቱ ፕሮጀክቱ መዘግየቱን ገልፀዋል፡፡ በአረቀጥ-ሆሳዕና ጊዜውን ባልጠበቀ ዝናብ ምክንያትና በሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ጥያቄ መሰረት የከተማው መንገድ ክልል በመራዘሙ መዘግየቱን ገልፀዋል፡፡

- ከምዕራብ ሪጅን በጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች በወቅቱ አለመነሳታቸው፣ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ በማጋጠሙ እና የሥራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም ለጊዜ መራዘም ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡የቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክትን በተመለከተ የተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ የሚዛን እና የጨና ከተማን ማርዘም እና ጥቃቅን የዲዛይን ማሻሻያ መጨመር ዋና ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም በጊዳሜ-ሙጊ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በ 2009 እና በ 2010 በአገሪቱ በተከሰተ የሲሚንቶ

እጥረት፣ በዲዛይን ወቅት ያልታየ ግን በግንባታ ወቅት በተከሰተ የአለት ቁፋሮ ተጨማሪ ሥራ፣ ያልተጠበቀ ከባድ ዝናብ እና የተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም ለፕሮጀክቱ በወቅቱ አለመጠናቀቅ ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

- ከሰሜን ሪጅን በወሪኢ. ሪጅ አድዋ በፕሮጀክቱ የተጨመረው ዋጋና የግዜ መራዘም ምክንያቶች በአድዋ ከተማ ውስጥ በክልልና በከተማው መስተዳድር ጥያቄ መሰረት በተደረገ የከተማ ውስጥ የዲዛይን ማሻሻያ ሥራና የከተማውን የመንገድ ክልል በ 4.8 ኪ.ሜ ጭማሪ ተደርጎ እንዲሰራ በተደረገ የለውጥ ትዕዛዝ ምክንያት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም በማይቀንጣል ከተማ ክልልየውሃ ተፋሰሱ ሥራ ከዳን እንዲኖረው በመደረጉ፤ በመቀሌ ስረት መንደር በፕሮጀክቱ መጀመሪያ የነበረው የመንገድ አቅጣጫና የመንገድ ስፋት በክልሉ በኩል በቀረበ ጥያቄ መሰረት አቅጣጫው እንዲቀየርና የመንገዱም ስፋት የከተማይቱን እድገትና የማህበረሰቡን አሰፋፈር መሰረት ባደረገ መልኩ በከተማ ክልል ዲዛይን እንዲሰራ በቀረበው ጥያቄ መሰረት ቀድሞ 7 ኪ.ሜ ይሸፍን የነበረውን መንገድ አቅጣጫ በማስቀየር በ 11.3 ኪ.ሜ ርዝማኔ ባለው አዲስ መንገድ እንዲሻሻል በመደረጉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡በተጨማሪም የቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክት የግዜ መራዘም የተደረገው በአገር አቀፍ ደረጃ ተከስቶ በነበረው የሲሚንቶ እጥረት ምክንያት ሲሆን፤ የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ውጤታማ አለመሆኑ እየታወቀ የግዜ መራዘም የተደረገው በአፈፃፀሙ ላይ መዘግየት ቢኖርበትም ውጤታማ እንደማይሆን በወቅቱ ማወቅ በማይቻልበት ደረጃ በመሆኑና ውሉ በተዋዋዮች መሀል እስካልተቋረጠ ድረስ ሥራ ተቋራጩ የሚገባውን የግዜ መራዘም መከልከል ከውሉ አስተዳደር ውጪና የተቋራጩን መብት የማያስጠብቅና የባለሥልጣን መ/ቤቱን ግዴታ የሚጥስ ፣ስለሆነ መሆኑን ገልፀዋል፡፡
- ከደቡብ ሪጅን የቀድሞው ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክት ዋጋም ሆነ ግዜ መለወጥ ዋነኛ ምክንያቶቹ በመጀመሪያ የፕሮጀክቱ አካል ያልነበረው የአርባ ምንጭ ከተማ የፕሮጀክቱ አካል እንዲሆን ከአካባቢው አስተዳደርና ከህብረተሰቡ በመጣ ጥያቄ መሰረት 6 ኪ.ሜ ርዝመት ያለው ባለ 6 ሌን መንገድ /ይህም በኖርማል ሴክሽን ቢሆን 18 ኪ.ሜ/ እንዲካተት በመደረጉ ሲሆን በኋላም የኩልፎ ድልድይ አስጊ ሁኔታ ላይ በመሆኑ የከተማው የመንገድ ክፍል በቀድሞው መስመር ቢሄድ ህዝብ በብዛት ባልሰፈረበት አካባቢ ስለሚሆን በድጋሚ ከዩኒቨርሲቲ መግቢያ ወደ ጋሞ አደባባይ ሪአላይንመንት እንዲሰራ በመደረጉና 45 ሜ ርዝመት ያለው የኩልፎ ድልድይ እንደ አዲስ በመሰራቱ መሆኑን

ገልፀዋል፡፡እንዲሁም አካባቢው ለጎርፍ ተጋላጭ ከመሆኑ አንፃር አንዳንድ የማሻሻያ ሥራዎች በመሰራታቸው እና በአካባቢው ያልተጠበቀ ዝናብ ለፕሮጀክቱ ግዜ መራዘም ምክንያት መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ በአዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ የአካባቢው ህብረተሰብ ባህላዊ የመስኖ አጠቃቀም በመከተሉ ውሃ አቅጣጫውን በየግዜው በመቀያየሩ መንገዱን ለመከላከል ተጨማሪ የፍሳሽ ማሳለፊያ ፉካዎች መሥራት በማስፈለጉ እና ለራያና ቀሜ ድልድዮች የመሰረት ምርመራ/Geothecnical Investigation/ ተሰርቶ በተገኘ ውጤት የዲዛይን ለውጥ ማድረግ በማስፈለጉ የ ብር 16,809,634.83 የዋጋ ለውጥ መደረጉን ገልፀዋል፡፡

- በአለታ ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክት ለኮንትራት ዋጋ መናር ዋና ምክንያት የደብል ሰርፌስ ትሪትመንት ወደ አስፋልት ኮንክሪት መቀየር ሲሆን፤ይህም በአካባቢው ህብረተሰብ ጥያቄ መሰረት የተፈፀመ መሆኑና በተጨማሪም በአካባቢው ረዘም ያለ የዝናብ ወቅት መኖር የግዜ መራዘም ማስከተሉን እና
- በአርባ ምንጭ-ብልታ ፕሮጀክት በአካባቢው ካለው የመሬት መንሸራተት ችግር አንፃር የቆረጣ ሥራዎችን በመቀነስ የዲዛይን ለውጥ ሥራው የፕሮጀክቱን ዋጋ ሊያስቀንስ ቢያስችልም የመሬት መንሸራተትና በአካባቢው ረዘም ያለ የዝናብ ወቅት መኖሩ የግዜ መራዘም እንዲኖር ያስቸለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. የዲዛይን ቅድመ-ጥናት በሚደረግበት ወቅት መንገዱ የሚያልፍባቸውን የመስተዳደር አካላትና ህብረተሰብ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ከየከተሞቹ አንፃራዊ እድገት ጋር በማገናዘብ ጥልቅ ግንዛቤ ማድረግ እና መንገዱ የሚገነባባቸውን ቦታዎች ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥና የአፈር ዓይነት በባለሙያዎች ማስጠናት እንዲሁም የአካባቢውን የአየር ንብረት በቂ ጥናት አካቶ ለጨረታ ውድድር ከሚቀርቡት ተቋራጮች የተሻለ የሥራልምድ ላለው ሥራውን መስጠቱ ከላይ በመልስ የቀረቡትን ምክንያቶች የሚያስቀር መሆኑን በመገንዘብ የተሰጡት ምክንያቶች ከድንገተኛ ዝናብ መዝነብ የተፈጥሮ ክስተት ውጪ ያሉት ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን የኦዲት ቡድኑ አምኖበታል፡፡

59. በበቂ ቅድመጥናት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ካልተሰሩ መንገዱ የሚሰራለት ህብረተሰብ በታቀደ ግዜ ባለመጠናቀቁ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ፍጥነቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማሳደሩም በላይ አገሪቷ ለሌላ ተግባር የምታውለውን በጀት

ለሚታዘዙ ተጨማሪ ሥራዎች እንድታውል በማድረግ የሀገር ውስን ሀብትን ኢኮኖሚያዊ፣ ብቃት ባለው እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

**ለተጨማሪ ሥራዎች የሚከፈል ክፍያ የኮንትራቱን ዋጋ ከ 15-25% ያልበለጠ መሆኑን በተመለከተ**

60. **የኢትዮጵያ መንገዶች** ባለሥልጣን ተቋራጭ ለሚያቀርበው የተጨማሪ ሥራዎች ክፍያ በአማካሪ መሀንዲስ ታምኖበት የሚደረገው ጭማሪ የኮንትራቱን ዋጋ ከ 15-25% ያልበለጠ ሊሆን ይገባል፡፡

61. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ተቋራጭ ለሚያቀርበው የተጨማሪ ሥራዎች ክፍያ በአማካሪ መሀንዲስ ታምኖበት የተደረገው ጭማሪ የኮንትራቱን ዋጋ ከ 15-25% ያልበለጠ ስለመሆኑ ክትትል ማድረጉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 12 ፕሮጀክቶችበሰንጠረዥ ውስጥ የተመለከቱት ግኝቶች ተገኝተዋል፡፡

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ለተጨማሪ ሥራ የወጣ ወጪ በብር | የመነሻ ኮንትራቱን ዋጋ በፐርሰንት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | ወልቂጤ-አረቅት | 45,056,963.92 | 6 | |
| 2. | አረቅጥ-ሆሳዕና | 42,000,000 | 6.78 | |
| 3. | ቦንጋ-ሚዛን | 4,331,654.76 | 0.58 | |
| 4. | ጊዳሚ-ሙጊ | 45,123,652.20 | 12.12 | |
| 5. | ወሪኢ ሪጅ-አድዋ | 44,168,053.81 | 9.22 | |
| 6. | መቀሌ ስረት መንደር | 145,395,499.62 | 31.02 | ከ 25% በላይ |
| 7. | የቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ | 122,361,123.85 | 32.18 | ከ 25% በላይ |
| 8. | አለታ ወንዶ - ዳዬ | 118,921,452.80 | 48.9 | ከ 25% በላይ |

ከላይ ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው መቀሌ ስረት መንደር፣ የቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭና አለታ ወንዶ ዳዬ ፕሮጀክቶች ከተፈቀደው ከ 25% በላይ ሆነው መገኘታቸው ታውቋል፡፡

62. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤትየየሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን በወልቂጤ-አረቅጥና በአረቅጥ-ሆሳዕና ለተጨማሪ ሥራዎች መከሰት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-

- በወልቂጤና በሆሳዕና ከተማ አስተዳደር ጥያቄ መሰረት የወልቂጤና የሆሳዕና የከተማ መንገድ ክልል በመራዘሙ፣ፕሮጀክቶቹ የሚያልፉባቸው አካባቢዎች ዝናባማ በመሆናቸው የመንገዱ ተሸካሚ/Shoulder/ ከ Sub-base ወደ single Surface Treatment በመቀየሩ እንዲሁም ተጨማሪ የውሃ ማስተላለፊያ ቱቦዎች በሁለቱም ፕሮጀክቶች ላይ በመጨመራቸው፣ በመሬት መንሸራተት ምክንያት የተጨማሪ ድንጋይ ግንብ በማስፈለጉ እና በኪ.ሜ 12+156/ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት መነሻ በ 12.156 ኪሜ ርቀት ላይ / እና 28+376/ፕሮጀክቱ ከተጀመረበት መነሻ በ 28.376 ኪ.ሜ ርቀት ላይ/ የሚገኙት ድልድዮች የእግረኛ መንገድ ስለሌላቸው አራት የእግረኛ ድልድዮች ግራና ቀኝ በመገንባቱ፣
- ከምዕራብ ሪጅን ቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ የህዝብ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በተደረጉ የተጨማሪ ሥራዎች ትዕዛዝና በጥቃቅን የዲዛይን ማሻሻያ ሥራዎች ሲሆን ጊዳሚ-ሙጊን በተመለከተ በፕሮጀክቱ ላይ በዲዛይን ወቅት ያልታየ የአለት ቁፋሮ፣ ገቲ እና የገሪ ድልድዮች እንዲሁም ከኪ.ሜ 81+300 እስከ ኪ.ሜ 159+657 የተደረጉ የዲዛይን ክለሳዎች መሆናቸውን፣
- ከሰሜን ሪጅን በወሪኢ.ሪጅ-አድዋ በአድዋ ከተማ ውስጥ በከተማው መስተዳድር ጥያቄ መሰረት በተደረገ የከተማ ውስጥ የዲዛይን ማሻሻያ ሥራ እና የከተማውን የመንገድ ወሰን 4.8 ኪ.ሜ ጭማሪ በተደረገ የለውጥ ሥራ እንዲሁም በማይቀነባል ከተማ ክልል የውሃ ተፋሰሱ ክዳን እንዲሰራለት በመደረጉ፣መቀሌ ስረት መንደር የመቀሌ ሊንክ ሮድ የአስፋልት ሥራ፣የሀገረ ሰላም የከተማ ክልል መጨመርና የከተማው ዲዛይን ማሻሻያ መሰራት፤እንዲሁም በመሬት መንሸራተት ምክንያት የተደረገ የመንገድ ለውጦች መሆናቸው፡፡
- ከደቡብ ሪጅን ለሁምቦ አርባ ምንጭ ተጨማሪ በጀት ያስፈለገበት ምክንያት በአካባቢው ህብረተሰብና አስተዳደር ጥያቄ የአርባ ምንጭ ከተማ በመንገድ ግንባታው ውስጥ እንዲካተት በመደረጉ እና በድጋሚ የአላይንመንት ለውጥ ተደርጎበት 45 ሜትር ርዝመት ያለው የኩልፎ ድልድይ እንዲካተት በመደረጉ፣የአለታ ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክት ከደብል ሰርፌስ ትሪትመንት ወደ አስፋልት ኮንክሪት በመቀየሩ ምክንያት ሲሆን ተጨማሪው ወጪ ከተፈቀደው ክልል በላይ የሆነበት ምክንያት የተደረገው የሥራ ለውጥ ትልቅ ለውጥ በመሆኑና ሥራው በመጀመሪያው ውል ላይ ያልነበረ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ቦርድን ይሁንታ በማግኘቱ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

63. በባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች የተሰጡት ምክንያቶች በቅድመ ጥናት ወቅት ትኩረት ያልተደረገባቸው በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ አሳማኝ ሆኖ አላገኛቸውም፡፡

64. የመሬትን ጂኦሎጂያዊ ጥናት በጥልቅ አለማጥናት፣ መንገዱ የሚሰራላቸው እና መንገዱ የሚያልፍባቸውን መስተዳድር አካላትና ማህረሰቦች በቅርበት አለማወያየት፣ የከተሞችን አንፃራዊ እድገት በቅድመ ዲዛይን ጥናት ወቅት ዳሰሶ ለመንገድ ዲዛን ሥራው ግብዓት አለማድረግ እና ግዜ ተሰጥቶት ባልተሰራ ዲዛይን ምክንያት የሚከሰቱ ተጨማሪ ሥራዎች የሀገር ሀብት በቁጠባ እና ውጤታማ ለሆነ ስራ እንዳይውል ያደርጋሉ፡፡

## ተቋራጭ ለፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች መከላከያ አሟልቶ መሥራቱን በተመለከተ

65. ተቋራጭ በመንገድ ግንባታ ሂደት ውስጥ የሰራቸው የውሃ ማሾለኪያ እና የፍሳሽ መስመሮች በሚያመነጩት ውሃ የአፈር መሸርሸር እና በህብረተሰቡም ላይ ጉዳት እንዳያስከትል መከላከያ ሊሰራ ይገባል፡፡

66. ተቋራጭ በመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ሂደት ውስጥ የሰራቸው የውሃ ማሾለኪያና የፍሳሽ መስመሮች በሚያወጡት ውሃ የአፈር መሸርሸርና ሌሎች ችግሮች በህብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳያስከትሉ መከላከያ መሥራት ያለበት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 3ቱ የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፡፡

- በአረቅጥ-ሆሳዕና መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በሌራ ከተማ የስትራክቸር ሥራው ፕሮጀክቱ ሳይጠናቀቅ እየፈራረሰ መሆኑ፣ የውሃ መውረጃ/ዲች/ስትራክቸር የሚሰራበት ድንጋይ ወደኖራ አፈርነት የተቀየረ መሆኑ፣ መጋጠሚያ /ጃንክሽን/ ላይ የሚጠቀሙበት ቦታ አቃፊ የሌለው መሆኑ ለሀዋክ ተቋራጭ ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ጽ/ቤት በ 22/07/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ ለማወቅ ተችለዋል፡፡ እንዲሁም በዲች አለመሰራት ምክንያት በመንገዱ ግራና ቀኝ የሚኖሩ ሶስት የግለሰቦች ቤቶች በጎርፍ የተጎዱ መሆኑ፣ በጅማ-ቦንጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ለሸቤ ሰምቦ ወረዳ ጽ/ቤት ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ከመንገድ ጥራት አኳያ ከአስፋልት ወደ ዲች የሚያስገባ የጎርፍ መውረጃ ቀዳዳ ከፍ ብሎ በመሰራቱና ጠባብ በመሆኑ በዝናብ

ወቅት ውሃ አስፋልቱ ላይ የሚተኛና ግለሰቦች ቤት በመግባት ንብረት ያበላሸ መሆኑ ተገልጿል፡፡

- በቦንጋ-ሚዛን መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በጩና ከተማ ወደ ምክር ቤት መግቢያ ላይ መንገዱ ሲሰራየአፈር መገደቢያ ግድግዳ ባለመሰራቱ አፈር እየተናደ መሆኑ፣ ወደ ፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን እና ወደ ጥልቅ ውሃ ጉድጓድ መሄጃ የሚወስደው የመኪና መተላለፊያ ውሃ በሚያልፍበት ቦይ /በዲች/ በመዘጋቱ ማለፊያ የሌለ መሆኑ፤ እንዲሁም በመንገዱ ግራና ቀኝ ዲች የሚፈልጉ ቦታዎች ያልተሰራላቸው በመሆኑ የግለሰቦች ቤት በጎርፍ የተጠቃ መሆኑ በመስክ ኦዲት መረዳት ተችሏል፡፡/በፎቶ የተደገፈ/

67. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖች ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ፡-

- ከማዕከላዊ ሪጅን አረቅጥ-ሆሳዕና ፕሮጀክትን በተመለከተ በፕሮጀክቶቹ ላይ በዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው የፕሮጀክቶች ቁጥጥር ስርዓት አማካሪ መሀንዲስ በማስቀመጥ የሥራዎችን ጥራት ባለሥልጣን መ/ቤቱ እየተከታተለ መገኘቱን እና ሌራ ከተማ ውስጥ ከሚገነባው ፍሳሽ ማስተላለፊያ ሥራ ጋር በተያያዘ በቤት-ሙከራ ውስጥ የተገኙ የናሙና ውጤቶችን ማየት መቻሉን የገለፁ ሲሆን፣
- ከምዕራብ ሪጅን የጅማ -ቦንጋ ፕሮጀክት ተጠናቆ የካቲት 28/2014 ርክክብ የተካሄደ በመሆኑ ተቋራጩ በአሁኑ ወቅት የማስተካከያ ሥራ እና ቀሪ ሥራዎችን እየሰራ በመገኘቱ በሸቤ ሰምቦ ወረዳ የተጠቀሱት ችግሮች ማስተካከያ እየተደረገ በመሆኑ በመጨረሻ ርክክብ ወቅት የሚረጋገጥ መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም በቦንጋ ሚዛን ፕሮጀክት በጩና ከተማ የተጠቀሱት ቀሪ ሥራዎች አማካሪ መሀንዲሱ ከውሉና ከሙያ አንፃር አስተያየት እንዲሰጥበት የተደረገ ሲሆን ፕሮጀክቱ በግንባታ ሂደት ላይ በመሆኑ አስፈላጊው ማስተካከያ የሚወሰድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም የባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ጥራትና ቁጥጥር ደህንነት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ኃላፊ ጥራትና ቁጥጥርን በተመለከተ በሰጡት መልስ ዳይሬክቶሬቱ አዲስ የተቋቋመ በመሆኑ ጥራትና ደህንነት ለመሥራት፤ የሚሰሩትን ኦዲቶች ወጥ ለማድረግ የዲዛይን፣የግንባታ እና የሴፍቲ ኦዲት ቼክ ሊስት ሲያዘጋጅ በመቆየቱ የተገለፁትን ፕሮጀክቶች በመስክ ተገኝቶ ያልተመለከተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

68. በማዕከላዊ ሪጅን በሌራ ከተማ የታየውን የጥራት ችግር አስመልክቶ ስለተሰጠው መልስ የወረዳው አስተዳደር በቅርብ ሁኔታውን በመገንዘብ በማመልከቻ የጠየቀበት በመሆኑ

የተጠቃሚውን አስተያየት ዳይሬክቶሬቱ ከግንዛቤ ማስገባት ያለበት መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በማመን በስራ ኃላፊዎች የተሰጠው መልስ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

69. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው እስፔስፊኬሽን እና እስታንዳርድ ስለ መሰራታቸው አስፈላጊው የቅርብ ክትትል አለማድረግ እና በተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚሰጡ አስተያየቶችን ወይም ያጋጠሙ ችግሮችን አስቸኳይ መልስ አለመስጠት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት እንዲባባስ ሊያደርግ እና የሚገነቡት መንገዶች ያለግዜያቸው እንዲበላሹ ያደርጋል፡፡ /በፎቶ ተደገፈ ማስረጃ/



በቦንጋ ሚዛን የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዲች አለመሰራት ምክንያት ጎርፍ በግለሰቦች ቤት መግባቱን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

**<u>ተቋራጭ ለሚያደርገው የማጠናቀቂያ ግዜ የሥራ መዘግየት 10% የሚያዝበት መሆኑን በተመለከተ</u>**

70. ተቋራጭ ከአቅም በላይ ከሚከሰቱ አጋጣሚ ሁኔታዎች ባሻገር በውል የያዘውን የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት መጠናቀቅ በሚገበው ግዜ ካላጠናቀቀ በግንባታ ሂደት ላደረገው የሥራ መዘግት /Liquidated Damage/ የተሰራውን የመንገድ ግንባታ ሥራ ታሳቢ በማድረግ ካልተሰራው ሥራ 10% ሊያዝበት ይገባል፡፡

71. የመንገድ ግንባታ ተቋራጮች ውል በገቡት መሰረት በግንባታ ሂደት ውስጥ ለሚያደርጉት የሥራ መዘግየት/Liquidated Damage/ የተሰራውን ግንባታ ታሳቢ በማድረግ ካልተሰራው ሥራ10%/አስር ከመቶ/ የሚሆነው ክፍያ የሚያዝባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው በታዩት በ 12ቱም ፕሮጀክቶች፡- ወልቂጤ- አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፣ ጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን፣ጊዳሚ-ሙጊ፣ ወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣ የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር፣ የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ-በልታ፣አለታ ወንዶ-ዳዬ ና ሀረር-ጅግጅጋ ፕሮጀክቶች ተቋራጮች ላደረጉአቸው የሥራ ግዜ መዘግየት ተጨማሪ ግዜ በመፈቀዱ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ለእያንዳንዱንዱ ፕሮጀክት አማካሪ መሀንዲስ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ታውቋል፡፡

72. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የየሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅት-ሆሳዕናን በተመለከተ ሥራ ተቋራጮቹ ያቀረቡት የተጨማሪ ግዜ ይገባኛል ጥያቄዎች በውል አንቀጽ ላይ የሰፈሩትን ዝርዝር የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ግዜን ሊያራዝሙ የሚችሉ ቅድመ ሁኔታዎች በመሟላታቸው መሆኑን፣

- ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋ ና ቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ የመንገድ ግንባታ ተቋራጮቹ ከባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር በገቡት ውል አንቀጽ 47.1 መሰረት የግንባታ ግዜው ከውሉ አንፃር ዘግይቶ ከተገኘ ተፈፃሚነት የሚኖረው ግንባታው የዘገየው በሥራ ተቋራጩ ምክንያት ብቻ ሲሆንና በውሉ ሁኔታ መሰረት የግዜ ማራዘሚያ የማያገኝ ሲሆን መሆኑን፤
- ከሰሜን ሪጅን በውል አንቀጽ 47 መሰረት የሥራ መዘግየት ቅጣት ተግባራዊ የሚሆነው ሥራ ተቋራጩ የፕሮጀክቱን ሥራ በታቀደለት ግዜ ወይም በተራዘመው ግዜ ማጠናቀቅ ሳይችል ሲቀር እና ውሉ ሲጠናቀቅ ምንም ዓይነት የግዜ ማራዘሚያ ጥያቄ ያላቀረበ ከሆነ መሆኑ፣
- የቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክትን በተመለከተ የመጀመሪያ ና የተራዘመ ግዜ ውል ተጠናቆ ተቋራጩ የሚፈለግበትን የውል ግዴታ መወጣት ባለመቻሉ ፕሮጀክቱም በሥራ ተቋራጩ ደካማ አፈፃፀም ምክንያት በውል አግባብ አንቀጽ 63 መሰረት ፕሮጀክቱ ሊቋረጥ በመቻሉ የግዜ መዘግየት ቅጣት ተግባራዊ አለመደረጉን በሌሎቹ ግን የግዜ መራዘም በመጠየቁ ምክንያት ተግባራዊ ሊሆን አለመቻሉን፣

- ከደቡብ ሪጅን በውለታ ሰነድ አንቀጽ 44 ላይ እንደተጠቀሰው ከተቋራጩ አቅም ውጪ በሆነ ምክንያት ለምሳሌ ወሰን ማስከበር፣ባልተጠበቀ ዝናብ፣በዲዛይን ለውጥ ወይም በሌላ አግባብነት ባላቸው ምክንያቶች ሥራው ቢስተጓጎል ተቋራጩ ተጨማሪ ግዜ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣በውል አንቀጽ 47 መሰረት ተቋራጩ የሥራ መዘግየት ካሳ ሊቆረጥበት የሚችለው በመጀመሪያ ወይም በተራዘመ ግዜ ሥራውን መጨረስ ካልቻለ መሆኑን፣በዚህምመሰረት በቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ-በልታና አለታ ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክቶች ተፈፃሚ አለመሆኑን፣
- እንዲሁም ከምሥራቅ ሪጅን የሀረር ጅግጅጋ ፕሮጀክትን በተመለከተ የኮንትራት ውል ተጨማሪ ግዜ የሚያሳጡ ጉዳዮች ከሌሉና ፕሮጀክቱ በመጀመሪያው ወይም በተለወጠው የግንባታ ግዜ አለመጠናቀቅ ምክንያት የተቋራጩ ብቻ መሆኑ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ ባለፈ ማስረዳት ሲቻል ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

73. የባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች በዓመት ውስጥ በእቅድ በተያዘ ፕሮግራም የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ዘርግተው ክትትል ባለማድረጋቸውና እንዲሁም በዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ጭምር ደካማ የሥራ መዘግየት ታይቶባቸዋል ተብለው የተፈረጁ እንደ ሀዋክ፣ ኪንግናም፣የጊዳሚ-ሙጊ/በርሄ-ሃጎስ/ ተቋራጮች ፕሮጀክቶቻቸውን በሶስት ዓመት ግዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ውል ገብተው 3ዓመት የግዜ መራዘም የተደረገላቸው በመሆኑ፤ ላደረጉት የሥራ ማጠናቀቂያ ግዜ መራዘም በውል መሰረት የተሰራውን ሥራ ታሳቢ በማድረግ ካልተሰራው ሥራ ላይ 10% መያዝ ተግባራዊ አለመደረጉ ኦዲት ቡድኑ አግባብነት ያለው **ሆኖ አላገኘውም፡፡**

74. በሥራ አፈፃፀማቸው ደካማ ተብለው በሚፈረጁ ተቋራጮች ላይ በዓመታዊ እቅድ በተካተተ ቁጥጥርና ክትትል እንዲሁም ግምገማ ስርዓት በመከታተል በውል መሰረት 10% እንዲያዝ አለመደረጉ የስራ ተቋራጮቹ የሚያከናውኗቸውን ፕሮጀክቶች በተታቀደላቸው ግዜና የኮንትራት ዋጋ እንዲፈፅሙ ግፊት ለመፍጠር አያስችልም፡፡

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረጉን በተመለከተ**

75. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶችን ለመከታተል የቁጥጥርና ክትትል ስርዓትተግባራዊ ሊያደርግ፣የግንባታጥራትንለመከታተል ከአማካሪ መሀንዲስና ከተቋራጭ ጋር በዓመታዊ እቅድ የተካተተ የሶስትዮሽ ግምገማ ማድረግ፤ እንዲሁም አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በገቡት ውል መሰረት መስራታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

76. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በግንባታው የሥራ ሂደት ጥራቱን የጠበቀ ሥራ መሰራቱን ለማረጋገጥ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከአማካሪ መሀንዲስና ከተቋራጭ ጋር በመሆን የሶስትዮሽ ግምገማ ማድረጉን እና በዓመታዊ እቅድ ማካተቱን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

**በናሙና ተመርጠው በመስክ ኦዲት ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች፡-**

- በወልቂጤ-አረቅጥና በአረቀጥ-ሆሳዕና መንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በሪጅናል ዳይሬክቶሬት ደረጃ መፈታት የማይችሉ ችግሮች ሲያጋጥሙ የሶስቱም ወገኖች ኃላፊዎች በተገኙበት የግምገማ መድረክ በማዘጋጀት ችግሮች እንዲፈቱ የሚደረግ መሆኑን በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ መልስ የተሰጠ ቢሆንም ከ 2004-2006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ የግምገማው ስርዓት በዓመታዊ እቅድ ስለመያዙ እና ፕሮጀክቶቹ በመስክ ክትትል የተገመገሙ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛንና ጊዳሚ-ሙጊ ፕሮጀክቶች በተለያየ ግዜያት ከ 2004- 2006 ዓ.ም በባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊዎች፣ በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ የሶስትዮሽ ውይይት በማድረግ የፕሮጀክቶቹ አፈፃፀም ተገምግሞ የማሻሻያ ሀሳብ መሰጠቱ ቢገለፅም፣ የፕሮጀክት መሀንዲስ ተካፋይ ከሆነበት ቃለ-ጉበኤ ውጭ ሌሎች ከፍተኛ ባለሥልጣናት የተካፈሉበት የመስክ ክትትል ሪፖርት ወይም ግብረ መልስ መሰጠቱን የሚያሳይ ማስረጃ አለመቅረቡ፣
- በወሪኢ. ሪጅ-አድዋ ፕሮጀክት ባለሥልጣን መ/ቤቱ፣ አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በ 2004 ዓ.ም በመስከረም ወር እና 2005 ዓ.ም በ መስከረም ወር በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን መ/ቤት ተገኝተው የሶስትዮሽ ግምገማ ማድረጋቸው ቢገለፅም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣ እንዲሁም የፕሮጀክቱን ሥራ ሂደት መዘግየት አስመልክቶ በሰኔ ወር

2006 ዓ.ም በትግራይ ክልል ርዕሰ-መስተዳድር ቢሮ ሚኒስትሩና የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊዎች በተገኙበት ግምገማ መደረጉ ቢገለፅም የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የያዘ ማስረጃ ለኦዲት ቡድኑ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ፣

- በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በዓመታዊ እቅድ በተካተተ ፕሮግራም ከ 2004-2006 ዓ.ም የመስክ ክትትል በማድረግ የሶስትዮሽ ግምገማ አለማድረጋቸው፣
- የቀድሞው ሁምቦ-አርባ ምንጭ ፕሮጀክት ያልታሰበ የጎርፍ አደጋ በ 2002 ዓ.ም ደርሶበት ለ 10 ወራት ሥራው በተቋረጠበት ወቅትና ተቋራጩ የፋይናንስ ቀውስ በደረሰበት ግዜ ፕሮጀክቱን ወደ መስመር ለማስገባትና በአግባቡ እንዲጠናቀቅ ለማድረግ የሶስትዮሽ ግምገማ መደረጉ፤እንዲሁም መጋቢት16/2014 እ.ኤ.አ የፕሮጀክት መሀንዲሱ የተሳተፈበት በቃለ-ጉበኤ የተደገፈ ማስረጃ የተገኘ ቢሆንም ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዓመታዊ እቅድ ያልያዘው መሆኑ፣
- በአዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭ በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም በባለሥልጣን መ/ቤቱ ኃላፊዎች የመስክ ክትትል የሶስትዮሽ ግምገማ ባይደረግም በፕሮጀክቱ ተወካይና ቡድን መሪ በፈረቃ በየወሩ የሶስትዮሽ የመስክ ግምገማ መደረጉ፣
- በሀረር-ጅግጅጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም የመስክ ክትትል የሶስትዮሽ ግምገማ ከ 2004-02006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ በባለሥልጣን መ/ቤቱ ከፍተኛ ኃላፊዎች የያዘ ኮሚቴ፣ አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ የመስክ ግምገማ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

77. በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገዶች ግንባታ ፕሮጀክቶችን ከ 2004-2006 ዓ.ም የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ መሆኑንና ክትትል ላደረገባቸው ፕሮጀክቶችም ግብረመልሶችን መስጠቱን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በወልቂጤ-አረቅጥ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ዋና ዳይሬክተር ከ 2004-2006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ የመስክ ክትትል አለማድረጋቸው፣ የኢንጅነሪንግ ኦፐሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር 4 ግዜ የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸው፣ የሪጅኑ ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር 2 ግዜ መስክ ጉብኝት ማድረጋቸውና የፕሮጀክቱ መሀንዲስ በየወሩ የመስክ ክትትል ማድረጉ ቢገለፅም የሪጅኑ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የመስክ ክትትል ማስረጃ ያልቀረበ ሲሆን፤ የፕሮጀክቱ መሀንዲስ ሚያዚያ 29/2004 ዓ.ም የዓለም

ባንክ ተወካዮች በተገኙበት ተቋራጩ መሰብሰቢያ አዳራሽ የግምገማ ስርዓት ላይ መሳተፉን የሚያሳይ ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም መ/ቤቱ ዓመታዊ የመስክ ክትትል ስርዓት ዘርግቶ በእቅድ ውስጥ የተካተተ የመስክ ክትትል ያደረገ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በአረቅጥ-ሆሳዕና የባለሥልጣን መ/ቤቱ ዋና ዳይሬክተር ከ 2004-2006 ዓ.ም የመስክ ክትትል አለማድረጋቸው፣ የኢንጅነሪንግ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር መ/ቤቱ በዓመታዊ የመስክ ክትትል እቅድ ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ 4 ግዜ መስክ ጉብኝት ማድረጋቸው የተገለፀ ሲሆን የሰጡት የመስክ ምልከታ የማሻሻያ ሀሳብ/ግብረ መልስ/ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣ የሪጅኑ ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር 2 ግዜ የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸውና የፕሮጀክቱ መሀንዲስ በየወሩ የመስክ ክትትል ማድረጋቸው ቢገለፅም የሪጅኑ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የመስክ ክትትል ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ ሲሆን ፣ የፕሮጀክት መሀንዲሱ በየወሩ የመስክ ክትትል በማድረግ ችግሮች ላይ በቃለ-ጉበኤ በመያዝ ውይይት ቢደረግም በችግሮች ላይ የተወሰደውን መፍትሄ የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑና እየተደረገ ያለውም ክትትል መ/ቤቱ ዓመታዊ የመስክ ክትትል ስርዓት ዘርግቶ በእቅድ ውስጥ ያካተተው የመስክ ክትትል መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን ከ 2004-2006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ጀነራል ማናጀር፣ የኢንጅነሪንግ ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ ዳይሬክተር፣ የቡድን መሪና የፕሮጀክቱ መሀንዲስ በተለያዩ ግዜያት የመስክ ጉብኝት በማድረግ በፕሮጀክቱ አፈፃፀም ላይ የማሻሻያ ሀሳብ ማቅረባቸው ለምዕራብ ሪጅን ዳይሬክቶሬት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ መልስ የተሰጠ ቢሆንም የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ለማሳያ ከቀረቡ ማስረጃዎች በጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት በ 14/12/2012 አማካሪ መሀንዲሱ ቢሮ በተደረገ ስብሰባ ፕሮጀክት መሀንዲሱን ያካተተ የቃለ-ጉበኤ ማስረጃ የቀረበ ቢሆንም በዓመታዊ እቅድ ውስጥ የተካተተ ስለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤ በተጨማሪም ከተሰጠው መልስ ቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክትን የሚያካትት ቢሆንም የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣
- በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት ጀነራል ማናጀርና የኮንትራት ማኔጅመንት ኦፕሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር በ 2004 ዓ.ም ፕሮጀክቱን 3 ግዜ፣ በ 2005 ዓ.ም በግንቦት ወር

ከመንገድና ትራንስፖርት ሚኒስትር ጋር እንዲሁም ሰኔ 2006 ዓ.ም ከመንገድና ትራንስፖርት ሚኒስትሩ ጋር በመስክ ተገኝተው ፕሮጀክቱን የጎበኙ መሆኑ ቢገለፅም ፕሮጀክቱ ተገምግሞ የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳብ የያዘ ማስረጃ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣ የሪጅኑ ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጥቅምት 7/2004፣ ታህሳስ፣ ጥር እና ሐምሌ 2006 ዓ.ም /5ግዜ/ የመስክ ምልከታ ያደረጉ መሆኑ፣ የቡድን መሪና የፕሮጀክት መሀንዲሱ በተለያዩ ወራቶች 11 ግዜ በመስክ ተገኝተው ምልከታ ማድረጋቸው የተገለፀ ቢሆንም ፕሮጀክቱን ገምግመው የሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ በማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

- በአለታ ወንዶ-ዳዬ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከ 2004-2006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ጀነራል ማናጀርና የኮንትራት ማኔጅመንት ኦፐሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር በዓመት ውስጥ 2 ግዜ የመስክ ጉብኝት ያደረጉ መሆኑ፣ የሪጅኑ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በዓመት ውስጥ 3 ግዜ፣ የቡድን መሪና የፕሮጀክቱ መሀንዲስ እያንዳንዳቸው 6 ግዜ የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸውና የመንገድና ትራንስፖርት ሚኒስትሩም 1 ግዜ ጉብኝት ማድረጋቸው ቢገለፅም የተሰጠ የማሻሻያ ሀሳብ ማስረጃ አለመገኘቱና በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም ከ 2004-2006 ዓ.ም በመስክ በመገኘት የገመገሙበትና የሰጡት የማሻሻያ ሀሳብ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሁምቦ-አርባ ምንጭ ጀነራል ማናጀርና የኮንትራት ማኔጅመንት ኦፐሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር እንዲሁም የደቡብ ሪጅን ዳይሬክተር በ 2006 ዓ.ም በጀት ዓመት 1 ግዜ በመስክ ተገኝተው ሥራውን የገመገሙ መሆኑ ለአማካሪ መሀንዲስ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃው ያልቀረበ መሆኑና በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም አለመሆኑ፤ ሆኖም የፕሮጀክቱ ቡድን መሪና መሀንዲስ በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም ባይሆንም በፈረቃ በየወሩ የመስክ ጉብኝት የሚያደርጉ መሆኑ የተገለፀ መሆኑ፤ ለማሳያ ሐምሌ 24/2014 የፕሮጀክት መሀንዲሱ ባለሥልጣኑን ወክሎ በአማካሪ መሀንዲስ ቢሮ ስብሰባ የተሳተፈበት የግምገማ ቃለ-ጉበኤ ማስረጃ የቀረበ መሆኑ፣
- በአርባ ምንጭ-በልታ ከ 2004-2006 ዓ.ም ባለው ግዜ ውስጥ ጀነራል ማናጀሩና የኮንትራት ማኔጅመንት ኦፐሬሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተሩና የሪጅኑ ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የመስክ ክትትል አለማድረጋቸው ሲገለፅ የቡድን

መሪና የፕሮጀክት መሀንዲሱ 3 ግዜ የመስክ ክትትል ማድረጋቸው የተገለፀ ቢሆንም ማስረጃ ማቅረብ ያልተቻለ መሆኑ ታውቋል፡፡

78. ስለ ሁኔታው የባለሥልጣን መ/ቤቱ የየሪጅኖች ኃላፊዎ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ ሆሳዕናን በሚመለከት በአሁኑ ወቅት ከ 100 በላይ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ባለሥልጣን መ/ቤቱ እያስተዳደረ በመሆኑ ዋና ዳይሬክተሩ ሁሉንም መጎብኘት ባይችሉም በተመረጡ ፕሮጀክቶች ላይ የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸውን፣የሶስትዮሽ ግምገማን በተመለከተ የሥራ ኃላፊዎችን የያዘ በኮሚቴ ደረጃ የተዋቀረ አካል የሌለ መሆኑን፤ሁኖም እንደ አሰራር በሪጅናል ዳሬክቶሬት ደረጃ መፈታት የማይችሉ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የሶስቱም ወገኖች በተገኙበት መድረክ ተዘጋጅቶ ችግሮች በውይይት የሚፈቱ መሆኑን፣

- ከምዕራብ ሪጅን ጅማቦንጋና ቦንጋ -ሚዛንን አስመልክቶ አማካሪ ድርጅቶችና ተቋራጮች ከዋናው መ/ቤታቸው ተወክለው በሚመጡ ከፍተኛ ኃላፊዎች የሚገመገም መሆኑን እንዲሁም የሶስትዮሽ ግምገማን በተመለከተ በእቅድ በተያዘ ፕሮግራም ባይተገበርም የፕሮጀክቱን አሳሳቢነት በማየት የሥራ ተቋራጮቹን ወርሃዊ ሪፖርት አፈፃፀም በማየት በውይይት የማሻሻያ ሀሳብ የሚሰጥ መሆኑን፤
- ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋ፣መቀሌ ስረት መንደር እና ሳንጃ ቀራቀርን በተመለከተ የፕሮጀክቶችን አፈፃፀም ለመከታተል እንደ አስፈላጊነቱና እንደየፕሮጀክቱ ሁኔታ የመስክ ጉብኝት የሚደረግ ቢሆንም በዋናነት ግን የሚደረገው ፕሮጀክቱን በሚከታተል መሀንዲስ አብዛኛውን ግዜ በወር አንድ ግዜ በመስክ በመገኘት ሲሆን የክትትሉን አድማስ ለማስፋት ባለሥልጣን መ/ቤቱ አሁን ተግባራዊ እያደረገ ባለው ሞደርናይዜሽን ትግበራ የመስክ ጉብኝት የሚደረግበት አግባብ ለመፍጠር በእንቅስቃሴ ላይ መገኘታቸውን ገልፀዋል፡፡የሶስትዮሽ ግምገማን አስመልክቶ በመቀሌ ስረት መንደርና በወሪኢ ሪጅ-አድዋ ፕሮጀክቶች ላይ በመስከረም 2004 እና 2005 ዓ.ም በአዲስ አበባ በዋናው ቢሮ ዳይሬክተር ጀነራልና የሪጅናል ዳይሬክተሩ በተገኙበት የአፈፃፀም ግምገማ የተደረገ መሆኑን፣በተጨማሪም የመስክ ጉብኝትን በተመለከተ ሪጅናል ዳይሬክተሩ በተለያየ ግዜያት የመስክ ጉብኝት ማድረጋቸው፣የቀድሞው ትራንስፖርት ሚኒስቴር የተከበሩ አቶ ድሪባ ኩማና የቀድሞው የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዳይሬክተር

ጀነራል በአቶ ዛይድ ወ/ገበርኤል የተመሩ ኃላፊዎች ግንቦት 23/2013 የተደረገ መሆኑ፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ መሰረተ ልማት ቋሚ ኮሚቴ ሚያዚያ 25/2014፣ እንዲሁም በትራንስፖርት ሚኒስትሩ የተከበሩ አቶ ወርቅነህ ገበየሁና የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ደፒውቲ ዳይሬክተር ጀነራል የተመሩ ኃላፊዎች ሰኔ 4/2014 የጎበኙ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

- ከደቡብ ሪጅን የክትትልና ቁጥጥር ስርዓትን በተመለከተ ከዳይሬክተር ጀነራል ጀምሮ የተለያዩ ኃላፊዎች በመ/ቤቱ ከሚተዳደሩ ብዙ ፕሮጀክቶች አንፃር እንደሚፈለገው ሁሉንም ማዳረስ ባይችሉም በሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት ላይ ቃለ ጉበኤ ባይያዝም በተለያየ ግዜ የመስክ ጉብኝት በማድረግ የመፍትሄ ሀሳብ የሰጡ መሆኑን ሲገልፁ የሶስትዮሽ ግምገማን በተመለከተ የፕሮጀክት ጥራት ክትትልና ቁጥጥር ሥራ አማካሪ መሀንዲሱ በየዕለቱ የሚያከናውነው የዘወትር ተግባር ሲሆን በባለሥልጣን መ/ቤቱም በኩል በፕሮጀክት መሀንዲሱ በየወሩ፣በቡድን መሪ በየሶስት ወር በሚደረግ መስክ ጉብኝት የሚገመገም መሆኑን፤ ሆኖም በዓመታዊ እቅድ በየፕሮጀክቱ ተነጥሎ ያልተያዘ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

79. ባለሥልጣን መ/ቤቱ እያንዳንዱ የመ/ቤቱ ባለሥልጣን በበጀት ዓመት ውስጥ በእቅድ በተካተተ ፕሮግራም የመስክ ክትትልና ግምገማ የሚያደርግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣ እንዲሁም በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም የሶስትዮሽ ግምገማ በማድረግ በማስረጃ የተደገፈ የማሻሻያ ሀሳብ በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ እጅ አለማኖሩ ፕሮጀክቶችን ከመከታተል አንፃር ያለውን ከፍተኛ ድርሻ አለመወጣቱን የሚያመለክት በመሆኑ የተሰጡት ምክንያቶች በኦዲት ቡድኑ አግባብነት ያላቸው ሆነው አልተገኙም፡፡

80. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም ፕሮጀክቶችን የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ዘርግቶ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም የሶስትዮሽ ግምገማ አለማድረጉ በስራ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች ወቅታቂ ማሻሻያ ለመስጠት የማያስችል በመሆኑ፤ የፕሮጀክቶች የመጠናቀቂያ ግዜ መራዘም ምክንያቶች በር እንዲከፈት አድርጓል፡፡

## ባለሥልጣን መ/ቤቱ የማስተካከያ እርምጃ መውሰዱን በተመለከተ

81. ባለሥልጣን መ/ቤቱ አማካሪ መሀንዲስም ሆነ ተቋራጭ የገቡት ውል ተፈፃሚ ካልሆነ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

82. በባለሥልጣን መ/ቤቱ አማካሪ መሀንዲስም ሆነ ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ሥራው በገቡት ውል መሰረት ተፈፃሚ ካላደረጉ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስድ መሆኑ በተግባርና ኃላፊነቱ ላይ የተገለፀ ሆኖ በናሙና ተመርጠው በኦዲት ወቅት በታዩት12 ፕሮጀክቶች ወልቂጤ- አረቅጥ፣ አረቅጥ-ሆሳዕና፣ጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ- ሚዛን፣ጊዳሜ- ሙጊ፣ ወሪኢ ሪጅ- አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደር፣የቀድሞ ሳንጃ ቀራቀር፣ የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ- በልታ፣አለታ ወንዶ-ዳዬ ና ሀረር- ጅግጅጋ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ የግዜ ማራዘሚያና የኮንትራት ዋጋ ክለሳ ከመፍቀድ ውጪ በውል የገቡትን ግዴታ ሊወጡ ባልቻሉና ተደጋጋሚ ችግር በሚፈጥሩ ተቋራጮችና አማካሪ መሀንዲሶች ላይ ከቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር በስተቀር የወሰደው የማስተካከያ እርምጃ የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

83. ስለ ሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የየሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፤ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕናን በተመለከተ ለፕሮጀክቶቹ የመጠናቀቂያ ግዜ መራዘም ምክንያቶች በውላችን አንቀጽ ላይ የተዘረዘሩትን የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ግዜ ቅድመ-ሁኔታዎችን አሟልተው በመገኘታቸው መሆኑን፣ ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋ፣ ቦንጋ-ሚዛን እና ጊዳሜ-ሙጊ የግዜ ማራዘሚያ የተፈቀደላቸው ውሉ በሚፈቅደው መሰረት ሲሆን የፕሮጀክቶቹን ግንባታ በታቀደው ግዜ እውን ለማድረግ በተለያየ ግዜ ከሥራ ተቋራጮቹ የበላይ ኃላፊዎች ጋር ውይይት እንደተደረገና ማስጠንቀቂያ እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑን፣ ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋና መቀሌ ስረት መንደርን አስመለክቶ የፕሮጀክቶቹ ግዜ ሊራዘም የቻለው ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሰጠው ተጨማሪ ሥራዎች ምክንያት በመሆኑ ገልፀዋል፡፡እንዲሁም በቀድሞው ሳንጃ ቀራቀር ፕሮጀክት ተቋራጩ በተደጋጋሚ ያለውን ደካማ አቋም እንዲያሻሻል ቢመከርም ሊያሻሽል ባለመቻሉ ፕሮጀክቱን እንዲያቋርጥ የማስተካከያ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከደቡብ ሪጅን የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ-በልታና አለታ-ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ፕሮጀክቶቹ የሚተዳደሩት መ/ቤቱና ተቋራጭ በገቡት የውለታ ዶክመንት መሰረት በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ

የሚወሰደውም የውለታ ዶክመንት መሰረት በማድረግ ሲሆን፤ፕሮጀክቶች በታቀደው ግዜ እንዲጠናቀቁ እየሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡እንዲሁም ከምሥራቅ ሪጅን ሀረር-ጅገጅጋ ፕሮጀክትን አስመልክቶ ከአማካሪና ከተቋራጩ ጋር ባለው የውል ግንኙነት መሰረት በተቋራጩም ሆነ በአማካሪው ላይ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል የውል ስምምነት የሚጥስ ድርጊት ባለመገኘቱና መ/ቤቱን ተጠያቂ የሚያደርጉ የፕሮጀክቱ ልዩ ባህሪ የፈጠራቸው ችግሮች በመኖራቸው የግዜ መራዘሚያ በመሰጠቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

84.የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሥራ አፈፃፀም ጋር በተያያዘ የአረቅት-ሆሳዕና /ሀዋክ/፣ የጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን /ኪንግናም/፣ የወሪኢ ሪጅ እና የአለታ ወንዶ-ዳዬ /አለማየሁ-ከተማ/ እና የጊዳሚ-ሙጊ/በርሄ-ሀጎስ/ ተቋራጮች በባለሥልጣን መ.ቤቱ ኃላፊዎች በደካማነት ሲፈረጁ የቆዩና ፕሮጀክቶቹን እስከ 3 ዓመታት ግዜ ያራዘሙላቸው በመሆኑ የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰዱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

85. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ደካማ አፈፃፀም በሚያሳዩ ተቋራጮች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ባለመውሰዱ ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ከሚገባቸው ግዜ በላይ በእጥፍ ግዜ እንዲጨምሩ አድርጓል/ለማሳያ ጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን ከ 3 ዓመት ወደ 6 ዓመት/፡፡

__ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ግብዓት/ማቴሪያል/ አቅርቦት የሚያገለግል የዋጋ ማነፃፀሪያ መኖሩን በተመለከተ__

86. ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ማቴሪያል አቅርቦት ሊያገለግል የሚችል የዋጋ ማነፃፀሪያ/Price Index/ የተዘጋጀ ሊኖር ይገባል፡፡

87.የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በመንገድ ግንባታ ሂደት ውስጥ ለመንገድ ፕሮጀክቶች ማቴሪያል አቅርቦት ሊያገለግል የሚችል ዋጋ ማነፃፀሪያ የተዘጋጀ የሚጠቀም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- ቃለ-መጠይቅ ከቀረበላቸው 5 ሪጅኖች 2ቱ በሰጡት መልስ ከደቡብ ሪጅን ኮንትራት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጥቅም ላይ የዋሉ የዋጋ ማነፃፀሪያዎች በተለይም ለመሳሪያዎች ከውጭ ሀገር መሆናቸው የሀገር ውስጥ ዋጋን ለማነፃፀር ትክክለኛነታቸውን ላያንፀበርቁ የሚችሉ መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን፣ ከምሥራቅ ሪጅን ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ማቴሪያል/ሪኢንፎርሲንግ ባር፤ሲሚንቶ…/ ሊያገለግል የሚችል የዋጋ ማነፃፀሪያ አለመኖር የአገሪቱን ገበያ ሁኔታ የማያንፀባርቅ ዋጋን

በመጠቀም ተቋራጩን ወይም አሰሪውን መ/ቤት ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ የሚችል በመሆኑ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን ከሰጡት መልስ መረዳት የተቻለ ሲሆን ቀሪዎቹ ችግር ያልገጠማቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

88. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሁለቱ ፕሮጀክቶች የሪጅን ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከምሥራቅ ሪጅን ሀረር-ጅግጅጋ ፕሮጀክትን በተመለከተ የዋጋ ማነፃፀሪያ አለመኖር የአገሪቱን የገበያ ሁኔታ የማያንፀባርቅ ዋጋን በመጠቀም ተቋራጩን ወይም አሰሪውን መ/ቤት ለአላስፈላጊ ወጪ የሚዳርግ መሆኑን፤ የዋጋ ማነፃፀሪያ በሌለበት ሁኔታ የዋጋ ማስተካከያ የሚሰራው እቃ አቅራቢዎች በተናጠል የሚሰጡትን ዋጋ መሰረት በማድረግ መሆኑን፣ከደቡብ ሪጅን ሁምቦ አርባ ምንጭ፣ አርባ ምንጭ-በልታ እና አለታ ወንዶ-ዳዬ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ ለግንባታ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ የዋጋ ማነፃፀሪያዎች የውጭ ሀገር መሆናቸው የሀገር ውስጥ ዋጋን ለማነፃፀር ትክክለኛነታቸውን ላያንፀባርቁ የሚችሉ መሆናቸውን ሲገልፁ ሌሎቹ ኃላፊዎች ችግር ያልገጠማቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

89. ለግንባታ የሚያስፈልጉ ማቴሪሎች የዋጋ ማነፃፀሪያ በሀገር ደረጃ አለመዘጋጀቱ ባለሥልጣን መ/ቤቱንም ሆነ ተቋራጩን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

<u>ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ያለው መሆኑን በተመለከተ</u>

90. ባለሥለጣን መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም ካሳ የተከፈለባቸው ንብረቶች በሚነሱበት ግዜ የሚከሰት የፀጥታ ችግርን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡

91. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ከክልሎች መስተዳድርና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር፣ ህብረተሰቡን በማሳተፍ እና ማሳመን እንዲሁም ከሚመለከታቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር ችግሮችን የፈታ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ፡- ባለስልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በወልቂጤ-አረቅጥ በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ የአገልግሎት መስመሮችን መብራት ሃይል በወቅቱ አለማንሳቱ፣ የአካባቢው

ነዋሪዎች በየግዜው የመንገድ ግንባታው ሥራ እንዲቋረጥ ማድረጋቸው እና የአስፋልት ሬንጅ ስርቆት መፈፀሙ ለተቋራጭና ለመንገድ መብት ማስከበር ወኪል በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ታውቋል፡፡በአረቅጥ-ሆሳዕና መብራት ሃይል በወቅቱ የአገልግሎት መስመሩን ባለማንሳቱ በግንባታው ላይ የግዜ መጓተት ማድረሱ፤ እንዲሁም ግለሰቦች ለመንገድ ግንባታ የሚውል ድንጋይ በሚወጣበት ቦታ በመገኘት ሥራ እንዲቆም ያደረጉበት ሁኔታ መኖሩ፣በጅማ-ቦንጋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ከወረዳ፣ቀበሌና ፖሊስ ሃይል አካላት ጋር በቅንጅት ባለመሰራቱ በክምችት የተያዙ የግንባታ ግብዓቶች፣ የማሽነሪና ኢኪውፕመንት እስፔርፓርቶች በአካባቢው በሚኖሩ ግለሰቦች የተሰረቁ መሆኑ ታውቋል፡፡በመንገድ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች አለመነሳትና ባለሥልጣን መ/ቤቱም በወቅቱ ካሳ ክፍያ አለመፈፀሙ፤ እንዲሁም በቦንጋ-ሚዛን መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት መስከረም 18/2009 የሺሺንዳ ከተማ ነዋሪዎች ሥራ ያስቆሙ መሆኑ፣ ሰኔ 29/2011 የዲንብራ ቀበሌ ነዋሪዎች ሥራ ማስቆማቸው፣ ታህሳስ 11/2009 በአካባቢው ነዋሪዎች ሥራ እንዲቆም የተደረገ መሆኑ፣ ግንቦት 19/2012 በውሽውሽና ጨና ከተማ ነዋሪዎች ችግር መፍጠር ምክንያት ሥራ መቆሙ፣ ነሀሴ 03/2012 ኳሪ ሳይት አካባቢ ባሉ ነዋሪዎች ችግር መፍጠር ምክንያት ሥራ መቆሙ፣ በየካቲት 19/2013 ቦሮ ቂፋሮ አካባቢ በሚኖሩ ነዋሪዎች ችግር መፍጠር ሥራ መቋረጡ፣ በሚያዚያ 10/2013 ቦሮ ቂፋሮ አካባቢ በሚኖሩ ነዋሪዎች ምክንያት ሥራ መቋረጡ እና በመንገድ ክልል ውስጥ ለገቡ ንብረት አለመነሳት ችግር መፈጠር ዋና ምክንያት የጠመንጃ ያኀ ወረዳ መስተዳድር አካላት ትብብር አለማድረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

92. በተጨማሪም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ካሳ የተከፈለባቸው ንብረቶች በሚነሱበት ግዜ የሚከሰት የፀጥታ ችግርን ለመከላከል ከሚመለከታቸው ጋር በቅንጅት መሥራቱን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፡- በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 2ቱ በአረቅጥ-ሆሳዕና የመሬት ግመታ በተካሄደበት ወቅት በቀበሌና በግለሰቦች መካከል የመሬት ይገባኛል ፀብ ተፈጥሮ ቀበሌ ለራሱ በማስገመቱ እና ግለሰቦች የኛ ነው በማለታቸው በሥራ ግዜ ላይ ጫና መፈጠሩ ለመንገድ መብት ማስከበር ወኪል በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ተገልጿል፡፡በወሪኢ ሪጅ-አድዋ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገቡ ቤቶች የማጥራት ሥራ በሚሰራበት ወቅት ሚያዚያ 24/2006 ዓ.ም

ከቀኑ 10 ሰዓት አካባቢ አንድ ግለሰብ በመንገድ መብት ማስከበር ወኪል ላይ የድብደባ ሙከራ በማድረግ ሥራ ያስቆመ መሆኑ ለመንገድ መብት ማስከበር በቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ሲገለፅ ለፖሊስ በወቅቱ ለማመልከት ቢችሉም ትብብር አለማድረጉ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ከላይ ለተገለፁት ችግሮች መንስኤው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቅድመ ቅንጅታዊ ሥራ አለመስራቱ መሆኑ በመንገድ መብት ማስከበር ወኪሎች መገለፁ በመስክ ኦዲቱ ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች መረዳት ተችሏል፡፡

93. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖች ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕናን በተመለከተ ከአገልግሎት ሰጪ መ/ቤቶችም ሆነ ከወረዳ/ከከተማ መስተዳደር አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን፤ ነገርግን ግለሰቦች በተለያየ ምክንያት ሥራ የሚያስቆሙበት ሁኔታ ቢኖርም ከሚመለከታቸው ጋር በመነጋገር ችግሮች የሚፈቱበት አግባብ መኖሩን ገልጸዋል፡፡ካሳ የተከፈለባቸው ንብረቶች በሚነሱበት ግዜ የሚከሰት የፀጥታ ችግር ጉዳይ የወረዳው/የከተማው አስተዳደር ኃላፊነት መሆኑን፣ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት የግምት ሥራው በወቅቱ እንዲሰራና የካሳ ክፍያ ከተፈፀመ በኋላ ንብረቶች በወቅቱ እንዲነሱ ኃላፊነትና ሥልጣን ላለው ለወረዳው/ከተማው ማሳወቅና መከታተል መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋ፣ቦንጋ-ሚዛንና ጊዳሜ-ሙጊን አስመልክቶ በፕሮጀክቶች ግንባታ ሂደት ለሚያጋጥሙ ችግሮች ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ግዜያት የጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛን በሚያልፉባቸው የቀበሌ፣የወረዳ፣እንዲሁም የዞን መስተዳድር አካላት ጋር በአካልና በደብዳቤ የችግሮችን አሳሳቢነት በመግለፅ በፕሮጀክቶቹ ላይ ለተፈጠሩ ችግሮች እልባት ለመስጠት ጥረት ያደረጉ መሆኑን፤ይሁን እንጂ በአካባቢው የሚገኙ አንዳንድ የመስተዳድር አካላት ትብብር አናሳ በመሆኑ ችግሮቹን ሙሉ ለሙሉ ለመፍታት አዳጋች ሁኔታዎች መከሰታቸውን፣
- ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋ ፀጥታን በተመለከተ በመንገድ መብት ማስከበር የተከሰተው ችግር ያጋጣሚ ክስተት መሆኑን አሳውቀው በቅንጅት ስለመሰራቱ በተለያየ ግዜ ንብረት ከማንሳት ጋር በተያያዘ ግዜያዊ ችግሮች ሲፈጠሩ ከወረዳው ኮሚቴ ጋር ግንኙነት በመፍጠር እየፈቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ከደቡብ ሪጅን ሁምቦ አርባ ምንጭና በአርባ ምንጭ በልታ በካሳ ክፍያ ሂደት ለተከሰቱ ችግሮች በአዋጁ 455/97 መሰረት ንብረት የማስነሳት ሥራ መከናወን ያለበት በወረዳ አስተዳደር በመሆኑ ንብረት ከማስነሳት ጋር በተያያዘ የሚነሱ የፀጥታ ችግሮች መፍትሄ የሚጠበቀው ከወረዳ መስተዳድር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

94. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው ከተሞችና በሚያልፉባቸው አካባቢዎች ካሉ የመስተዳድር አካላት ጋር የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር ባለመፍጠሩና እንዲሁም በመስተዳድር አካላቱ አማካኝነት የአካባቢው ማህበረሰቦች ስለመንገድ ግንባታው ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ባለማድረጉ ከላይ የተገለፁት ችግሮች የተከሰቱ በመሆናቸው የኦዲት ቡድኑ የተሰጡት ምክንያቶች አሳማኝ ሆነው አላገኛቸውም፡፡

95. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታው ሂደት ከሞመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር የሌለው በመሆኑ በፕሮጀክቶች ግንባታ ሂደት የተለያዩ ችግሮች በመከሰታቸው የግዜ መጓተት እንዲፈጠር እንዲሁም ተቋራጮች ትብብር እንዲያጡ ምክንያት ሆኗል፡፡

<u>የካሳ ገማች ኮሚቴ ዓባላት ስልጠና የተሰጣቸው መሆኑን በተመለከተ</u>

96. በካሳ ክፍያ አዋጅ455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 ላይ ለካሳ ገማች ኮሚቴ ዓባላት ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት በቂ ሥልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

97. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የካሳ ክፍያ ሂደትን ተፈፃሚ ለማድረግ ለካሳ ገማች ኮሚቴ አባላት በካሳ ክፍያ አፈፃፀም አዋጅ 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 ላይ በቂ ስልጠና የሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 5ቱ በወልቂጤ-አረቅጥ፣አረቅጥ-ሆሳዕና፣ በጅማ-ቦንጋ፣በሳንጃ ቀራቀር፣ በወሪኢ ሪጅ-አድዋ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን አማከኝነት ስልጠና አለመሰጠቱ ሲታወቅ በቦንጋ-ሚዛን በወረዳው የፍትህ አካል፣እንዲሁም በመቀሌ ስረት መንደር በባለሥልጣን መ/ቤቱ ድጋፍ ሰጪ ለወረዳ መስተዳድር አካላት ስልጠና መሰጠቱ ቢገለፅም ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በኦዲት ቡድኑ

ለወረዳ መስተዳድር አካላትና ለመንገድ መብት ማስከበር ወኪሎች በቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ከተሰጠ መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

98. **ስለሁኔታው** የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖች ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን በወልቂጤ-አረቅጥና በአረቅጥ-ሆሳዕና በአዋጁና በአሰራሩ ላይ በቂ ግንዛቤ የተደረገ ሲሆን ወደፊትም የሚቀጥል መሆኑን እና የኮሚቴ ዓባላት በአብዛኛው የተማሩ በመሆናቸው አዋጁንና አሰራሩን ለመረዳት ከግንዛቤ በላይ የግድ ሥልጠና የማያስፈልጋቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ከምዕራብ ሪጅን በጅማ-ቦንጋና በቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክቶች በየግዜው የግምት ሥራውን ለመሥራት ለተቋቋሙት ኮሚቴዎችና ለወረዳ መስተዳድር ኃላፊዎች የግንዛቤ ሥራ ሲሰራ መቆየቱን እና አዋጁና ደንቡ ኮፒ እንዲደርሳቸው የተደረገ መሆኑን፤ ይሁን እንጂ በየግዜው በሚደረገው የወረዳ አመራርና የኮሚቴ ዓባላት ለውጥ ምክንያት ሁሉም በቂ ግንዛቤ አለው ለማለት የሚቸገሩ መመሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ከሰሜን ሪጅን ባለሥልጣን መ/ቤቱ አዳዲስ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች ሲጀመሩ ለወረዳ/ከተማ አስተዳደር ኮሚቴዎች ስልጠና እንዲሁም የካሳ ክፍያ ለሚመለከታቸው ህብረተሰቦች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ መስራቱን ገልፀዋል፡፡ ሆኖም በመቀሌ ስረት መንደር ስልጠና የተሰጠበት ሰነድ አለመያዝ ክፍተት ወደፊት ከወረዳ አስተዳደርና ከኮሚቴዎች ጋር በመነጋገር የሚስተካከል መሆኑን፣ከደቡብ ሪጅን ሁምቦ አርባ ምንጭ ከተጀመረ የቆየ በመሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያልተከናወነ ቢሆንም በአርባ ምንጭ በልታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሰራቱን ገልፀዋል፡፡

99. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ቅድሚያ ኃላፊነት ወስዶ ባለው የህግ ክፍል ባለሙያዎች ሥልጠና በመስጠት የካሳ ገማች ኮሚቴ አባላትን ወደ ሥራ አለማስገባቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከላይ የተሰጡትን ምክንያቶች ለኦዲት ቡድኑ አሳማኝ ሆነው አልተገኙም፡፡

100. በካሳ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 ላይ ስልጠና ሳይሰጣቸው የካሳ ገማች ኮሚቴ ዓባላት ወደ ሥራ መግባታቸው አዋጁን እና ደንቡን በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል በማድረግ ተነሺ ህብረተሰቦችን በአሰራራቸው ቅሬታ እንዲያድርባቸው ያደርጋል፡፡

## ለመሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል ካሳ ግምት ሀገር አቀፍ አዋጅን መሰረትያደረገ መሆኑን በተመለከተ

101. ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት የወጣውን ሀገር አቀፍ አዋጅ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

102. ለልማት እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬትና በመሬቱ ላይ ለሚገኝ ንብረት የሚከፈል የካሳ ግምት የወጣውን አዋጅ 455/97 አንቀጽ 4 መሰረት በማድረግ ካሳ ለተነሺ ህብረተሰብ መከፈሉን ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክትትል ማድረጉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 7ቱ የሚከተሉት ሁኔታዎች ታይተዋል፡-

- በወልቂጤ- አረቅጥ ፕሮጀክት ለወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት ቅሬታ ካቀረቡ ተነሺ ግለሰቦች የተወሰኑትን በናሙና በመምረጥ 5 ተነሺ ግለሰቦች ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው 2ቱ ባቀረቡት የቅሬታ አስተያየት 1ኛ በአምቦ ጥርብ የተገነባ ቤት ከተለያዩ ቋሚ ተክሎች ጋር ተመጣጣኝ ካሳ ያልተከፈላቸው መሆኑን ለወረዳ መስተዳድርና ለገማች ኮሚቴ በወቅቱ አመልክተው መልስ ያላገኙ ሲሆን፣ 2ኛ አዲስ መኖሪያ ቤትና የተለያዩ ቋሚ ተክሎች ተነስተው በተመሳሳይ ሁኔታ ተመጣጣኝ ካሳ አለመከፈሉን ለገማች ኮሚቴና ለወረዳ መስተዳድር ቅሬታ ቢያቀርቡም መልስ አለማግኘታቸውን የገለፁ መሆኑ፣
- በአረቅጥ-ሆሳዕና ፕሮጀክት ለ 5 ግለሰቦች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ 2ቱ እያንዳንዳቸው በአቀረቡት ቅሬታ 1ኛ ግለሰቡ ከ 200 በላይ ለሚሆን የባህርዛፍ ቋሚ ተክል፤ እንዲሁም 2ኛ ግለሰብ 150 ካሬ ሜትር የከተማ ቦታ/በሌራ ከተማ/ 300 ቋሚ ተክል ጥድ ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ አለማግኘታቸውን ለወረዳ መስተዳድርና ለካሳ ገማች ኮሚቴ ቅሬታቸውን በማመልከቻ ቢያቀርቡም መልስ ያላገኙ መሆናቸውን የገለፁ መሆኑ፣
- በጅማ-ቦንጋ ለ11 ግለሰቦች ቃለ-መጠይቅ ቀርቦላቸው 4ቱ ባቀረቡት ቅሬታ 1ኛ በሸክላ የተሰሩ ቡቲክና መጠጥ ቤት ብር 400,000 ወጪ የተደረገባቸው፣ 2ኛ ግለሰብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 ላይ ምትክ መሬት ለማይሰጠው የአንድ ዓመት አማካይ ገቢን በ 10 አባዝቶ እንደሚከፈል የተገለፀ ቢሆንም ለቋሚ ተክል ማንጎ፣ግሸጣ፣ ፓፓያ እና ሸንኮራ አገዳ የተከፈለ የአንድ ዓመት ብቻ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣ 3ኛ ግለሰብ የሸቤ ከተማ ነዋሪ የሆኑ አዛውንት በቁጥር BU1/203/01 በቀን 30/02/2003 በተፃፈ

ደብዳቤ የሸቤ ሰምቦ ወረዳ ማህተም ያረፈበት የባለሥልጣን ፊርማ በሌለው ማስረጃ ለኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ወጪ ሆኖ ተልኳል በሚል ብር 46,676.16 ተገምቶ ቤታቸው ፈርሶ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣ 4ኛ  የሸቤ ከተማ ኗሪ ግለሰብ የካሳ መገመቻ ቅፅ ላይ በ 30/02/04 ብር 30,625.76 ተገምቶላቸው ቤታቸው ፈርሶ ግምቱ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣

- በቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክት የወዳ ቁልሽ አርሶ አደር ተቋራጭ ምንም ዓይነት ውል ሳይገባ ከመሬታቸው ላይ ለመንገድ ግንባታው አፈር ቆፍሮ መውሰዱንና በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ብር 4000 የምትገመት ላም ወድቃ መሞቷን የገለፁ መሆኑ፤
- በወሪ ሪጅ-አድዋ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት 12 ግለሰብ ነጋዴዎች በአንድነት ቀርበው ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በአዋጅ 455/97 የ 90 ቀናት የማስለቀቂያ ግዜ በፅሁፍ ተገልፆ የሚሰጥ ቢሆንም በ 6 ቀናት እንዲለቁ በፅፍ መጠየቃቸውን ገልፀው የክልሉ መስተዳድር የከተማና ኢንዱስትሪ ልማት መመሪያ አንቀፅ 42 ተ.ቁ 3 በሚያዘው መሰረት ተለዋጭ ቦታ፣ ቤት፣ቢያንስ የኮንዶሚኒየም ቤት እንዲያገኙ ማድረግ ሲገባ ተፈፃሚ ባለማድረግ እንዲለቁ የተገደዱ መሆኑን መግለፃቸውና  በመንገድ መብት አስከባሪ ወኪሉ በኩልም በህግ አግባብ ተፈፃሚ እንዲሆን ትብብር ያልተደረገላቸው መሆኑን የገለፁ መሆኑ፤
- መቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለቋሚ ተክሎች የአንድ ዓመት ክፍያ በመክፈሉ ምክንያት የትግራይ ክልል መመሪያ የ 1 ዓመት አማካይ ገቢንበ 10 ዓመት አባዝቶ እንዲከፈል ታሳቢ የሚያደርግ በመሆኑ  የከተማው መስተዳድር በ 10 ዓመት አስቦ የከፈለ መሆኑ፤ ሆኖም አዋጅ 455/97 እንዲለቀቅ የተደረገ የሰብል ወይም የቋሚ ተክል መሬትን በተመለከተ በአንቀፅ 15 መሰረት እንዲሁም በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 መሰረት ምትክ መሬት መስጠት ካልተቻለ የሚከፈለው የማፈናቀያ ካሳ ሰብሉ ወይም ተክሉ ያስገኘው አማካይ አመታዊ ገቢ በ 10 ተባዝቶ የሚገኘው መጠን ነው ቢልም በባለሥልጣን መ/ቤቱ ተግባራዊ ባለማድረጉ የአይደር ክፍለ ከተማ እንዲከፍል የተደረገ መሆኑ የተገለፀ መሆኑ፤
- በሁምቦ አርባ ምንጭመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ምዕራብ ዓባያ ወረዳ ዋጅፎ ከተማ 3 ግለሰቦች በቅደም ተከተል ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ 1ኛ ግለሰብ በመንገድ ግንባታው ምክንያት 3 የዋንዛ ዛፎች፣ 2 እግር ብርቱካን፣30 የቤት ክዳን ቆርቆሮዎች፣ 2 እግር ባለ 40 እና ባለ 50 ሜትር ስፋት የሚወጣው ሎል እንጨትና 25 ሜትር ርዝመት አጥር፣

2ኛ/ግለሰብ 79 ግራቪሊያ ቋሚ ተክል፣1 እግር ማንጎ፣2 ዋንዛ፣ 24 ሜትር ርዝመት ያለው አጥር በአጠቃላይ በብር 1,250 3ኛ/ 85 ግራቪሊያ ቋሚ ተክል፣2 ዋንዛና 40 ክዳን ቆርቆሮ ቤት ተመጣጣኝ ባልሆነ ዋጋ መገመታቸው ፍትሃዊ አለመሆኑን በመግለፅ ቅሬታቸውን ለምዕራብ ዓባያ ወረዳና አርባ ምንጭ ዞን ቢያቀርቡም መልስ አለማግኘታቸውን የኦዲቱ ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡፤

103. እንዲሁም ለልማት ሥራ ሲባል ከሚገኝበት መሬት ወደ ሌላ መሬት በመዛወር እንደገና ሊተከል እና እንደነበረ አገልግሎት ለመስጠት ለሚችል ንብረት ንብረቱን የማንሻ፣ የማጓጓዣና መልሶ የመትከያ ወጪ የሚሸፍን ካሳ ሊከፈል እንደሚገባ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 7 ተ.ቁ 5 በተመለከተው መሰረት የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የካሳ ክፍያ መፈፀሙን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- በመንገድ ግንባታው ምክንያት ከጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት የተነሱ ግለሰቦች በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ በፕሮጀክቱ አማከኝነት 50 የአካባቢ ኗሪዎች የሚጠቀሙበት በፊንላንድ ሚሽን የተሰራ የውሃ ፓምፕ ተመልሶ ይሰራል በማለት ተነስቶ ተመልሶ ያልተሰራ በመሆኑ ህብረተሰቡ በውሃ ችግር ላይ ያለ መሆኑን መግለፃቸው፤
- እንዲሁም በአርባ ምንጭ-በልታ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በቦንኬ ወረዳ ገረሴ ከተማ 4 ግለሰቦች በሚከተለው ቅደም ተከተል ቤቶቻቸው በመንገዱ አጠገብ በመሆናቸው ለማንሳት ካሳ ገማች ኮሚቴ እንዲገምትላቸው ጠይቀው መልስ አለማግኘታቸው፡፡

1ኛ. የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተቀኝ በኩል 4.4 ሜትር ርቆ የሚገኝ የመኖሪያ ቤት ባለ 90 ቆርቆሮ ክዳን ለመንገዱ ሲባል የተሞላ ሙሌት በርና መስኮቱን የዘጋውና መንገዱ በሩሎ ሲመታ መሰነጣጠቅ የደረሰበት

2ኛ. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተግራ በኩል 6.5 ሜትር የሆነ በመንገዱ አጠገብ በመሆኑ የመሰነጣጠቅና የጎርፍ ጉዳት የደረሰበት

3ኛ. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተቀኝ 4.8 ሜትር ገባ ብሎ የሚገኝ በመንገዱ ሥራ ማሽን እንቅስቃሴ ምክንያት መሰነጣጠቅና እንዲሁም የጎርፍ መግባት ጉዳት የደረሰበት

4ኛ. የቤት ርቀት የመንገድ ግንባታው ከሚገኝበት ለእግረኛ መንገድ ከተተወ በስተግራ በኩል 2.80 ሜትር የሆነ መንገዱ ከመሰራቱ በፊት ሜዳ የነበረ አሁን በግንባታው ምክንያት በ 5 ሜትር ከፍታ በመሰቀሉ ከቤት ተወጥቶ መቆሚያ ደጃፍ የሌለው ሲሆኑ፤ ከአራቱ ሶስቱ ግለሰቦች ችግራቸው በቦንኬ ወረዳ ታምኖበት በ 26/10/06 እና በ27/12/06 ለኔት ኮንሰልታንት አማካሪ መሀንዲስ በተፃፉ ማመልከቻዎች የካሳ ግምት ተሰርቶላቸው ቤታቸውን ወደ ኋላ በማሸሽ እንዲሰሩ ቢጠየቅም መልስ ያልተገኘ መሆኑ መገለፁ ለግለሰቦቹ ኦዲት ቡድኑ ካቀረበው ቃለ-መጠይቅና ማስረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡




በአርባምንጭ-ብልታ በገረሴ ከተማ በመንገድ ግንባታው ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 2 ቤቶች ካሳ ያልተገመተላቸው መሆኑን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

104. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የየሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕናን በተመለከተ ንብረት አሁን በሌለበትና በተነሳበት ሁኔታ የግለሰቦችን አስተያት ብቻ ተቀብሎ አዋጁ በሚፈቅደው መሰረት ያልተተገበረበት ሁኔታ ብሎ አስተያየት ማቅረብ ተገቢ አለመሆኑን በመቀጠልም የንብረቶቹን ዋጋ የሚያቀርቡት የዞኑ ወይም የወረዳ የሚመለከታቸው ሴክተር መ/ቤቶች በመሆናቸውና አጠቃላይ ግምቱ

የወረዳው/የከተማ አስተዳደሩ ባቋቋመው የንብረት ገማች ኮሚቴ የሚሰራ በመሆኑ በቀጥታ ከፋይ መ/ቤቱን የሚመለከት አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡

- ከምዕራብ ሪጅን በጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት በሸክላ የተሰሩ ቡቲክና የመጠጥ ንግድ ቤት ብር 400,000 ወጪ ተደርጎባቸው ተመጣጣኝ ካሳ ያልተከፈለቸው ስለመባሉ መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 10 ተራ ቁጥር 1 መሰረት ሥልጣን ከተሰጠው የወረዳ ገማች ኮሚቴና በደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 3 ተራ ቁ. 1 መሰረት በወረዳው ባለሙያ በየደረጃው በሚወጣው የቤት ነጠላ ዋጋ መሰረት የቤቶቹ መጠን ተለክቶና በወጣለት ነጠላ ዋጋ ተባዝቶ የግምት ሥራው ተሰርቶ እያንዳንዱ ሰነድ ላይ በኮሚቴ ተፈርሞ በወረዳ አስተዳደሩ ፊርማ ፀድቆ እና እያንዳንዱ ገፅ ላይ የወረዳው ማህተም ተደርጎበት በቃለ-ጉባኤ ተደግፎ በሸኚ ደብዳቤ ሲላክ ክፍያው የሚፈፀም መሆኑን፤ ስለሆነም የካሳ ግምት የሚሰራው ወረዳው ባወጣው የግምት ነጠላ ዋጋ መሰረት በማድረግ እንጂ ግለሰቦች ይህን ያህል ወጪ አወጣን በሚሉት አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ በፊንላንድ ሚሽን የተሰራ የውሃ ፓምፕ የማፈናቀያ ካሳ ባለመሰራቱ ተመልሶ ሊተካ አልተቻለም ስለተባለው በአዋጅ ቁጥር 455/97 ተራ ቁ. 5 በተገለፀው መሰረት የአገልግሎት መስመሮች እንደ ውሃ፣መብራትና ስልክ የመሳሰሉት ንብረቶች ካሳ የመተመን ሥልጣንና ከመንገድ ክልል ውስጥ አንስቶ የማዛወር ሥልጣን ለአገልግሎት መስመር ኃላፊዎች/ለቴሌ፣ ውሃና መብራት ሃይል መ/ቤቶች/ የተሰጠ በመሆኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርሻ በመንገድ ክልል ውስጥ ለገቡትና ተገምተው ለቀረቡት የማዘወሪያ ክፍያ ብቻ መፈፀም በመሆኑ የውሃ ፓምፑን መተካት ያለበት ካሳውን የተቀበለው የሚመለከተው ክፍል ኃላፊነት መሆኑን እንጂ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት አለመሆኑን፣
- ከሰሜን ሪጅን መቀሌ ስረት መንደርን አስመለክቶ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአካባቢ ያስገነባው ነባር መንገድ በመሆኑና በአዋጅ ቁጥር 66/1936 መሰረት ነባር መንገድ ከመሀል ግራና ቀኝ 15 ሜ የመንገድ ክልል ውስጥ ያለ መሬት የባለሥልጣን መ/ቤቱ መሆኑን የተጠቀሰው የህግ አግባብ የሚደነግግ ሲሆን በመንገድ ክልል ውስጥ ለሚገኝ ቋሚ ንብረት ኮሚቴው ገምቶ በሚያቀርበው ግምት መሰረት የአንድ ግዜ የተክሉ ወይም ሰብሉ በነበረበት ሁኔታ ወቅት የአንድ ግዜ ዋጋ ግምት ቀርቦለት ክፍያ እንደሚከፈል አዋጁ የሚደነግግ በመሆኑ በዚሁ መሰረት ክፍያው የተፈፀመ መሆኑን፣

- ከደቡብ ሪጅን ሁምቦ አርባ ምንጭ መንገድ ግንባታ ላይ ዋጅፎ ከተማ ግምት የተሰራው በ 2000 ዓ.ም ሲሆን ዋጋ የማውጣት ኃላፊነት የወረዳው አስተዳደር በመሆኑ በወቅቱ ገበያ መሰረት ወረዳው ትክክል ነው ያለውን ማውጣቱ፤እንዲሁም ንብረትን ከቦታ ቦታ ማዛወርን በተመለከተ የካሳ ክፍያ የሚከፈለው አማካሪ መሀንዲሱ የመሬት አቀማመጡን፣ የመንገዱን ዲዛይን፣ የሥራ ተቋራጩን ጥያቄ መሰረት በማድረግ ተገቢውን ግምገማ አድርጎ በሚልከው የንብረት ይነሳልኝ በመሆኑ በወረዳ/ከተማ አስተዳደር በተቋቋመ ገማች ኮሚቴ ተገምቶ ሲቀርብ በመሆኑ ከላይ የተገለፁት ቤቶች ያልተገመቱት መነሳት የለባቸውም ተብሎ በመታሰቡና ጥያቄ ያልቀረበባቸው በመሆኑ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡

105. የካሳ ክፍያ አፈፃፀም አዋጅ 455/97 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በመስክ በታዩት ፕሮጀክቶች በህግ ክፍሉ በኮሚቴ ደራጃ በወረዳ ለተቋቋሙ ገማች ኮሚቴዎች ተገቢው ስልጠና ያልተሰጠ መሆኑ የተገለፀ በመሆኑ ግንዛቤ ያለገኙ የኮሚቴ ዓባላት አይሳሰቱም ብሎ ማሰብ አግባብነት የሌለው መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በማመን የተሰጡት ምክንያቶችም ተቀባይነት እንደሌላቸው እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱ ክፍያ ከመፈፀም ውጪ ኃላፊነት እንደሌለው ለተገለፀው በባለሥልጣን መ/ቤቱ የተወከሉ የመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ከተሰጣቸው ተግባርና ኃላፊነት መካከል የተነሺ ንብረቶችን ዝርዝር ከማዕከል ወይም በፕሮጀክቱ ከሚገኘው አማካሪ ቢሮ በመረከብ ከመንገድ ክልል ውስጥ የሚነሱ ንብረቶችን በቀረበው ዝርዝር መሰረት በትክክል ለንብረት ገማች ኮሚቴ ማሳየት እንዲሁም የንብረት ገማች ኮሚቴዎች በተገቢው ግዜ የግምት ሥራውን እንዲያጠናቅቁ ማስተባበርና ሥራው በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲከናወን ከሚመለከታቸው የመስተዳድር አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የኮሚቴ አባላት ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እንዲያከናውኑ ማድረግ እንደሚገባቸው የተገለፀ በመሆኑ የተሰጠው መልስ አግባብነት የሌለው መሆኑ ታምኖበታል፡፡

106. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለገማች ኮሚቴዎች ስልጠና ባለመሰጠቱ የካሳ አገማመቱ ስርዓት በተነሺ ግለሰቦች ላይ ቅሬታዎች እንዲያድሩ ምክንያት ሆኗል፡፡

**<u>የግል ባለይዞታና የአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች/ቴሌ፣ውሃና የመብራት ሃይል መ/ቤቶች/በተገቢው ወቅት ንብረታቸውን ያነሱ መሆኑ በተመለከተ</u>**

107. ለልማት እንዲለቀቅ የሚፈለግ መሬት ባለይዞታ የካሳ ግምት በተከፈለው በ90ናኛው ቀን በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 2 መሰረት ንብረቱን ማንሳት፤ እንዲሁም የአገልግሎት መስመር /ቴሌ፣መብራትና ውሃ/ ባለንብረቶች የካሳ ክፍያ በተፈፀመ በ60 ቀናት ውስጥ ካሳ የተከፈለበትን የአገልግሎት መስመር አጠናቆ በማንሳት በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 6 ተ.ቁ3 መሰረት መሬቱን ማስረከብ ይገባል፡፡

108. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ ግንባታ እንዲለቀቅ በሚፈለግ መሬት ባለይዞታው የካሳ ግምት በተከፈለው በ 90ኛው ቀን ንብረቱን አንስቶ ለመንገድ ግንባታ የካሳ አከፋፈል ለመወሰን በወጣ አዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 2 መሰረት ርክክብ መፈፀሙን መከታተሉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 2ቱ በወሪኢ ሪጅ-አድዋ ፕሮጀክት ወረኢለህ ወረዳ ማይቀናጣል ከተማ ግለሰቦች ቤት አናፈርስም በማለታቸው ለክልልና ወረዳ መስተዳድር ደብዳቤዎች መስከረም 19/2005 ዓ.ም፣29/9/2005 ዓ.ም እና 8/06/2005 ዓ.ም በመፃፍ የሥራውን ብዙ ወራት አባክነው መፍረሳቸው በመንገድ መብት አስከባሪው የተገለፀ መሆኑ፤

እንዲሁም በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት ለአርባ ምንጭ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት በአማካሪ መሀንዲስ ጥር 26/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በአርባ ምንጭ ከተማ ከኪ.ሜ184+760 አስከ ኪ.ሜ184+800 በቀኝ በኩል የሚገኙት ንብረቶች የካሳ ክፍያ ተፈፅሞላቸው ባለመነሳታቸው በመንገድ ግንባታው ሂደት የግዜ ተፅዕኖ መፍጠራቸው የተገለፀ መሆኑ፣

- በአዲሱ ሁምቦ -አርባ ምንጭ መንገድ ግንባታ ፕሮጀክት በምዕራብ ዓባያ ወረዳ አስተዳደር በዋጅፎና በኦሞላንቴ ቀበሌ ግለሰቦች የካሳ ግምት አነሰን በማለት ንብረት ያላነሱ በመሆኑ ሥራው ችግር ያጋጠመው መሆኑ በአማካሪ መሀንዲስ የተገለፀ መሆኑ፣ እና በአርባ ምንጭ-ብልታ ፕሮጀክት ለተቋራጩ በኦዲት ቡድኑ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ

በተሰጠ መልስ በመንገድ ግንባታ ክልል ውስጥ የገቡ ንብረቶች 37+100 እስከ 37+300 እንዲሁም 35 +200 እስከ 35 +300 ያሉ የእርሻ ቦታዎች ባለመነሳታቸው ማሽኖች ለብዙ ቀናት መቆማቸው መገለፁን ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ማወቅ ተችሏል፡፡

109. እንዲሁም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች ቴሌ፣ መብራትና ውሃ በአዋጅ ቁጥር 455/97 አንቀጽ 6 ተ.ቁ 3 መሰረት ክፍያው በተፈፀመላቸው በ 60 ቀናት ውስጥ ካሳ የተከፈለባቸውን የአገልግሎት መስመሮች አጠናቆ በማንሳትመሬቱን ለግንባታ ያስረከቡ መሆናቸውን መከታተሉን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ፡-በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 8ቱ፡-

- በውልቂጤ-አረቅጥ የመብራት ሃይል መ/ቤት ፖሎችን በማንሳት በኩል ችግር በመፍጠር የሥራ ግዜ እንዲጓተት ያደረገ መሆኑ፣ በአረቅጥ-ሆሳዕና በቀቡልና በአረቅጥ ከተማ መብራት ሃይል ለማንሳት ሁለት ዓመት ያስፈልጋል በማለት ያላነሳ መሆኑ፣
- በጅማ-ቦንጋ ፕሮጀክት ውሃ፣ቴሌና መብራት ሃይል ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችግር የሚታይባቸው መሆኑ ሲገለፅ በተለይም መብራት ሃይል  አጅግ የከፋ መሆኑ፣በቦንጋ - ሚዛን ፕሮጀክት በሚዛን ከተማና በአካባቢው ያሉ ፖሎችን መብራት ሃይል አለማንሳቱ፣
- በወሪኢ-ሪጅ አድዋ ፕሮጀክት የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን መ/ቤት የማይቀናጣል ከተማ የአገልግሎት መስመሩን ለማንሳት ካሳ በ 2004 ዓ.ም ተከፍሎት በ 2006 ዓ.ም በማንሳት በፕሮጀክቱ ላይ ከፍተኛ የግዜ ጫና ማሳደሩ የተገለፀ መሆኑ፣ በመቀሌ ስረት መንደር ፕሮጀክት በመቀሌና ሀገረ ሰላም ከተማዎች የኤሌክትሪክ ፖሎች በወቅቱ ባለመነሳታቸው ችግር በመፍጠራቸው የተገለፀ መሆኑ፣
- በቀድሞው ሁምቦ አርባ ምንጭ ፕሮጀክት የአርባ ምንጭ ቴሌ፣መብራትና ውሃ ልማት ድርጅቶች የአገልግሎት መስመሮቻቸውን ባለማንሳታቸው የፕሮጀክቱ ሥራ እንዲዘገይ ያደረጉ መሆናቸው፤ በተለይ በአርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ በነበረ ሥራ ቴሌ መስመሩን ባለማንሳቱ እንዲዘገይ ማድረጉን ለአርባ ምንጭ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት ነሀሴ 01/2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የተገለፀ መሆኑ፣
- በአዲሱ ሁምቦ- አርባ ምንጭ ፕሮጀክት በመንገድ ክልል ውስጥ የገባ ውሃ መስመር የካሳ ግምት ተሰልቶ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ገንዘቡ ፈሰስ ሲደረግ የላንቴ ከተማ የውሃ ኮሚቴ ገንዘቡ ወደግለሰብ አካውንት እንዲገባ በመጠየቁ የክፍያ ሂደቱ በመስተጓጎሉ ጥቅምት 26/2007 ዓ.ም ህብረተሰቡን በማስተባበር ሁከት በመፍጠር ተቋራጭ ሥራ

እንዳይሰራ ያደረገ ሲሆን፤ ሂደቱም ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅትምመቀጠሉ የተገለፀ መሆኑ፣ በአርባ ምንጭ-በልታ ፕሮጀክት የመብራት ሃይል የመብራት ፖሎችን ባለማንት የሥራ እንቅፋት እየሆነ መገኘቱ በአማካሪ መሀንዲስና በመንገድ መብት አስከበሪ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ወኪሎች በኦዲት ቡድኑ ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ መረዳት ተችሏል፡፡

110. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖቹ ዳሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ ሆሳዕናን በተመለከተ ከፍተኛ ችግር የሆነው መብራት ሃይል መሆኑን፣

- ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ የአገልግሎት መ/ቤቶች በ 60 ቀናት ውስጥ ማንሳት እንዳለባቸው በአዋጁ ቢቀመጥም ኃላፊነቱ የአገልግሎት መስመር ሰጪ ባለቤት መሆኑን፤ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለአገልግሎት መስመር ባለቤትና ለሚኒስቴር መ/ቤቶች ያሳወቀ መሆኑንና አስካሁንም ድረስ በሚፈለገው ፍጥነት ለማንሳት/ለማዛወር እልባት ያልተገኘ መሆኑ፣
- ከሰሜን ሪጅን ወሪኢሪጅ-አድዋና መቀሌ ስረት መንደርን በተመለከተ  የአገልግሎት መስመሮችን አስመልክቶ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና ለሌሎች የአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች በመንገድ ወሰን ውስጥ ለገቡ ንብረቶች ካሳ በመክፈል ህጉ በሚያስቀምጠው ቀናት ውስጥ ንብረታቸውን እንዲያነሱ በተደጋጋሚ በተፃፉ ደብዳቤዎች ቢጠየቁም እንዲሁም ጥምር ኮሚቴ ከተለያዩ መ/ቤቶች ተዋቅሮ ስለሚያነሱበት ሁኔታ ውይይት የተደረገ ቢሆንም መ/ቤቶቹ ፖል፣መኪና የለም በማት ያላነሱ መሆኑን እና በአሁን ወቅትም ክፍያውን ተቀብለው ያላነሷቸው ብዙ ንብረቶች በመኖራቸው በግንባታ ሂደት ላይ የግዜ መጓተት እየፈጠሩ መሆኑን፣
- ከደቡብ ሪጅን የቀድሞ ሁምቦ አርባ ምኝጭ፣ አርባ ምንጭና አዲሱ ሁምቦ አርባ ምንጭን በተመለከተ በሪጅኑ ካለው የመንገድ መብት ጥበቃ ወኪል እጥረት አኳያ በየፕሮጀክቱ ኤጀንት በቋሚነት መድቦ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴን መከታተል ባይቻልም አማካሪ መሀንዲሱ በየግዘው በሚሰጠው መረጃ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገርና ደበደዳቤ በመፃፍ እንደአስፈላጊነቱ ኤጀንት በመላክ ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት ጥረት ያደረጉ መሆኑን እና አርባ ምንጭ በልታ ላይ የሚሰራ የመንገድ መብት ወኪል ያለ ሲሆን የተጠቀሰው ችግር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

111. ከደቡብ ሪጅን በመንገድ መብት አስከበሪ ወኪል የቀረቡ ችግሮች በመሆናቸው የተሰጠው መልስ የኦዲት ቡድኑ አግባብነት የሌለው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

112. የባለሥልጣኑ መ/ቤት በመንገድ ግንባታ ሂደቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና እንዲሁም በመንገድ ግንባታው ምክንያት የመሬት ባለይዞታነት የሚያጡና ንብረት የሚያነሱ ግለሰቦችና የአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች ቅድመ-ግንዛቤ በመስጠት የትስስር ውህደት ባለመፍጠሩና ከዚህም ባሻገር ከሳ ከከፈለ በኋላ በአዋጁ የተደነገጉትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ ለህጋዊ አካል ማቅረብ ባለመጀመሩ በግንባታ ሂደት የሚገኙ ፕሮጀክቶች ላይ የግዜ መጓተት እንዲኖር አድርጓል፡፡

## መሬት ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ ሲለቀቅ ካሳ ጠያቂው አካል ህጋዊ ባለቤት ስለመሆኑ የሚረጋገጥ መሆኑን በተመለከተ

113. መሬት ለመንገድ ግንባታ እንዲለቀቅ ሲወሰን ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሊያቀርብ ይገባል፡፡

114. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በካሳ ክፍያ ሂደት ውስጥ ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ በማቅረብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 መሰረት የካሳ ክፍያ መፈፀሙን መከታተሉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው ከታዩት 9 ፕሮጀክቶች በ 8ቱ ፡- በወልቂጤ-አረቅጥ በቸሃ አስተዳደር ወረዳ ጽ/ቤት፣በአረቅጥ-ሆሳዕና በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣

- በጅማ-ቦንጋ በሸቤ ሰምቦ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ በቦንጋ-ሚዛን በጨና ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣በወሪኢ. ሪጅ-አድዋ በአድዋ ወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት፣ በመቀሌ ስረት መንደር በዓይደር ክፍለ-ከተማ ጽ/ቤት በሁምቦ-አርባ ምንጭ በምዕራብ ዓባያ ወረዳ ጽ/ቤት እና በአርባ ምንጭ-በልታ በቦንኬ ወረዳ ጽ/ቤት ካሳ የተከፈላቸው ተነሺ ግለሰቦች ህጋዊ ባለይዞታ ስለመሆናቸው የተረጋገጠበት ማስረጃ በመዝገብ ቤታቸው ያልተገኘ ሲሆን፣ እንዲሁም በ ኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በመንገድ መብት አስከባሪ ወኪልነት

በሚሰሩ ግለሰቦች እጅም ማስረጃው አለመገኘቱ በኦዲት ቡድኑ ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ማወቅ ተችሏል፡፡

115.ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤት የሪጅኖች ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከማዕከላዊ ሪጅን ወልቂጤ-አረቅጥና አረቅጥ-ሆሳዕናን በተመለከተ የንብረት ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ኃላፊነት የወረዳው/የከተማው አስተዳደር በመሆኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱ ይህን ለማረጋገጥ የተሰጠው ኃላፊነት የሌለ መሆኑን፣ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋና ቦንጋ-ሚዛንን በተመለከተ የባለሥልጣኑ መ/ቤት ተወካይ ኤጀንቶች የግምት ሥራውን በሚያስተባብሩበት ወቅት የወረዳው ኮሚቴ የባለቤትነት ማረጋገጫ እየጠየቀ እንዲሰራ አስፈላገውን ክትትል የሚያደርጉ መሆኑን፤ ይሁን እንጂ በደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 21 መሰረት መረጃ የመያዝ ግዴታ የወረዳ መስተዳድሩ መሆኑን፣

- ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ. ሪጅ-አድዋ፣ መቀሌ ስረት መንደርን አስመለክቶ አዋጅ ቁጥር 455/97 በመንገድ ክልል ውስጥ ለገቡ ንብረቶች የካሳ ግምት የመሥራት ኃላፊነትና ስልጣን ለወረዳ ወይም ለከተማ መስተዳድር የተሰጠ በመሆኑ የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታነት መረጋገጥ ያለበት በወረዳ መስተዳድር አካለት መሆኑን፤ሆኖም የባለሥልጣኑ መ/ቤት ኃላፊነት የግምት ሰነድ በወቅቱና በአግባቡ እንዲሰራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ድምሩ ልክ መሆኑን አረጋግጦ ክፍያ መፈፀም መሆኑን፣
- ከደቡብ ሪጅን ሁምቦ አርባ ምንጭና አርባ ምንጭ-በልታን በተመለከተ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ስለማይኖር በአስረጂነት የቀበሌ ሊቀመንበሩ በኮሚቴ ውስጥ እንዲካተት ተደርጎ በአዋጁ መሰረት በተቋቋመው ገማች ኮሚቴ ዓባላትም በግምት ሰነዱ ላይ እንዲፈርሙ በማድረግ የወረዳው አስተዳደሩ በመጨረሻ ስለሚያፀድቀው በተገቢው መልኩ ሊፈፀም የሚችል መሆኑን እንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡

116. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ከተሰጡት ኃላፊነትና ተግባር ላይ የካሳ ግምት በሚሰራበት ወቅት የንብረቱ ዓይነት በትክክል መለየቱን፣ልኬት በትክክል መወሰዱን፣ የቤቶች ደረጃ ፍተሀዊ መሆኑንና ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተል ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ተገቢውን ሪፖርት ማቅረብ አለበት የሚል በመሆኑ፤ካሳ የሚከፈለው አካል የመሬቱ ህጋዊ

ባለይዞታና የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚያስፈልገው ጉዳይ በመሆኑ፤ የዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ጉዳዩ የወረዳ መስተዳድር አካላትን ብቻ የሚመለከት አድርገው ባለሥልጣን መ/ቤቱ ግምት ብቻ መክፈል ላይ ትኩረት ያደርጋል ብለው የሰጡት መልሶች በኦዲት ቡድኑ ተገቢ ሆነው አልተገኙም፡፡

117. ካሳ እንዲከፈለው የሚጠይቅ ማንኛውም አካል የሚለቀቀው መሬት ህጋዊ ባለይዞታና ካሳ የሚከፈልበት ንብረት ባለቤት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ በተጠቀሱት ወረዳ መስተዳድር መዝገብ ቤቶች እና በመንገድ መብት ማስከበር ወኪሎች እጅ አለመገኘትና የቀበሌ መስተዳድር አካላት በሚያቀርቡት ስም ዝርዝር ብቻ ክፍያ መፈፀሙ ሊከፈላቸው የማይገባቸው ግለሰቦችን አለአግባብ ተጠቃሚ ከማድረጉም በላይ የሀገሪቷን ሀብት ለማባከን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

## <u>ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ ውሳኔ የተሰጠው መሬት ክትትል የሚደረግለት መሆኑን በተመለከተ</u>

118. ለልማት የሚለቀቅ መሬት ስለመሆኑ ውሳኔ የተሰጠው ባለይዞታ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ለተሰራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ለተተከለ ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሳ እንዳይከፈል በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 መሰረት ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡

119. የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለልመት የሚለቀቅ መሬት ስለመሆኑ ውሳኔ የተሰጠው ባለይዞታ ውሳኔ ከተሰጠው በኋላ ለተሰራ ወይም ለተሻሻለ ቤት፣ ለተተከለ ቋሚ ተክል ወይም በመሬት ላይ ለተደረገ ቋሚ ማሻሻያ ካሳ እንዳይከፍል ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለበት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 የተመለከተውን በካሳ ክፍያ ሂደት ውስጥ ክትትል ማድረጉን ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በ 2ቱ፡- በጅማ-ቦንጋ የጎላ ችግር መኖሩ በመንገድ መብት ማስከበር የተገለፀ ሲሆን የመንገዶችን ወሰን የሚያስከብር መደበኛ ቋሚ የመንግሥት አካል ማስፈለጉን የገለፁ መሆኑ፣

- በወሪኢ. ሪጅ-አድዋ በመንገድ መብት ማስከበር ወኪል ከተሰጠ መልስና ከውሳኔ አልፎ ካሳ ከተከፈለ በኋላ እርሻ ማረስ፣ተክሎች መትከልና ግንባታዎች መሥራት የመንገዱን

ወሰን በማለፍና መሀል መንገዱን በመጠጋት በወሪኢ.ሊህ ወረዳ አድዋ ከተማና አዲአቡን አልመዳ ጨርቃጨርቅ አካባቢ ችግሩ በግልፅ መታየቱን ከቀረበ ቃለ-መጠይቅና በኦዲቱ ወቅት በተ ተደረገ የመስክ ምልከታ ማወቅ ተችሏል፡፡

120. የባለሥልጣኑ መ/ቤት የምዕራብና የሰሜን ሪጅን ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ በቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፤ ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋን በተመለከተ ከቅየሳ በኋላ እና የንብረቶቹ ዝርዝር ከተያዘ በኋላ ተጨማሪ አዳዲስ ንብረቶች ካሳ ለማግኘት ተብሎ ሲካተቱ ህገ ወጥ ከሆኑ እንዲሰረዙ የሚደረግ መሆኑን፤ሆኖም ግን ዝርዝሩ ሲሰራ ሳይካተቱ የቀሩ ከሆኑ የሚመለከታቸው ወረዳዎችና ኮሚቴዎች ማብራሪያ በመስጠት ተጨማሪ መረጃ አያይዘው የሚልኩ መሆኑን፤ሆኖም ግን ጉዳዩን መከታተል ያለባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች መሆናቸውን፤እንዲሁም ችግሩ ለዘለቄታው እንዲፈታ ጠንካራ የክትትልና የሰነድ አያያዝ ስርዓት ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑን፣ ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ-አድዋ ካሳ ከተከፈለ በኋላ የመንገድ ወሰንን በማለፍ እርሻ ላረሱ፣ቋሚ ተክሎች ለተከሉና ግንባታዎችን ላከናወኑ ግለሰቦች በወቅቱ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የመንገድ ጥበቃ ባለሙያ ለወረዳው አስተዳደር አካላት በቃልና በጽሁፍ ያመለከቱ መሆናቸውን፤እንዲሁም ባለሥልጣን መ/ቤቱም ለተከናወነው ህገ ወጥ ግንባታ በወረዳው በኩል እርምጃ እንዲወሰድ በጽሁፍ አሳውቆ ክትትል እያደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

121. በምዕራብ ሪጅን የተገለፀውን ጉዳዩን መከታተል ያለባቸው ወረዳዎችና ቀበሌዎች ናቸው ለሚለው መልስ በባለሥልጣኑ መ/ቤቱ የመንገድ መብት ማስከበር ወኪል ተግባርና ኃላፊነት ላይ ንብረቶችን በዝርዝር መመዝገብና ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች መከታተል ያለበት መሆኑ የተገለፀ በመሆኑ የኦዲት ቡድኑ የተሰጠው መልስ ተገቢ ሆኖ አለገኘውም፡፡

122. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በመንገድ ክልል መሆናቸው ውሳኔ ከተሰጣቸው በኋላ የተሰሩት ሥራዎች ህገ ወጥ መሆናቸውን በደብዳቤ ካሳወቀ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 በሚደነግገው መሰረት በህግ አግባብ እንዲታይ አለማድረጉ ግለሰቦች ህግ ጥሰው ተገቢ ያልሆነ ድርጊት እንዲፈፅሙ አድርጓል፡፡

## በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የካሳ ግምት አሰራር መኖርን በተመለከተ

123. ከወረዳ ወረዳ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የካሳ ግምት አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

124. ከወረዳ ወረዳ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የካሳ ግምት አሰራር መኖሩን በተመለከተ ኦዲት ሲደረግ በናሙና ተመርጠው በመስክ ከታዩት 9 የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶ በ 5ቱ፡-

- ለወልቂጤ-አረቅጥ መንገድ መብት ማስከበር ወኪል በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠ መልስ አንድ ወጥ የሆነ የንብረት ዋጋ ግምት አሰራር ቢኖር ለአሰሪው ጥሩ መተማመኛ መሆኑን መገለፁ፣ በአረቅጥ-ሆሳዕና ለምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ጽ/ቤት በቀረበ ቃለ-መጠይቅ ከተሰጠ መልስ በካሳ አገማመት ሂደት ውስጥ ባለንብረቶች የተገመተላቸውን ንብረቶች ከጎረቤት ወረዳ ጋር በማነፃፀር ቅሬታ የሚሰማቸው መሆኑን እና ወጥ የካሳ ግምት አሰራር አለመኖር ተመሳሳይ ንብረትና ቋሚ ተክል ባነሰ ወይም በበለጠ ዋጋ እንዲተመን በማድረጉ ቅሬታ እንዲኖር ማድረጉ፣
- በጅማ-ቦንጋ ለሸቤ ሰምቦ ወረዳ አስተዳደር በኦዲት ቡድኑ ለቀረበ ቃለ-መጠይቅ በተሰጠ መልስ ወጥ የካሳ ግምት አሰራር አለመኖር አካባቢንና ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታን የማገናዘብ ችግር የታየበት በመሆኑ የግመታው ስርዓት አንድ ወጥ ቢሆን ለአሰራር አመቺ መሆኑን፣
- በቦንጋ-ሚዛን ፕሮጀክት የካሳ ግምት አሰራሩ ወጥ ባለመሆኑ በተለይም በግንባታ ንብረቶች ላይ ችግር መፍጠሩ የጨና ወረዳ መስተዳድር ጽ/ቤት መግለፁ፣
- በወሪኢ. ሪጅ-አድዋ ወጥ የካሳ ግምት አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት የምርት ዋጋን በተጋነነ መልኩ በማቅረብ፤ እንዲሁም የጎረቤት ወረዳዎች ተመሳሳይ ንብረት በከፍተኛ ዋጋ ሲተመን የኛ ለምን አነሰ በማለት ችግሮች መከሰታቸው የተገለፀ መሆኑ በኦዲቱ ወቅተ ከቀረቡ ቃለ-መጠይቆች መረዳት ተችሏል፡፡

125. ስለሁኔታው የባለሥልጣኑ መ/ቤትየየሪጅኖቹ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ከምዕራብ ሪጅን ጅማ-ቦንጋና ቦንጋ ሚዛንን

በተመለከተ በቦንጋ-ሚዛን  በጨና ወረዳ መስተዳድር በግንባታ ንብረቶች ላይ ወጥ ዋጋ ባለመኖሩ ለካሳ ግምት  ሥራው ችግር የፈጠረ መሆኑን መገለፁን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 455/97 በአንቀጽ 9/2/  ላይ የካሳን መጠን ለመገመት የሚቻልበት አቅም ለመፍጠር የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር አግባብ ካላቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥት አካላት ጋር በመመካከር እስኪያረጋግጥ ድረስ ንብረት የሚገመተው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 በሚቋቋሙ ኮሚቴዎችና በአገልግሎት መስመር ባለቤቶች መሆኑን የሚገልፅ በመሆኑና በአንቅጽ 10 ተራ ቁ 1 መሰረት ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ሲሆን ችግሩ ሊፈጠር የቻለው በባለሙያ እጥረት ሳይሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ የዋጋ/ Standard/ ባለመኖሩ መሆኑን፣ከሰሜን ሪጅን ወሪኢ ሪጅ አድዋን አስመልክቶ በካሳ አገማመት ላይ የነጠላ ዋጋን በተመለከተ ከአካባቢ አካባቢ የዋጋ ልዩነት ሊፈጠር የሚችል መሆኑን ለምሳሌነትም የእርሻ ምርት ትርፍ አምራች በሆነና ባልሆነ አካባቢ፣የዛፍ ተክል ቢወሰድ በአካባቢው ያለው የዛፍ መጠን እንዲሁም ቤትን ብንመለከት የተሰራበት ማቴሪያል ሁኔታዎች መኖር የዋጋ መለያየት እንዲኖር ሊያደርጉ የሚችሉ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

126. የሰብሎችና የቀዋሚ ተክሎች እንዲሁም የግንባታ ቤቶችን ከፋፍሎ ደረጃ በማውጣት ወጥ ሀገር አቀፍ ዋጋ አለመዘጋጀቱ የአገማመት ሁኔታው በአጎራባች ወረዳዎች ለተመሳሳይ ንብረት ተመሳሳይ ክፍያ ባለማስገኘቱ በካሳ ተከፋዮች ላይ ቅሬታ ፈጥሯል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሀሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶች ላይ እንደተመለከተው በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን የመንገዶች ኮንትራት አስተዳደርና የካሳ ክፍያ አፈፃፀምን በተመለከተ በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ በታዩት የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች የሚከተሉት መደምደሚያዎች ተሰጥተዋል፡-

127. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ የዲዛይን ሥራዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተው እንዲሰሩ ባለማድረጉ እንዲሁም በቅድመ ዲዛይን ጥናት ወቅት የማህበረሰቡንና የመስተዳድር አካላትን ሀሳቦች ከግምት ውስጥ ባለማስገባቱ በዲዛይን ችግር ምክያት በፕሮጀክቶች ላይ ተጨማሪ ሥራ ከተጨማሪ ወጪ ጋር እንዲከሰት ማድረጉ፣

128. በባለሥልጣኑ መ/ቤቱ የተዘጋጀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ መመሪያ እና የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/1995 በአማካሪ መሀንዲሶችና በተቋራጮች በእጃቸው አለማኖሩ ፣ እንዲሁም በተቋራጩ የተዘጋጀውን የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ እቅድ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን/በትራንስፖርት ሚኒስቴር አስገምግሞ እንዲተገበር አለማድረጉ እና የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ሥራ ላይ እንዲውሉ አለማድረጉ፣

129. ለግንባታ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣የላቦራቶሪ እቃዎችና የሰው ሃይል በፕሮጀክቶች የሥራ ፕሮግራም በታቀደው እቅድ መሰረት አለመቅረብና በግንባታ ሂደት ወቅት የሚበላሹ የግንባታ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች በአፋጣኝ ተጠግነው ወደ ሥራ አለመግባት በፕሮጀክቶቹ ላይ የግዜና የወጪ ጫና በመፍጠር የማጠናቀቂያ ግዜ እንዲራዘም ማድረጉ፡፡

130. በኮንትራት ውሉ የጥራት መመዘኛ መስፈርት ክፍል አንቀጽ 1000 በሰፈረው መሰረት አማካሪ መሀንዲስ በበላይነት የጥራት ፍተሻን የሚቆጣጠርበት የራሱ የሆነ ላቦራቶሪ ሊኖረው የሚገባ ሲሆን ተቋራጩም ቅድመ ፍተሻ የሚያደርግበት የራሱ ላቦራቶሪ የሚያስፈልግ በመሆኑ አንድ ላቦራቶሪን በጋራ መጠቀም የመግባባትን ስሜት በመፍጠር የጥራት መስፈርቶች በተገበው ሁኔታ እንዳይታዩ በማድረግ የሥራውን ጥራት እንዲጓደል የሚያደርግ መሆኑ፡፡

131. የመንገድ ግንባታ ተቋራጮችየመድህን ዋስትናን ተግባራዊ አለማድረጋቸው በፕሮጀክቱ ግንባታ ሂደት ወቅት በሰራተኞች እና በንብረት ላይ ለሚደርስ ድንገተኛ ጉዳት የሚሸፍን ካሳ የሚያሳጣ ሲሆን የሥራ ዋስትና እንዲያዝ አለማድረጋቸው የኃላፊነት ግዴታ ተሰምቷቸው እንዳይሰሩ የማያደርግ መሆኑ፣

132. የዲዛይን ቅድመ-ጥናት በሚደረግበት ወቅት መንገዶች የሚያልፍባቸውን የመስተዳደር አካላትና የህብረተሰቡን መሰረታዊ ጥያቄዎችን ከየከተሞቹ አንፃራዊ እድገት ጋር አለማገናዘብ እና መንገዱ የሚገነባባቸውን ቦታዎች ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥና የአፈር ዓይነት እና የአየር ንብረት በባለሙያዎች አለማስጠናት እንዲሁም ሥራውን በአፈፃፀም ብቃታቸው ለታወቁ ተቋራጮች አለመስጠት የመንገድ ግንባታው ተጠቃሚ ህብረተሰብ በታቀደው ግዜ ባለመጠናቀቁ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት እንቅስቃሴ ተጠቃሚነት ፍጥነቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በላይ ሀገሪቱ ተጨማሪ በጀት በተጨማሪ ሥራዎች ምክንያት ወጪ እንድታወጣ ማድረጉ፣

133. ለመንገድ ዲዛይን ሥራ በቂ ግዜ ተሰጥቶ በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሰራ ባለ ማድረግ ምክንያት ለተከሰቱ ተጨማሪ ሥራዎች ሀገሪቱ አላስፈላጊ ወጪ እንድታወጣ መደረጉ፡፡

134. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው እስፔስፊኬሽን እና እስታንዳርድ መሰራታቸውን በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ጥራትና ቁጥጥር ደህንነት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት አስፈላጊው የቅርብ ክትትል አለመደረጉና እና አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ በተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚሰጡ አስተያየቶች ወይም ያጋጠሙ ችግሮችን ከግንዛቤ እንዲያካትቱ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የየሪጅኑ ዳይሬክቶሬት ኃላፊዎች ክትትል አለመደረጉ በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ማባባስና ወደ ከፋ ደረጃ እንዲደርስ የሚያደርግ መሆኑ፣

135. ተቋራጭ ለሚያደርገው የመንገድ ግንባታ የሥራ መዘግየት 10 ከመቶ የሚያዝበት ቢሆንም አሳማኝ ባልሆኑ ምክንያቶች አንቀጽ 44.1 እና 47 በመጥቀስ በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሥራ ተጨማሪ ግዜ ፍቃድ ተግባራዊ በመደረጉ የራሳቸው ድክመት አለባቸው ተብለው በዳይሬክተሮች የተፈረጁ ኪንግናም እና የጊዳሜ- ሙጊ ተቋራጮች

ለፕሮጀክቶቻቸው የመጠናቀቂያ ግዜ 3ዓመት የሥራ መዘግየት እንዲከሰት ማድረጉ፣

136. ባለሥልጣን መ/ቤቱ እያንዳንዱ የመ/ቤቱ ባለሥልጣን በበጀት ዓመት ውስጥ በእቅድ በተካተተ ፕሮግራም የመስክ ክትትልና ግምገማ የሚያደርግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣ እንዲሁም በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም የሶስትዮሽ ግምገማ በማድረግ በማስረጃ የተደገፈ የማሻሻያ ሀሳብ ለአማካሪ መሀንዲስና ለተቋራጭ አለመስጠቱ እና ልምድ ያላቸውን የፕሮጀክት መሀንዲሶች በየወሩ ለግመገማ መስክ አለመላኩ ከቅርብ ክትትል አንፃር ለፕሮጀክቶች መጠናቀቂያ ግዜ መራዘም አስተዋፆ ያደረገ መሆኑ፣

139. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ችግሮችን በሀገር ደራጃ ባላገናዘበ የውል ግዜ መራዘም ምክንያትና በራሱም ለመንገድ ግንባታዎች የሚሰራ ዲዛይን ላይ በጥንቃቄ ግዜ ሰጥቶ ባለማሰራቱና ግንባታው የሚያርፈበትን መሬትና አካባቢ አስጠንቶ ባለመግባት ምክንያት፤ ለምክንያቶች ተጋለጭ በመሆኑ በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ ለሚከሰቱ ደካማ አፈፃፀሞች የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወስድ መሆኑ፣

140. ለግንባታ የሚያስፈልጉ ማቴሪሎች የዋጋ ማነፃፀሪያ በሀገር ደረጃ አለመዘጋጀት ባለሥልጣን መ/ቤቱንም ሆነ ተቋራጩን ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ የሚችል መሆኑ፣

141. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው ከተሞችና በሚያልፉባቸው አካባቢዎች ካሉ የመስተዳድር አካላት ጋር የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር ባለመፍጠሩና በመስተዳድር አካላቱ አማካኝነት የአካባቢው ማህበረሰቦች ስለመንገድ ግንባታው ጠቀሜታ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ባለማድረጉ በመንገድ ግንባታው ሂደት የግዜ መጓተት እንዲፈጠር እንዲሁም ተቋራጭ ለመንገድ ግንባታ ያከማቻቸው ግብዓቶች በግለሰቦች ሲሰረቁ በሚመለከታቸው አካላት ተቋራጮች ትብብር እንዲያጡ ምክንያት መሆኑ፣

142. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በካሳ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 ላይ ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሳይሰራ

የካሳ ገማች ኮሚቴ ሥራ እንዲገቡ በማድረጉ የካሳ ገማች ኮሚቴዓባላት አዋጁን እና ደንቡን በአግባቡ ሥራ ላይ ባለማዋላቸው ተነሺ ህብረተሰቦችን በአሰራራቸው ቅሬታ እንዲያድርባቸው ማድረጉ፣

143. የካሳ ክፍያ አፈፃፀም አዋጅ 455/97 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ላይ በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን በመስክ በታዩት ፕሮጀክቶች የመንገድ መብት አስከባሪ ወኪልና በኮሚቴ ደራጃ በወረዳ ለተቋቋሙ ገማች ኮሚቴዎች ተገቢው ስልጠና ባለመሰጠቱ ግንዛቤ ያለገኙ የኮሚቴ ዓባላት በካሳ ግምታ ሂደት ውስጥ የተነሺ ግለሰቦች ንብረቶችን በአግባቡ ባለመገመታቸው ቅሬታዎች እንዲኖሯቸው ያደረጉ መሆኑ፣

144. ባለሥልጣኑ መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና እንዲሁም በመንገድ ግንባታው ምክንያት የመሬት ባለይዞታነት የሚያጡና ንብረት የሚያነሱ ግለሰቦችና የአገልግሎት መስመር ባለንብረቶች ቅድመ-ግንዛቤ በመስጠት የትስስር ውህደት ባለመፍጠሩና ከዚህም ባሻገር ካሳ ከከፈለ በኋላ በአዋጁ የተደነገጉትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ ለህጋዊ አካል ማቅረብ ባለመጀመሩ በግንባታ ሂደት የሚገኙ ፕሮጀክቶች ላይ የግዜ መጓተት እንዲኖር ማድረጉ፡፡

145. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ከተሰጡት ኃላፊነትና ተግባር ላይ የካሳ ግምት በሚሰራበት ወቅት የንብረቱ ዓይነት በትክክል መለየቱን፣ ልኬት በትክክል መወሰዱን፣ የቤቶች ደረጃ ፍተሀዊ መሆኑንና ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን በቅርበት በመከታተል ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ተገቢውን ሪፖርት ማቅረብ የሚል የተገለፀ ቢሆንም ካሳ የሚከፈለው አካል የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታና የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚያስፈልገው ጉዳይ ሆኖ እያለ የቀበሌ መስተዳድር አካላት በሚያቀርቡት ስም ዝርዝር ብቻ ክፍያ መፈፀሙ ሊከፈላቸው የማይገባቸውን ግለሰቦችን ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል አሰራር ሲሆን ይህ በመንገድ መብት ማስከበር ወኪሎች ክትትል ያልተደረገበት መሆኑ፡

146. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ ውሳኔ በተሰጣቸውና ካሳ በተከፈለባቸው መሬት ላይ የተሰሩት ሥራዎች ህገ ወጥ መሆናቸውን በደብዳቤ

ካሳወቀ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 በሚደነግገው መሰረት በህግ አግባብ እንዲታይ አለማድረጉ ግለሰቦች ህግ ጥሰው ያልተገባ ድርጊት እንዲፈፅሙ ማድረጉ፡

147. በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የካሳ ግምት አሰራር መኖርንበተመለከተ የሰብሎችና የቋሚ ተክሎች እንዲሁም የግንባታ ቤቶችን ከፋፍሎ ደረጃ በማውጣት ወጥ ሀገር አቀፍ ዋጋ አለመዘጋጀቱ የአገማመት ሁኔታው በአጎራባች ወረዳዎች ተመሳሳይ ንብረት ተመሳሳይ ክፍያ ባለማግኘቱ በካሳ ተከፋዮች ላይ ቅሬታ እንዲፈጠር ያደረገ መሆኑ፣

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

148. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ የዲዛይን ሥራዎች በበቂ ጥናት ላይ ተመስርተው እንዲሰሩ በማድረግ እንዲሁም በቅድመ ዲዛይን ጥናት ወቅት በማህበረሰቡና በመስተዳድር አካላት የሚሰጡ ሀሳቦችን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዲዛይን ችግር ምክያት በየፕሮጀክቶች የሚከሰቱ ተጨማሪ ሥራና ወጪ ማስቀረት ይኖርበታል፡፡

149. በባለሥልጣኑ መ/ቤት የተዘጋጀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥበቃ መመሪያ እና የአካባቢ ጥበቃ አዋጅ 295/1995 በአማካሪ መሀንዲሶችና በተቋራጮች እጅ በማኖር መተግበሩን መከታተል ፤ እንዲሁም በተቋራጩ የተዘጋጀውን የአካባቢ ጥበቃ ተፅዕኖ እቅድ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን/በትራንስፖርት ሚኒስቴር አስገምግሞ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ እንዲተገበር ማስደረግ ይገባል፡፡

150. ለግንባታየሚያስፈልጉ ግብዓቶች፣ መሳሪያዎች፣ ማሽነሪዎች፣የላቦራቶሪ እቃዎችና የሰው ሃይል በፕሮጀክቶች የሥራ ፕሮግራም በታቀደው እቅድ መሰረት ሊቀርቡና በግንባታ ሂደት የሚበላሹ የግንባታ መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች በአፋጣኝ ተጠግነው ወደ ሥራ መግባት የግዜና የወጪ ጫና በፕሮጀክቶቹ ላይ የሚቀንሱ በመሆኑ መተግበራቸውን ባለሥልጣን መ/ቤቱ መከታተል ይኖርበታል፡፡

151. ባለሥልጣን መ/ቤቱ አማካሪ መሀንዲስና ተቋራጭ የጥራት ፍተሻን የሚቆጣጠሩበት ላቦራቶሪ በየግላቸው ያላቸው መሆኑን በመቆጣጠር ሥራዎች የጥራት መስፈርቶች አሟልተው መሰራታቸውን ሊከታተል ይገባል፡፡

152. የመንገድ ግንባታ ተቋራጮችየመድህን ዋስትናንበፕሮጀክቱ ግንባታ ሂደት ወቅት በሰራተኞች እና በንብረት ላይለሚደርስ ድንገተኛ ጉዳት የሚሸፍን ካሳ ለማግኘት እንዲሁም የሥራ ዋስትና የኃላፊነት ግዴታ ተሰምቷቸውእንደሰሩ የሚያደርግ በመሆኑ ተግባራዊ ማድረጋቸው ክትትል ሊደረግበት ይገባል፡፡

153. በዲዛይን ቅድመ-ጥናት ወቅት መንገዶች የሚያልፍባቸውን የመስተዳደር አካላትና ህብረተሰብ መሰረታዊ ጥያቄዎችን ከየከተሞቹ አንፃራዊ እድገት ጋር በማገናዘብ እና መንገዱ የሚገነባባቸውን ቦታዎች ጅኦግራፊያዊ አቀማመጥና የአፈር ዓይነት

በባለሙያዎች በማስጠናት የተሻለ የሥራ ልምድ ላላቸው ተቋራጮች ሥራው መሰጠት ይኖርበታል፡፡

154. የመንገድ ግንባታ ዲዛይን ሥራ በቂ ግዜ ተሰጥቶት በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ እንዲሰራ በማድረግ የሚከሰቱ ተጨማሪ ሥራዎችንናአላስፈላጊ ወጪዎችን ማስቀረት ይገባል፡፡

155. የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው እስፔስፊኬሽን እና እስታንዳርድ መሰራታቸውን በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ጥራትና ቁጥጥር ደህንነት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

156. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሥራ አፈፃፀማቸው በደካማነት የፈረጃቸውንና ረዥም የግዜ መራዘም ለፈጠሩ ተቋራጮች ለሚያደርጉት የመንገድ ግንባታ የሥራ መዘግየት የሰሩትን ሥራ ታሳቢ ከማድረግ ካልሰሩት ላይ 10 ከመቶ ሊይይዝባቸው ይገባል፡፡

157. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከጄነራል ማናጀር አስከ ፕሮጀክት መሀንዲስ ያሉትን አመራሮች በበጀት ዓመት ውስጥ በእቅድ በተካተተ ፕሮግራም የመስክ ክትትልና ግምገማ የሚያደርግበትን ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣ እንዲሁም በዓመታዊ እቅድ በተያዘ ፕሮግራም የሶስትዮሽ ግምገማ በማድረግ በማስረጃ የተደገፈ የማሻሻያ ሀሳብ ለአማካሪ መሀንዲስና ለተቋራጭ በመስጠት ተግባራዊ ማድረግ እና ልምድ ያላቸውን የፕሮጀክት መሀንዲሶች በየወሩ ለግመገማ መስክ በመላክ የቅርብ ክትትል እንዲደረግ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

158. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በደካማ አፈፃፀም በሚፈርጃቸው በአማካሪ መሀንዲስና በተቋራጭ ላይ የማስተካከያ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

159. ለግንባታ የሚያስፈልጉ ማቴሪሎች የዋጋ ማነፃፀሪያ በሀገር ደረጃ በኢትዮጵያ እስታትስቲክስ ኤጀንሲ ማዘጋጀት አለበት፡፡

160. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክቶቹ በሚካሄዱባቸው ከተሞችና በሚያልፉባቸው አካባቢዎች ካሉ የመስተዳድር አካላት ጋር የጠበቀ ቅንጅታዊ አሰራር በመፍጠር የመንገድ ግንባታ ሂደትን በተሳካና ውጤታማ መንገድ ሊያካሂድ ይገባል፡፡

161. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በካሳ ክፍያ አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 ላይ ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት ለካሳ ገማች ኮሚቴ ዓባላት ስልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ይኖርበታል፡፡

162. ባለሥልጣኑ መ/ቤቱ በመንገድ ግንባታ ሂደት ለሚከሰቱ ችግሮች በቅድሚያ በደብዳቤ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በካሳ አከፋፈል በታወጀው አዋጅ ቁጥር 455/97 እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 የተደነገጉትን አንቀጾች መሰረት በማድረግ ለህጋዊ አካል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

163. በኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለመንገድ መብት ጥበቃ ወኪሎች ከተሰጡት ኃላፊነትናተግበር የተገለፀበመሆኑ፤ ካሳ የሚከፈለው አካል የመሬቱ ህጋዊ ባለይዞታና የንብረቱ ባለቤት ስለመሆኑ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡

164. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለልማት/ለመንገድ ግንባታ/ እንዲለቀቅ ውሳኔ በተሰጣቸውና ካሳ በተከፈለባቸው መሬት ላይ ህገወጥ እርሻ፣ ቋሚ ተክል ተከላና ግንባታ ለሚያደርጉ ግለሰቦች በደብዳቤ ካሳወቀ በኋላ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ 135/99 አንቀጽ 4 ተ.ቁ 1 በሚደነግገው መሰረት በህግ አግባብ እንዲታይ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

165. መሬት ለልማት በሚለቀቅበት ግዜ ለሚነሱ ህብረተሰቦች በካሳ ግመታ አሰራር ላይ የአጎራባች ወረዳዎችን እያነፃፀሩ በተከፈላቸው ክፍያ ቅሬታ እንዳያድርባቸው በሀገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የካሳ ግምት ዋጋ አሰራር መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡